# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

81ኛ ዓመት ቁጥር 279 ሰኔ 9 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

DERBA CEMENT



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም

- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ




# «ለሰብዓዊ ድጋፍ ወደ ትግራይ ከተጓዙት ሦስት ሺህ 297 ተሽከርካሪዎች አንድ ሺህ 128ቱ አልተመለሱም»

*- የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን*

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ሰብዓዊ ድጋፍ ጭነው ወደ ትግራይ ከተጓዙት ሦስት ሺህ 297 ተሽከርካሪዎች ውስጥ አንድ ሺህ 128ቱ እንዳልተመለሱ የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደበበ ዘውዴ በትግራይ ክልል እየተደረገ ያለውን ሰብዓዊ ድጋፍ ሁኔታ አስመልክተው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለትግራይ ክልል እየተደረገ ያለው ሰብዓዊ ድጋፍ አሁንም ቀጥሏል። በክልሉ አምስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ወገኖች ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል። እስካሁን ድረስ ሦስት ሺህ 297 ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎች ወደ ትግራይ ክልል የሰብዓዊ ዕርዳታ ጭነው ቢሄዱም አንድ ሺህ 128ቱ አልተመለሱም።

እስካሁን ለሰብዓዊ እርዳታ የተሰማሩ የጭነት ተሽከርካሪዎች ሦስት ሺህ 297 መሆናቸውን አቶ ደበበ ጠቁመው፤ እስካሁን የተመለሱት ተሽከርካሪዎች ሁለት ሺህ 169 ሲሆኑ፤ ያልተመለሱ ተሽከርካሪዎች ቁጥር

«ለሰብዓዊ ድጋፍ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# «አራት ቤተ መጽሐፍትን ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን በጠበቁ መልኩ ለልጆቻችን እየገነባን ነው»

*- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ*

**መሀመድ ሁሴን**

አዲስ አበባ፡-ትውልዱን ብሩህ የሚያደርጉ አራት ቤተ መጽሐፍት ዓለም አቀፍ ደረጃን ባሟላ መልኩ እየተገነቡ መሆናቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ትናንትን የማያውቅ ነገን አይገነባም፤ ከምድር በታች ያለውን የማያውቅ ከምድር በላይ ያለን አይገነባም፤ ሰማይ ላይ ያለውን የማያውቅ ምድር ላይ ነገ ሚመጣውን መገመት አይችልም ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር

«አራት ቤተ መጽሐፍትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# አሸባሪው ሸኔ እና ጋነግ በጋምቤላ ከተማ ከፍተውት የነበረው ድንገተኛ ጥቃት መክሸፉ ተገለጸ

አዲስአበባ፡-አሸባሪው ሸኔ እና ራሳቸውን የጋምቤላ ነፃነት ግንባር (ጋነግ) በማለት ከሚጠሩ ታጣቂዎች ጋር በመሆን በጋምቤላ ከተማ ከፍቶት የነበረው ድንገተኛ ጥቃት በፀጥታ ኃይሎች የተቀናጀ ጥረት መክሸፉን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡሞድ ኡጁሉ ገለጹ።

ርዕሰ መስተዳድሩ ጉዳዩን በተመለከተ በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ታጣቂዎቹ ወደ ጋምቤላ ከተማ ሰርገው በመግባት የሕዝቡን ሰላም ለማወክ እና ለመዝረፍ ያደረጉት ሙከራ በክልሉ እና በፌዴራል የፀጥታ ኃይሎች የተቀናጀ ጥረት ከሽፏል።

የክልሉ እና የፌዴራል የፀጥታ ኃይሎች በታጣቂዎቹ ላይ በወሰዱት የተቀናጀ እርምጃ በርካታ ታጣቂዎች መገደላቸውንም ጠቁመው፤ አሁን ላይ የጋምቤላ ከተማ በሰላም እና መረጋጋት ላይ ትገኛለች ብለዋል አቶ ኡሞድ።

የከተማዋ ነዋሪዎች ከመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ጋር በመሆን ጥቃቱ እንዲከሽፍ ላበረከቱት



**አቶ ኡሞድ ኡጁሉ**

አስተዋጽኦም ርዕሰ መስተዳድሩ ምስጋና ማቅረባቸውን ኢቢሲ ዘግቧል።

የከተማዋን ሰላም በማስጠበቅ ረገድ የፀጥታ ኃይሉ እና ኅብረተሰቡ በቅንጅት እየሠሩ መሆናቸውንም ተናግረዋል።

በከተማዋ አሁን ላይ ከመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች በስተቀር ከምሽቱ 2 ሰዓት በኋላ መንቀሳቀስ የማይቻል ስለመሆኑም ገልጸዋል።

ኅብረተሰቡ አካባቢውን ነቅቶ እንዲጠብቅ እና የትኛውም ዓይነት አጠራጣሪ ጉዳይ ሲገጥመው በአቅራቢያው ለሚገኙ የፀጥታ አካላት በመጠቆም ትብብር እንዲያደርግ ርዕሰ መስተዳድሩ ጥሪ ማቅረባቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

በሌሎች አካባቢ የሚገኙ የክልሉ ነዋሪዎችም ከፀጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት አካባቢያቸውን ነቅተው እንዲጠብቁ ጠይቀዋል።

የሽብር ቡድኑ ታጣቂዎች በከተማዋ በተወሰኑ ግለሰቦች ላይ ላደረሱት የሕይወት ጉዳትም ርዕሰ መስተዳድር ኡሞድ ኡጁሉ በክልሉ መንግሥት ስም የተሰማቸውን ጥልቅ ኀዘን ገልጸዋል።



# የትግራይ ህዝብ የህወሓት ቡድን ወደ ሰላም ፊቱን እንዲያዞር ጫና ማድረግ እንዳለበት ተጠቆመ

ገጽ 4







ዜና

# ሶስት ተቋማት ከ30 ሺህ በላይ መጽሐፍትን ለአብርሆት ቤተመጻሕፍት አበረከቱ

**ሞገስ ተስፋ**



አዲስ አበባ፡- የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር 400 ሺ ብር የሚያወጡ መጽሐፍትን፣ የአዲስ አበባ ምክር ቤት አንድ ሺ 200 መጽሐፍትንና የሪቮ ካፕ ፋውንዴሽን ከ28 ሺ በላይ መጽሐፍትን ለአብርሆት ቤተመጻሕፍት አበረከቱ።

መጽሐፍቱን ያበረከቱት የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሃመድ እንደገለጹት፣ ለአብርሆት መጽሐፍትን ለማሰባሰብ በተደረገው ጥሪ መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከተልዕኮው ጋር የሚገናኙ መጽሐፍትን አበርክቷል። በሳይንስ ዘርፍ ላይ ትኩረት ያደረጉ 400 ሺ ብር የሚያወጡ መጽሐፍት ለአብርሆት ቤተመጽሐፍት በማበርከት አሻራ አሳርፈናል ብለዋል።

በቆላማ አካባቢዎች ያሉ ሰፋፊ መሬቶችን እና በአካባቢው የሚፈሱ ወንዞችን ጥቅም ላይ በማዋል በምግብ ራስን የመቻል ተልዕኮ ለማሳካት የተመሰረተ መሆኑንም አስታውሰዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ፋይዛ መሃመድ በበኩላቸው እንደገለጹት፣ መጽሐፍቱ ማህበረሰቡን የሚያንጹና ትውልዱን የሚያነቁ ናቸው። ጥራት ባለው ቤተመጽሐፍት ጥራት ያላቸው መጽሐፍት መኖራቸው አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ምክር ቤቱ በ11ዱም ክፍለ ከተሞች በመሰብሰብ ለአብርሆት የሚመጥኑ በሳይንስ፣ በግብርና፣ በጤና ዘርፍ እና በሌሎች መስኮች ይዘት ያላቸውን 500 ሺ ብር የሚገመቱ አንድ ሺ 200 መጽሐፍትን ማበርከታቸውን ገልጸዋል።

በተመሳሳይ የሪቮ ካፕ ፋውንዴሽን 28 ሺህ 638 መጽሐፍትን ለአብርሆት ቤተመጻሕፍት ያበረከቱት የፋውንዴሽኑ የአዲስ አበባ ቃል አቀባይ አቶ አክሊሉ ታደሰ እንደገለጹት፣ ሪቮ ካፕ እንደ እ.ኤ.አ በ2011 የተመሰረተና በቡና ንግድ ስር የተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት መሆኑን ጠቁመዋል። «አንዳንዴ መጽሐፍት መገንባት ብቻ ሳይሆን የማፍረስ አቅም ስላላቸው መጽሐፍት ሲመጡ በጥንቃቄ ተመርጠው ነው» ብለዋል።

መጽሐፍቱ የሳይንስ፣ የሂሳብ፣ የኢንጂነሪንግ፣ እንግሊዝኛ፣ ኢኮኖሚክስ፣ ሶፍትዌር ፕሮግራሚንግ፣ የአይሲቲና ሌሎች ለምርምር የሚሆኑ መጽሐፍት ተመርጠው መሰጠታቸውን ገልጸዋል። መጽሐፍቶችን ለማጓጓዝ ከ15 ሺ እስከ 16 ሺ ዶላር ወስደዋል ተብሏል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማህበራዊ ዘርፍ አማካሪ ሙዓዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት መጽሐፍቱን በተረከቡበት ወቅት እንደገለጹት፣ የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴርና ሪቮ ካፕ ፋውንዴሽን አስፈላጊና ቁልፍ መጽሐፍትን በማበርከታቸው ለአብርሆት ዛሬ የደስታ ቀን ነው ብለዋል።

«አብርሆት ዘመኑን የሚመጥን ቤተመጻሕፍት ነው። ይህን መሰል ቤተመጻሕፍቶች በሌሎች ከተሞች እንዲኖሩን እንፈልጋለን» ያሉት ሙዓዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል፣ ከውጭ አገር ተገዝተው የሚገቡ መጽሐፍት ያለቀረጥ እንዲገቡ እያደረገ ያለው የገንዘብ ሚኒስቴርን እናመሰግናለን ብለዋል።

አብርሆት ቤተ መጽሐፍት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሀሳብ አፍላቂነት በአንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ተገንብቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

# የነዳጅ ድጎማን የማንሳቱ ውሳኔ ፋይዳና ሊታሰብባቸው የሚገቡ ወሳኝ ጉዳዮች

**በአክበረት ታደሰ**



አዲስ አበባ፡- ድጎማ የሚለው ቃል ጥሬ ትርጉም አንድን ኅብረተሰብ ወይም ኢንዱስትሪን ከጫና ለመታደግ ከመንግሥት ወይም ከማህበረሰብ አካል ለተወሰነ ጊዜ የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍን የሚያመለክት ነው። በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት በልዩ ልዩ ሸቀጦች ላይ ድጎማ ሲደረግ እንደነበር ይታወቃል። ከእነዚህም መካከል ዝቅተኛ ኑሮ ያለውን የማህበረሰብ ክፍል ለማገዝ በሸገር ዳቦ አቅርቦት፣ በነዳጅ፣ በሰንዴ፣ በኮቪድ 19 ወቅትም በአንዳንድ ሸቀጦች ላይ ሲደረግ የነበረውን ማንሳት ይቻላል። ይሁንና አሁን ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት የነዳጅ ድጎማን ከተመረጡ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚያስቀር የውሳኔ ሀሳብ በመያዝ ወደ እንቅስቃሴ መግባቱ ይታወቃል።

ለዚህ ውሳኔ እንደ መነሻ የተወሰደውም የድሀውን ማህበረሰብ ገንዘብ ለሀብታም ላለመደጎም፣ ለነዳጅ የሚደረገው ድጎማ የፈጠረው ዕዳ ከፍተኛ መሆን፣ የነዳጅ ድጎማው የኮንትሮባንድ ንግድን ማስፋፋቱ ወዘተ የሚል ነው። ከዚህም ጋር በተያያዘ የድጎማው መነሳት የሚፈጥራቸው አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖዎችን እንዲሁም በትግበራው ሂደት መደረግ ባለባቸው ጥንቃቄዎች ዙሪያ የዘርፉ ምሁራን የሚያቀርቡት ምክረ ሃሳብ አላቸው።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርሄ እንደሚሉት ወቅታዊ ሁኔታዎችን ምክንያት በማድረግ የሚደረግ ድጎማ ተገቢና አስፈላጊ ነው። ነገር ግን በአገራችን ከኃይለስላሴ ዘመን ጀምሮ በቋሚነት እስካሁን ሲደረግ የነበረው ድጎማ ለመንግሥትም ለሕዝብም የሚጠቅም አይደለም። በተለይ ደግሞ አገራችን ኢኮኖሚዋ በዚህ ደረጃ አድጓል፣ የህዝቡም ገቢው ጨምሯል እየተባለ ባለበት ጊዜ ድጎማ አስፈላጊ አይሆንም።

በመሆኑም መንግሥት የነዳጅ ድጎማን ማንሳቱ ትክክል ነው። ይሁንና አሁን ካለው የሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር ግን ድጎማው ሲነሳ ማኅበረሰቡ ተጎጂ እንዳይሆን ቀስ በቀስና በሂደት ሊሆን የሚችልበት መንገድ መፈጠር አለበት።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ አክለውም አገር በፈጣን ዕድገት ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ሊፈጠሩ ስለሚችሉ ድጎማ የሚያስፈልግበት አግባብ ሊኖር ይችላል። ስለሆነም በምግብ፣ በነዳጅ፣ ኢንቨስተሮች ከውጭ በሚያስመጧቸው እቃዎች ወዘተ.... ላይ ድጎማ ይደረጋል። አሁን ግን ነጻ የገበያ ሥርዓት ውስጥ ስለሆንና ኢኮኖሚውም እያደገ ስለሆነ ድጎማ መቅረት ይኖርበታል።

በዚሁ ጉዳይ ዙሪያ አስተያየት የሰጡት የኢኮኖሚ ባለሙያው ዶክተር ተክሌ አለሙ ግን ከላይ የቀረበውን ሃሳብ አይቀበሉትም። እንደ እርሳቸው አስተያየት ድጎማን በደፈናው ጠቃሚ ወይም ጎጂ ነው ለማለት ዓይነቱ ይወስነዋል። ድጎማ ሲደረግ ማነው ተጠቃሚ ?ማነው ተጎጂ የሚለውም ግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል።

ከዚህ አንጻር ነዳጅ በኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ ሲደጎም የኖረ ነው። ይህም የሆነው የነዳጅ ዋጋ መጨመር በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ትልቅ ተጽእኖ ስለሚፈጥር ነው። ስለሆነም የነዳጅ ድጎማው የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ጠቅሟል። አሁን ላይ የነዳጅ ድጎማውን ማንሳት የዋጋ ግሽበቱን የበለጠ ተጽእኖ ውስጥ እንደሚከተው ምንም ጥርጥር የለውም። በመሰረቱ ሀገራችን ላይ የነዳጅ ድጎማ ሲደረግ ብቻ አልቆየም፣ በዓለም ገበያው ዋጋው ሲቀንስም ቀንሶ አያውቅም ብለዋል።

ዶክተር ተክሌ አያይዘውም ድጎማውን ከማንሳት ይልቅ ምርታማነት ላይ መስራት ውጤታማ ያደርጋል። ያደጉ ሀገራት ላይ የሰራ ፖሊሲ እኛም ጋር ይሰራል ማለትም አይቻልም። የዕድገት ደረጃችን፣ ባህላችንና አሰራራችን የተለያየ ነውና። ለምሳሌ እነ ፊንላንድና ኔዘርላንድ ከሶስት ዓመት በፊት ይህን አሰራር ተግባራዊ አድርገውታል። ነገር ግን የእኛ እና የእነሱ የኢኮኖሚ ደረጃ፣ የህዝብ ቁጥር ስለማይገናኝ እነሱ ጋር ውጤታማ የሆነ ውሳኔ እኛ ጋር ውጤታማ ይሆናል ማለት አይቻልም።


አገራችን ካለችበት ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር የድጎማው መነሳት የሚፈጥረውን ተጽእኖ እና ተጽእኖውን እንዴት መቋቋም ይቻላል ብለን ላነሳነው ሀሳብ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ሲመልሱ የሕዝብ ትራንስፖርትና ጭነቶች አካባቢ ድጎማው ሲነሳ ወጪውን ወደ ተገልጋዩ (ወደማህበረሰቡ) ነው የሚያስተላልፉት። ስለሆነም አሽከርካሪዎች የሚጎዱበት መንገድ የለም። በተለየ መልኩ ተጎጂ የሚሆኑት ፕሮፌሽናል ሥራ የሚሰሩ ባለሙያዎችና የመንግሥት ተከፋዮች ናቸው። ለእነዚህ ደግሞ መንግሥት ገቢያቸውን የሚያሻሽልበትን መንገድ መፍጠር አለበት። ማኅበረሰቡ ከዚህ ሁኔታ ጋር ለመኖር የሚያስችለውን አቅም መፍጠር እንጂ ድጎማው መነሳት አለበት የሚለው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አይደለም ብለዋል።

ሀገራችን ካለችበት ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር መንግሥት ብዙ ካፒታል ያስፈልገዋል። የቀጣዩን ዓመት በጀት ለማሟላትም ወጪውንና ብክነትን መቀነስ እንዲሁም በከፍተኛ ሁኔታ የተንሰራፋውን ሙስና መቀነስ አለበት። ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ማህበረሰቦችን ለመታደግም የተለያዩ የሴፍቲኔት ፕሮግራሞችን መዘርጋት ያስፈልጋል።


ዶክተር ተክሌ በበኩላቸው በእኛ ሀገር ሁኔታ ድጎማው ከተነሳ በኋላ ቁጥጥር በማድረግ ኅብረተሰቡ እንዳይጎዳ መጠንቀቅ የሚቻልበት መንገድ በጣም አናሳ ነው። የሰራተኛውን ገቢ መጨመር ኢኮኖሚው ላይ የሚፈጠረውን ቀውስ ይፈታዋል የሚል ግምትም የለኝም። ዝቅተኛ ኑሮ የሚኖረውን ማህበረሰብ ለማገዝ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችን መቆጣጠር በራሱ ከባድ ነው። ደሀውን ለማገዝ ተብሎ በድጎማ የሚሸጡ ሸቀጦችንም የተለያዩ አካላት ትንሽ ብር ጨምረው ለሀብታሙ ይሸጡታል። ስለሆነም የነዳጅ ድጎማው ከተነሳ በኋላ በቁጥጥር ኅብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን ጫና መቋቋም ይቻላል ማለት እጅግ ከባድ ነው።

በአጠቃላይ ሲታይ የድሃው ገንዘብ ወደ ሀብታም ኪስ እንዳይገባ፣ ድጎማው የፈጠረውን የኢኮኖሚ ጫና ለማቃለል ብሎም የነዳጅ ኮንትሮባንድን ከማስቀረት አንጻር ድጎማውን ማንሳቱ ፋይዳ ቢኖረውም የነዳጅ ድጎማው መነሳትን ምክንያት በማድረግ የሸቀጦች ዋጋ ንሮ ኅብረተሰቡ ሊጎዳበት የሚችል ዕድል ስላለ አተገባበሩ የአስፈጻሚ አካላትን ቅንጅትና ጥንቃቄ በእጅጉ የሚፈልግ ነው።


አቶ ጌታሁን አሰፋ


አቶ ደፋሩ ስጦታው


ወይዘሮ ፍቅርተ ተክለጻድቅ


አቶ አራጌ መኮንን

# ህግ በማስከበር የተወሰደው ርምጃ አበረታች ቢሆንም የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ብዙ ሥራ ይጠይቃል

**- የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች**

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ህግን ለማስከበርና ሰላም ለማስፈን መንግሥት በሁሉም አካባቢዎች እየወሰደው ያለው የሕግ ማስከበር እርምጃ አበረታች ቢሆንም በየጊዜው እየናረ የመጣውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት አሁንም ብዙ ሥራ እንደሚጠበቅ አስተያየታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሰጡ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ገለጹ።

የአዲስ አበባ ነዋሪው አቶ ጌታሁን አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው በሰጡት ማብራሪያ የአገሪቱን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅና የኑሮ ውድነቱን ለመቅረፍ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።በእሳቸው ንግግር መሰረት ህግ በማስከበር ረገድ ተጨባጭና የሚታይ ውጤት መገኘቱን ገልጸው የኑሮ ውድነቱን ከማረጋጋት አኳያ በመንግሥት የተሰሩ ሥራዎች ያመጡት ለውጥ የጎላ አለመሆኑን ተናግረዋል።

በተለይ ህግና ሰላም በማስከበር ሥራው ላይ የሚታይም አበረታች ውጤት አለ፤ ነገር ግን ሕዝቡን እየፈተነ ያለውን የኑሮ ውድነት ለማሻሻል መንግሥት ጠንካራ ሥራ ማከናወን እንደሚኖርበት ተናግረዋል።

የሚወሰደው የሕግ ማስከበር ርምጃም በተቻለ መጠን አጥፊዎችን በመለየትና ሕግን ተከትሎ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ያሉት አቶ ጌታሁን፤ በአንጻሩ የኑሮ ውድነቱም ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰና ሕዝቡን እያማረረ በመሆኑ ፈጣን የመፍትሄ ርምጃዎች ያስፈልጉታል ብለዋል።

የሕግ ማስከበር ጉዳይ የጸጥታ ኃይሉ ሥራ ብቻ አይደለም ያሉት አቶ ጌታሁን፤ ሕዝቡ ሰላምና ጸጥታን የማስከበር ሥራ የጸጥታ አካላት ብቻ አድርጎ የማየት ችግር በመኖሩ የሚወሰዱ ርምጃዎች ሙሉ እንዳይሆኑ አድርጓል። ሰላም የሁሉም ነገር መሠረት በመሆኑ ሕዝቡ ትክክለኛውን መረጃ ለህግ አካላት በመስጠት የሚወሰደውን ርምጃ መደገፍ እንዳለበት አስገንዝበዋል።

ሕዝቡ ተገቢ መረጃ በሰጠ ቁጥር የሚወሰደው ርምጃ ትክክለኛ የመሆን ዕድሉ ሰፊ እንደሚሆን ገልጸው፤ ሕዝቡ ከፍርሃት ተላቆ የሚስተዋለውን ህግ ወጥ ተግባር ማጋለጥና አካባቢውን በንቃት መጠበቅ አለበት። መንግሥትም ለሰላምና ህግ ማስከበር የሰጠውን ትኩረት ያህል የኑሮ ውድነቱንም ለማሻሻል ብዙ ሥራ መስራት እንዳለበት አስተያየት ሰጥተዋል።

ሌላኛው አስተያየት ሰጪ አቶ ደፋሩ ስጦታው በበኩላቸው፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በምክር ቤቱ ተገኝተው የሰጡት ማብራሪያ እንደ አገር የህግ ማስከበር ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል። ይህም ተስፋ ሰጪ ውጤት የተገኘበት ነው። አሁንም ዘላቂ በሆነ መልኩ የሚታዩ ችግሮችን ሳይባባሱ መቅረፍ ይገባል። በቀጣይም የሕግ ማስከበር ርምጃው ተጠናክሮ መቀጠልና አጥፊዎች ለሕግ መቅረብ አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን ሕዝቡን እያማረረ ያለው የኑሮ ውድነት አስቸኳይ መፍትሔ ያስፈልገዋል ያሉት አቶ ደፋሩ፤ ዓለም አቀፋዊው የኢኮኖሚ ጫና እንዳለ ሆኖ አገራዊ ምርቶች ጭምር በተጋነነ ዋጋ መሸጣቸው የብዙዎችን ሕይወት እየፈተነ ስለሚገኝ አስፈላጊውን ክትትልና የቁጥጥር ሥራ ማከናወን እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ሌላኛው አስተያየት ሰጪ አቶ አራጌ መኮንን እንደገለጹት ደግሞ፤ እንደ አገር የሕግ የበላይነት መከበሩን አብዛኛው ዜጋ የሚደግፈው ጉዳይ ነው። የሚወሰደው የሕግ ማስከበር ርምጃም አጥፊዎችን ለይቶ ለሕግ በማቅረብ ሕዝቡ በሰላም ወጥቶ በሰላም እንዲገባ የሚያደርግ በመሆኑ ከህብረተሰቡ አስፈላጊው ድጋፍ ያስፈልገዋል።

በእስካሁኑ ጥረት የሕግ ማስከበር ርምጃው አበረታች ቢሆንም የኑሮ ውድነቱ ግን ሕዝቡን ለኢኮኖሚ ውድቀት እየዳረገ በመሆኑ አሁንም ህብረተሰቡ ድረስ የሚታይ ተጨባጭ መፍትሄ ያሻዋል ብለዋል።

የዋጋ ግሽበት በመቆጣጠር ረገድ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚናገሩትና ወደታች የሚወርደው መመሪያ በትክክል እየተተገበረ ነው ወይ የሚለውን መፈተሽና ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ወይዘሮ ፍቅርተ ተክለጻድቅ በበኩላቸው፤ መንግሥት በየአካባቢው ሰላም ለማስፈንና ህግ ለማስከበር በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል።በዚህም በየአካባቢው ህዝቡ ያለ ስጋት ወጥቶ እየገባ ቢሆንም ዘላቂ ማድረግ ያስፈልጋል።መንግሥት ከሰላምና ከሕግ ማስከበሩ ጎን ለጎንም ህዝቡን በእጅጉ እየፈተነ ያለው በኑሮ ውድነት ስለሆነ የኑሮ ውድነቱን ለማረገብ የሚሰራቸው ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች አማራጮችን መጠቀም ይገባል ብለዋል።

በተለይ በምግብ እህሎች፣ በሸቀጣሸቀጦችና ሌሎችም ምርቶች ላይ እንዲሁም በቤት ኪራይ ላይ በሚታዩ የዋጋ ማሻቀቦች ኗሪዎች መቸገራቸውን ጠቁመው፤ ከዕለት ዕለት እየናረ በሚገኘውን የኑሮ ውድነት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች እየፈተነ ነው። መንግሥትም ሕዝቡ ያለበትን የኑሮ ሁኔታ ተረድቶ የዋጋ ማረጋጋት ሥራውን ሊያጠናክር ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።


አቶ ሀልገዮ ጂሎ

# በደቡብ ክልል 281 ፍቃድ የወሰዱ ባለሀብቶች ወደ ሥራ ገብተዋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ክልል 13 ነጥብ 06 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ 281 ባለሀብቶች ወደ ሥራ መግባታቸውን የክልሉ ኢንቨስትመንት እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ገለጸ።

የደቡብ ክልል ኢንቨስትመንት እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሀልገዮ ጂሎ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በተለይም ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ እየቀረበ ያለው የኢንቨስትመንት ጥያቄ ጨምሯል። ዘንድሮ በክልሉ 281 ኢንቨስትመንቶች ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ ሥራ መሰማራታቸውን ጠቁመው፤ በግብርና 64 በኢንዱስትሪ 93 እና በአገልግሎት ዘርፍ 124 እንደሆኑ ተናግረዋል። ቀደም ብሎ የተያዘው እቅድ 11 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር የሚያስመዘግቡ ኢንቨስተሮች ፈቃድ እንደሚያገኙ የነበረ ቢሆንም ከታቀደው በላይ 13 ነጥብ 06 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ኢንቨስተሮች ፈቃድ እንደወሰዱ ተናግረዋል።

ሌሎች ዘንድሮ ወደ ሥራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ያሉ በከተማ 61 በገጠር 41 በድምሩ ለ102 ኢንቨስትመንቶችም 11,679.1 ሄክታር መሬት እንዲያለሙ በክልሉ ካቢኔ እንደጸደቀላቸው ተናግረዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ በዘንድሮ ዓመት ሥራ የጀመሩት ኢንቨስትመንቶች በ11 ወራት ጊዜ ውስጥ በቋሚ 8 ሺ 201 እንዲሁም በጊዜያዊ 69 ሺ 377 በድምሩ ለ77 ሺ 578 ዜጎች የሥራ እድል የፈጠሩ ሲሆን 3 ሺ790 ለሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችም የቴክኖሎጂ ሽግግር አድርገዋል።

ኢንቨስተሮች ፈቃድ ከወሰዱ በኋላ ቶሎ ወደ ኢንቨስትመንት ገብተው የሥራ ዕድል መፍጠር ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ እና የውጭ ምንዛሪ ማዳን ይገባቸዋል ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ በተሰጣቸው ጊዜ ወደ ሥራ ያልገቡ ባለሀብቶች ተገምግመው 18ቱ ላይ ተመጣጣኝ እርምጃ እንደተወሰደባቸው ገልጸዋል።

የደቡብ ክልል በተፈጥሮ የታደለ እና ለኢንቨስትመንት ምቹ መሆኑን ያነሱት አቶ ሀልገዮ ፤ ክልሉ በአሁኑ ጊዜ አንጻራዊ ሰላም ያለበት፣ ለእርሻ ምቹ የሆነ እና የማዕድናት ሀብት ያሉት ክልል እንደመሆኑ ባለሀብቶች ከዚህም በላይ እንዲመጡ ይፈለጋል። ይህንን በመገምገም ክልሉ የተሻለ የመዋቅር አደረጃጀት በመፍጠር ባለሀብቶችን በስፋት የመሳብ ሥራ ለመሥራት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ እንደሆነ ገልጸዋል።

በአገራዊ ጥሪ ለመጡት ዲስፖራዎች የክልሉን የተፈጥሮ ሀብቶች ማስተዋወቅ እንደተቻለ ጠቁመው በዚህም አንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር ካፒታል በማስመዝገብ 28 ዲያስፖራዎች እና 54 አባላት ያሉት አንድ ማህበር የኢንቨስትመንት ፍላጎት በማሳየት በክልሉ እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆኑንም ተናግረዋል። በጎፋ ዞንም ወደ ሥራ የገቡ መኖራቸውን አረጋግጠዋል።

አቶ ሀልገዮ ጂሎ አክለውም የውጭም ሆነ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ በመምጣት ለኢንቨስትመንት ምቹ በሆነውና በተፈጥሮ በታደለው በደቡብ ክልል ኢንቨስት እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበው፤ የሚመጡትን ባለሀብቶች በተገቢው ሁኔታ ተቀብሎ ለማስተናገድም በቂ ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል።

# «መንግሥት ወደ ትግራይ ክልል ያልተገደበ ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ እያደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ ነው»

**- የዓለም የምግብ ፕሮግራም**


አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ትግራይ ክልል ያልተገደበ ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ እያደረገ ያለውን ጥረት እንደሚያደንቁ የዓለም የምግብ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተር ዳቪድ ቢስሌይ ገለጹ።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን የዓለም ምግብ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተር ዳቪድ ቢስሌይ እና የስዊድን ዓለም አቀፍ ትብብር ሚኒስትር ማቲልዳ ኤርንክራንስን ትናንት በጽህፈት ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋል።

የስዊድን ዓለም አቀፍ ትብብር ሚኒስትር ማቲልዳ ኤርንክራንስም የኢትዮጵያ መንግሥት ለዜጎች ሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረስ እያደረገ ያለውን ጥረት አድንቀዋል።

በውይይቱ በግጭት እና በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች ስለሚደረገው ሰብዓዊ ድጋፍ፣ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ከተካሄደው ጦርነት ጋር ተያይዞ ስለሚነሱ የግልጽነት ጉዳዮች እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግሥት የጋራ መተማመንን በመፍጠር ረገድ እየወሰዳቸው ስላሉ እርምጃዎች ላይ ትኩረት ተደርጓል።

አቶ ደመቀ መኮንን የስዊድን መንግሥት እና



የዓለም የምግብ ፕሮግራም በኢትዮጵያ ሰብዓዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ላደረጉት ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል።

በቅርቡ በሰመራ እና ሰርዶ ኬላዎች በመገኘት ወደ ትግራይ ክልል የሚላከውን የሰብዓዊ ድጋፍ ሁኔታ መገምገማቸውን ያስታወሱት አቶ ደመቀ፣ ሰብዓዊ አገልግሎት የሚሰጡ አጋሮች ያለገደብ እንዲንቀሳቀሱ መንግሥት ቁርጠኛ አቋም ያለው መሆኑን ገልጸዋል።

ነዳጅ እና ማዳበሪያን ወደ ትግራይ ክልል በመላክ ረገድ የሰብዓዊ ድጋፍ ተቋማት በጋራ ሊሠሩ እንደሚገባ በውይይቱ ወቅት መገለጹን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።




# የመጀመሪያው የሀጫሉ ሁንዴሳ ፋውንዴሽን የኪነጥበብ ሽልማት ሊካሄድ ነው

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የሀጫሉ ሁንዴሳ ፋውንዴሽን የመጀመሪያውን የኪነጥበብ ሽልማት ሊያካሂድ መሆኑን አስታወቀ።

አርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳን ለማስታወስ በስሙ የተቋቋመው ፋውንዴሽን ሰኔ 22 ቀን 2014 ዓ.ም ሃጫሉ ሁንዴሳ የተሰኘ የሙዚቃ ሽልማት (የአዋርድ) መርሐግብር እንደሚያካሂድ ታውቋል።

የሽልማት መርሐግብሩን አስመልክቶ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ባለቤትና የፋውንዴሽኑ የቦርድ አባል ወይዘሮ ፋንቱ ደምሰው ለመገናኛ ብዙሀን በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ፋውንዴሽኑ ደረጃውን የጠበቀ የሙዚቃ ውድድር በማድረግ በኪነጥበቡ ዘርፍ ጠንካራ የፉክክር መንፈስ የመፍጠር ዓላማ አንግቧል።

በመጀመሪያው የሃጫሉ ሁንዴሳ ሽልማት መርሐግብር ከሰኔ 22 ቀን 2012 እስከ መጋቢት 22 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ለሕዝብ የደረሱ ዜማዎችና የዜማ ቪዲዮዎች ለውድድር ይቀርባሉ። ለውድድር የቀረቡት የኪነጥበብ ሥራዎችም ተገምግመው አሸናፊ የሆኑት በዕለቱ በሚዘጋጀው መድረክ ሽልማታቸውን ይረከባሉ ሲሉ አስረድተዋል።

የዘንድሮው የሃጫሉ ሁንዴሳ ፋውንዴሽን ሽልማቶች በኦሮምኛ የሙዚቃ ሥራዎች ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን የገለጹት ወይዘሮ ፋንቱ ደምሰው፤ ሽልማቱ ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚዘጋጅና በርካታ የጥበብ ዘርፎችን እያካተተ የሚሄድ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሚቀጥሉት የሀጫሉ ሁንዴሳ የኪነጥበብ ሽልማቶች ላይ ከኢትዮጵያም አልፎ አፍሪካውያን ድምጻውያኖችን ለማካተት መታቀዱን አስታውቀዋል።

እንደ ወይዘሮ ፋንቱ ገለፃ፤ ሀጫሉ ሁንዴሳ አዋርድ ደረጃውን የጠበቀ፣ ግልፅና ለኪነጥበቡ ዘብ በመቆም በአርቲስቶች መሀል ጤናማ የውድድር መንፈስ መፍጠር ይሻል። ፋውንዴሽኑም ደረጃውን የጠበቀ ውድድር በማድረግ በኪነጥበቡ ዘርፍ ለተሻለ ዕድገት መፍጠርን አላማ አድርጓል።

የዘንድሮው የፋውንዴሽኑ የሽልማት ውድድር አስር ዘርፎችን ያጠቃለለ መሆኑን ጠቁመው፤ በተለይ የዓመቱ ምርጥ ዘፈን፣ የዓመቱ ምርጥ የሙዚቃ ክሊፕ ፣ የዓመቱ ምርጥ የሙዚቃ ግጥም ፣ የዓመቱ ምርጥ የሙዚቃ ዜማ፣ የዓመቱ ምርጥ የሙዚቃ አዘጋጅ/አቀናባሪ የሚሉ የውድድር ዘርፎች መኖራቸውን ገልጸዋል።

በተጨማሪም የዓመቱ ምርጥ የሙዚቃ ክሊፕ ዳይሬክተር፣ የዓመቱ ምርጥ የሙዚቃ ክሊፕ ኢዲተር የዓመቱ ምርጥ የሙዚቃ ክሊፕ ሲኒማቶግራፊ፣ የዓመቱ ምርጥ ወንድ አርቲስት እና የዓመቱ ምርጥ ሴት አርቲስት የተባሉ ዘርፎችም በውድድሩ መካተታቸውን አንስተዋል።

ፋውንዴሽኑ ላዘጋጀው የሽልማት ውድድር አሸናፊዎች የሚለዩት ውድድሩን በሚመሩት ዳኞች በሚሰጥ የ70 በመቶ ጽምጽ ሲሆን፤ 30 በመቶው ጽምጽ የሚወሰደው ደግሞ ከሙያው አፍቃሪያን በሚላኩ የአጭር የጽሁፍ መልዕክቶች እንደሆነ ወይዘሮ ፋንቱ አስረድተዋል።

ከአጭር የጽሁፍ መልዕክቱ በተጨማሪ ሕዝብ ድምፅ እንዲሰጥበት የተዘጋጀ ድህረ ገጽ መኖሩን ጠቁመው፤ ህብረተሰቡ ባሉት ቀሪ ቀናቶች ለውድድር የቀረቡ የኪነጥበብ ሥራዎች ላይ ድምጽ እንዲሰጥ ጥሪ አቅርበዋል።

ፋውንዴሽኑ በሃጫሉ ሁንዴሳ ስም የሚሰየም የሙዚቃ ተሰጽኦ ውድድር፤ አርቲስቶች የሚሰለጥኑበት እና ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበት ሃጫሉ ሁንዴሳ የጥበብ ማዕከልን ማቋቋም እንዲሁም የፋይናንስ አቅም የሌላቸውን የኪነጥበብ ባለሙያዎች በማወዳደር የስቱዲዮ ሥራ ድጋፍ የማድረግ አላማ እንዳለውም ተገልጿል።

የሀጫሉ ሁንዴሳ ፋውንዴሽን የኪነጥበብ ሽልማት በየዓመቱ ሰኔ 22 ቀን ቀጣይነት ባለው መልኩ እንደሚከናወን ተገልጿል።

# የትግራይ ህዝብ የህወሓት ቡድን ወደ ሰላም ፊቱን እንዲያዞር ጫና ማድረግ እንዳለበት ተጠቆመ

**ማእረግ ገ/እግዚአብሔር**

አዲስ አበባ፡- የትግራይ ህዝብ የህወሓት ቡድን ከጦርነት ጉሰማ ወጥቶ ፊቱን ወደ ሰላም እንዲያዞር ጫና ማድረግ እንዳለበት የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ)የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ ገለጹ።

አቶ ሙሉብርሃን ለወጋህታ ጋዜጣ እንደገለፁት፣ ከዚህ በፊትም ሆነ አሁን መንግሥት ችግሮቹን በድርድር ለመፍታት ከፍተኛ ፍላጎት አለው፤ በዚህ የሰላም ዕድል ተጠቃሚ ለመሆን የትግራይ ህዝብ የህወሓት ቡድን ከጦርነት ጉሰማ ወጥቶ ፊቱን ወደ ሰላም እንዲያዞር ጫና ማድረግ አለበት።

ችግርን በጦርነት ለመፍታት መሞከር አገርንና ህዝብን ለከፋ ሰቆቃና መከራ ይዳርጋል ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ የህወሓት ቡድን በተለይ ከአመሰራረቱ ጀምሮ ለሰላም ዝግጁ ሆኖ አያውቅም፤የእስካሁን ልምዱም የሚያሳየው የሚያጋጥሙ ችግሮች በሰላማዊ ውይይት የመፍታት ባህሪ የለውም፤በዚህ ተጎጂው የህወሓት ቡድን አመራሮች ሳይሆኑ የትግራይ ህዝብ በመሆኑ የህወሓት ቡድን ወደ ሰላም ፊቱን እንዲያዞር ህዝቡ ጫና ማድረግ አለበት ብለዋል።

የትግራይ ህዝብ ቡድኑ ከጦርነት ጎሰማ ወጥቶ ችግርን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ጫና ከፈጠረበት ቡድኑ ፊቱን ወደ ሰላም ለማዞር እንደሚገደድ ገልጸዋል።

የህወሓት ቡድን የጦርነት ነጋሪት ቢጎስምም የትግራይ ህዝብ በዚህ ሳይታለል ለሰላም ብቻ መስራት አለበት፤ ይህ ቡድን እየተከተለው ያለው አካሄድ የጥፋት መንገድ መሆኑን ተገንዝቦ ህዝቡ አደብ ሊያስይዘው ይገባል። ምክንያቱም ከዚህ በፊት ጀምሮ የተከፈለው ውድ ዋጋ ለትግራይ ህዝብ ጥቅም ሳይሆን ለቡድኑ አመራሮች ሲባል መሆኑንም አስረድተዋል።

መንግሥት ችግሮችን በውይይት መፍታት ይፈልጋል።ይህንንም በተደጋጋሚ አሳውቋል ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ በአገሪቱ ሰላም ለማስፈን ብዙ ሥራ እየሰራ መጥተዋል፤ አሁንም እየሰራ ነው ሲሉ ገልፀዋል።

የመንግሥት ፍላጎት ሰላም መሆኑ ከዚህ መረዳት ይቻላል፤ ችግሮቹን በድርድር ለመፍታት ሲሰራ ቆይቷል፤ አሁንም እየሰራ ነው፤ ነገር ግን ህወሓት ይህንን የመንግሥት የሰላም አማራጭ ወደ ጎን በመተው የራሱን ችግር ከሌሎች ጋር እያወሳሰበና የትግራይን ህዝብ በማታለል ወደ ጦርነት በማስገባት ለከፋ ችግር እንዲጋለጥ አድርጓል ሲሉ ገልፀዋል።

ቡድኑ ጦርነት እንደ መፍትሄ በመውሰድ ሀገሪቷን ጎትቶ ወደ ጦርነት አስገብቷታል፤ በዚህም የኢትዮጵያን ህዝብ በተለይም የትግራይ ህዝብ ሊከፍለው የማይገባውን ዋጋ ከፍሏል ሲሉ ተናግረዋል።

ህወሓት የሚያጋጥሙ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ተፈጥሮአዊ ባህሪው የማይፈቅድለት በመሆኑ በተለይም ከለውጡ በኋላ የጦርነት ነጋሪት በመጎሰምና የተለያዩ ሴራ በመንደፍ መንግሥትን ጎትቶ፣ የትግራይን ህዝብ ደም በማታለል ወደ አላስፈላጊ ጦርነት እንዳስገባቸው አውስተዋል።

ከአሁን በኋላ የትግራይ ህዝብ በህወሓት ቡድን የውሸት ፕሮፓጋንዳ ሳይታለል ከመንግሥትና ከሰላም ፈላጊ አካላት ጎን በመቆም ለሰላም የበኩሉን አዎንታዊ ሚና እንዲጫወትም ጥሪ አቅርበዋል።

# «ለሰብዓዊ ድጋፍ...

ከገፅ 1 የዞረ

አንድ ሺህ 128 ናቸው። ባልተመለሱ ተሽከርካሪዎች የሚመለከተው አካል ክትትል የሚያደርግ ይሆናል።

ለሰብዓዊ አገልግሎት ከአዲስ አበባ መቀሌ 236 በረራ መደረጉን አመልክተው፤ይህም በአጋር አካላት አማካኝነት ለሰውና ሰብዓዊ እርዳታ ጭነት ምልልስ የተደረገ ጉዞ እንደሆነ ገልጸዋል።

ሰብዓዊ ድጋፉ እየተደረገላቸው ያለው በ95 አጋር ድርጅቶች አማካኝነት መሆኑን ጠቁመው፤ድጋፉ ነዳጅን ጨምሮ ጥሬ ገንዘብ፣ መድኃኒትና የተመጣጠነ ምግብ እንዲሁም ምግብ ነክ ያልሆኑትን ጭምር ያካተተ እንደሆነ ነው አቶ ደበበ ያሳወቁት።በተጨማሪም ከሚያዚያ ወር ጀምሮ በለጋሽ አካላት አማካኝነት ሁለት ሺ 502 ተሽከርካሪዎች ሰብዓዊ ድጋፍ ጭነው መቀሌ መድረሳቸውን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ደበበ ገለጻ፤ እስካሁን ባለው ሁኔታ በጥሬ ገንዘብ ሁለት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ፣216ሺህ 91ኪሎ ግራም መድኃኒት እና 421ሺህ977 ኪሎ ግራም የተመጣጠነ ምግብ በአጋር ድርጅቶች አማካኝነት በአየር ትራንስፖርት ወደ መቀሌ መጓጓዙንም ጠቅሰዋል።

130ሺ 200ኪሎ ግራም ምግብ ነክ ያልሆኑ እንደ ውሃ፣ ንጽህና መጠበቂያ መጠለያና ቁሳቁስ እንዲሁም የእርሻ ግብአቶች በአየር ትራንስፖርት መጓጓዙን ተናግረዋል። ለህጻናት፣ ለነፍሰ ጡሮች፣ ለአጥቢ እናቶች እንዲሁም ለአቅመ ደካማዎች የሚውል112ሺህ 492 ሜትሪክ ቶን የተመጣጠነ ምግብን ጨምሮ በየብስ ትራንስፖርት ከሐምሌ ወር 2013ዓ.ም ጀምሮ እንደተጓጓዘም ገልጸዋል።

ውሃ መጠለያ ቁሳቁስና የንጽህና መጠበቂያ እቃዎችን ጨምሮ 15ሺህ 554ሜትሪክ ቶን ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች በየብስ ትራንስፖርት እየተጓጓዘ እንዳለም አመላክተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም 782ሺህ 396 ሊትር ነዳጅ ከሚያዝያ ወር 2014ዓ.ም ጀምሮ በየብስ ትራንስፖርት እየተጓጓዘ እንዳለ አስታውቀዋል።

# «አራት ቤተ መጽሐፍትን...

ከገፅ 1 የዞረ

ዐቢይ አሕመድ ተናግረዋል።

ትውልዱን ብሩህ የሚያደርጉ አራት ቤተ መጽሐፍት ዓለም አቀፍ ደረጃን በአሟሉ መልኩ እየተገነቡ መሆናቸውን ገልጸዋል።ከተገነቡት ቤተ መጽሐፍት የመጀመሪያው አብርሆት ቤተ መጽሐፍት መሆኑን ጠቁመው፤አብርሆት ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የተገነባና መጽሐፍት በዲጅታል ተሰንደው አገልግሎት የሚሰጡበት መሆኑን ጠቅሰዋል።

ሁለተኛው ቤተመጽሐፍት ሳይንስን የሚማሩ ልጆች በቀላሉ እውቀት የሚቀስሙበት የሳይንስ ሙዚየም ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከቦይንግና ከሌሎችም ኩባንያዎች ጋር እየተነጋገርን ነው ብለዋል። ልጆቻችን አውሮፕላን ማብረርን በተግባር እንዲማሩ ይደረጋል፤ ለምን ካላችሁ መፍጠር እንዲችሉ ብለዋል።

ሶስተኛው በቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ የሚገነባውና ስድስት ሺህ አገር በቀል እጽዋትን የሚይዘው ቦታኒክ ላይብራሪ (ፕላንት ላይብራሪ) ነው። በዚህ ላይብራሪ የሚመራመሩ ሰዎች በቀላሉ መጥተው በተግባር መመራመር እንደሚያስችላቸው አስረድተዋል።

አራተኛው በከርሰ ምድር ያሉትን ማዕድናት የሚያሳይ ላይብራሪ ገንብተናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለምን የከርሰ ምድር ሀብታችንን ካወቅን ፣ዩኒቨርስና ፊውቸር ሳይንስን ካወቅን ፣በምድር ላይ ያሉትን እጽዋት ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ ካወቅንና የተጻፈ ታሪካችንን ካወቅን የተሻለች አገር ለመገንባት እንችላለን ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ከምክር ቤት አባላት በትናንትናው ዕለት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልስና ማብራሪያ መስጠታቸው ይታወሳል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ወደ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ለመሻገር ስለጊዜ ያለንን አስተሳሰብ እንግራ!

አንድ ሕዝብ እንደ ሕዝብ ከሚያጋጥሙት ተግዳሮቶች አንዱ ለረጅም ዘመን በአንድ የታሪክ ምእራፍ ውስጥ መገኘቱ ነው። መሄድ መሻገር እየፈለገ ባለበት ዘመናት የማስቀጠሩ እውነታ ለሕይወት ያለውን ትርጓሜ በማበላሸት እንደ ሕዝብ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንደሚያስገባው ይታመናል።

ይህ ተስፋ መቁረጥ በራሱ ያ ሕዝብ እጁን አጣምሮ ትናንቶችን እንዲያመልክ፤ ዛሬና ዛሬዎች ለሚጠይቁት መስዋእትነት ራስን በማዘጋጀት ዘመን የሚያሻግረውን ድልድይ ከመስራት ይልቅ ጎርፍ እስኪያልፍ መጠበቅ አለበለዚያም በጎርፍ ውስጥ ዕድሉን የመሞከር ደመነፍስ ይዞ እንዲጓዝ ያደርገዋል።

ይህ በዘመን ውስጥ ዘመን የማስቀጠር እርግማን አንድም እንደ ትውልድ በታሪክ ውስጥ ያለን ስፍራ ካለመረዳት፤ ከዚያም በላይ ስለጊዜ ተገቢውን ግንዛቤ ካለመፍጠር የሚመነጭ የአስተሳሰብ/ የግንዛቤ ክፍተት እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል። ይህንን ፈጥኖ አለማረም በእርግማኑ ተጠልፎ ከታሪክ ተፈጥሯዊ ሂደት የመታገት ያህል ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ህዝብ ከዛሬ ይልቅ ትናንት ላይ የመቆማችን፤ ከነገ ተስፋችን ይልቅ በትናንት ታሪካችን መወሰዳችን የዚሁ እውነታ አንዱ መገለጫ ነው። በእጃችን ያለውን ዛሬ አቅልለን ማየታችን፤ በዚሁ የአስተሳሰብ መሰረት ነገን ተስፋ ማድረጋችን ብዙ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል።

በእርግጥ ለትናንት ታሪካችን ያለን ከበሬታ በትናንት ላይ ለተገነባው ማህበረሰባዊ ማንነታችን ውቅር፤ ስለ ራሳችን የጠራ ግንዛቤ እንዲኖረን በማስቻል ለማንነታችን ጠንካራ ማኅበረሰባዊ መሰረት ነው። እንደ ትውልድ በአንድ የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ሰርተን የምናልፈው የራሳችን ታሪክ እንዳለን አለመረዳት ግን ከታሪክ ፍሰት የሚያወጣን አዚም ነው።

ይህ አዚም እንደ አገር ብዙ መቶ ዓመታትን በአንድ የታሪክ ምእራፍ ውስጥ እንድንዳክር እያደረገን ይገኛል። በዚህም እስካሁን/እስከዚህ ትውልድ ድረስ ከቆምንበት ዘመን የምንሻገርበትን ድልድይ መገንባት አቅቶን በአንድ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ ለመገኘት ተገደናል። በዚህም እየኖርንበት ያለው የሕይወት ሁደት ትልቅ ታሪክ እንደነበረው ሕዝብ የሚመጥነን አልሆነም።

ከዚህ የተነሳም ስለ ትናንቶች በመተረክ ብዙ ዛሬዎችን ለማጣት ተገደናል። በትውልዶች መካከል በየዘመናቱ ተስፋ ያደረግናቸው ህልሞቻችን ከህልም ባለፈ ተጨባጭ ተስፋ ሊሆኑልን አልቻሉም። ከዚያ ይልቅ ሰብዓዊ የሆነውን ተስፈኛ ባህሪያችንን እየሸረሸሩት ወደ ቁዘማና ከዚህ ወደሚመነጭ ተስፋ መቁረጥ እንድንጓዝ ያስገደዱን ታሪካዊ ክስተቶች ብዙ ናቸው።

ይህ ስለ ጊዜ፤ ከዚያም በላይ እንደትውልድ በጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ያለንን ኃላፊነት በአግባቡ ያለመረዳት የትውልዶች /የማህበረሰባችን ችግር ዛሬም ለጀመርነው የለውጥ ጉዞ / የሽግግር ጉዞ ዋነኛ ተግዳሮት ሆኗል። ዛሬም ትናንትናና ትናንቶች በወለዷቸው አስተሳሰቦች በጊዜ ሁደት ውስጥ ወደኋላ ተመልሰን ለውጡ በብዙ መንገጫገጮች ውስጥ እንዲያልፍ ምክንያት እየሆንን ነው።

በአንድ በኩል ለውጥ በአንድ የጊዜ ማዕቀፍ የሚተገበር ማህበራዊ ንቅናቄ መሆኑን ያለመረዳትና ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነት አለመፍጠር ፤ በሌላ በኩል ለውጡ የሚጠይቀውን ፍጥነት ከጊዜ አንጻር አለማስላት ለለውጡ ትልቁ ተግዳሮት ሆኗል። ለውጡን ከተፈጥሯዊ ባህሪው ውጭ በትናንቶች የመገምገም ሂደትም ለውጡን በጊዜ ሁደት ውስጥ አዝጋሚ እያደረጉት ይገኛል።

ለዚህም ነው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሰሞኑን ፓርላማ ተገኝተው ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ሲሰጡ ስለ ጊዜ ባለን ግንዛቤ ዙሪያ ሰፊ ሰዓት ወስደው ለማብራራት የሞከሩት። ሕዝባችን እንደ ህዝብ፤ ትውልዱም እንደ ትውልድ ስለጊዜ ያለውን አስተሳሰብ ማረም ካልቻለ ተስፋ የምናደርጋቸው ነገሮቻችን በራሳቸው የሚጨበጡ ተስፋዎች እንደማይሆኑ አጽንኦት ሰጥተው ያሳሰቡት።

በእርግጥም ለረጅም ዘመናት ከቆምንበት የታሪክ ምዕራፍ ወጥተን በሚጨበጥ ተስፋ ወደ ተሞላ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ለመሻገር፤ በአንድ የታሪክ ምእራፍ ብዙ ከመቆማችን የተነሳ ካለንበት አሻጋሪ ያልሆነ አስተሳሰብ ለመውጣት፤ ከዚያም በላይ አስተማማኝ ዘመንና አሻጋሪ ድልድይ ለመገንባትና ትውልዶችን ለማሻገር ስለጊዜ ያለንን አስተሳሰብ መግራት ይጠበቅብናል። ለዚህም ከራሳችን ጋር ልንታረቅ ይገባል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የውጭ ተጽእኖና ተግዳሮት የማይለየው የኢትዮጵያ አንድነት

ክብረ ነገስት

ኢትዮጵያ ከውጭው ዓለም ጋር ፖለቲካል፣ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ግንኙነት ማድረግ የጀመረችው ከአክሱም ሥርዎ መንግስት በፊት እንደነበረ የታሪክ ድርሳናት ይናገራሉ። በዚህ ወቅት የነበረው የኢትዮጵያ ግንኙነት ሁለንተናዊ ጥቅሟን ማስከበር ብቻ ሳይሆን የውጭውን ዓለም ተፅዕኖ ጭምር መመከት የቻለ እንደነበርም ይታወሳል።

ይሁን እንጂ ከአክሱማይት ሥርወ መንግስት መዳካም ጋር ተያይዞ ብዙ ነገሮች እንዲቀየሩ ሆነዋል። አንዱ በአውሮፓ የተፈጠረው የአውሮፓዊያን ተሃድሶ (EUROPIAN RENASSANCE) ሲሆን፤ ሌሎች አገራትን ለመርገጥ የሚያስችላቸውን ስትራቴጂ የቀየሱበት ነው። ቀድመው ይዘውት የነበረውና ለዘመናት ሲከተሉት የቆየው በሃይማኖት እና በባህል ላይ ያተኮረው ተግባር አዋጭነት ያለው አልነበረም። ስለዚህም ወደ ሰውኛ ሥራ (humanistic activity) እንዲቀይሩት አድርጓቸዋል። ይህ ደግሞ ፍላጎታቸውን እንዲያሰርጹ ያገዛቸው እንደሆነም ይታመናል።

ይህ አስተሳሰባቸው ደግሞ ከአውሮፓ ውጭ ያሉ ዓለማትን ጭምር እንዲያውቁ ያጓጓቸውና ፍላጎታቸውን ያሰፋላቸው ሆኗል። በዚህም አውሮፓዊያን መላ ዓለምን ለማሰስ በቁ። እነአሜሪካን የመሰሉ አዲስ አህጉር የመገኘታቸው ምስጢርም ይኸው ነው። እነኚህ በአሳሽነት ስም በየአገራቱ የሚዘዋወሩ አውሮፓዊያን በንጉሳቸው እና በንግስታቸው ድጋፍ እንዲሁም በአሳሾ ፍላጎት የሌሎችን አገራት ጥቅም እየደፈጠጡ እንዴት የራሳቸውን አገር ጥቅም ማስከበር እንደሚችሉ በትጋትም ሰርተዋል። በዚህም በቀረው ዓለም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድረዋል። በዚህ ዘመን ሃይማኖትን ሽፍን ተደርጎ በኢትዮጵያ የተፈጠሩ አገራዊ አንድነታችንን የሚፈታተኑ ጦርነቶች ዋና ተዋናኞችም እነሱም ስለመሆናቸው የሚሞግቱ የታሪክ ሰዎች አሉ ።

ከአጼ ፋሲለደስ ንግስና በኋላ ሸፍጠኞቹ አውሮፓዊያን ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ተደርገው ነበር። ሆኖም ሥራቸው እንዳይጠፋና እንዲቀጥል የተከሉት ነገር ነበር። አንዱ ከሃይማኖት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሲሆን፤ እንደ ቅባት፣ ጸጋ፣ የስጋ ልጅ ወዘተ የሚባሉት ተተክለው የቀሩት በዚህ ምክንያት እንደሆነም ይነገራል።

ከተሃድሶ ዘመናቸው ቀጥሎ የተፈጠረው ደግሞ አውሮፓዊያን በዓለም ፖለቲካና ኢኮኖሚ ላይ ጫና እንዲያደርጉ መጓዝ ሲሆን፤ ለዚህ ማሳያው በፈረንሳይ የተጀመረው የምሁራን ንቅናቄ (Enlightenment) እና በእንግሊዝ ተጀምሮ በኋላም በመላ አውሮፓ የተዛመተው የኢንዱስትሪ አብዮት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እነኚህ ሁለት ነገሮች የዓለምን ሁለንተናዊ ቁመና ቀይረውታል። በተጨማሪም የአውሮፓዊያንን ኃያልነት አሳይተዋል። በተለይም የኢንዱስትሪ አብዮት አውሮፓዊያኑ አፍሪካን እንዲቀራመቱ ያስቻለ እንደነበር ይገለጻል።

አውሮፓዊያን በበርሊን ኮንፈረስ ተስማምተው አፍሪካን ለመቀራመት ሲመጡ ከአውሮፓዊያን የቅርጫ ዝርዝር ውስጥ በግንባር ቀድምትነት የገባቸው ኢትዮጵያ ነበረች። በመካከለኛው ዘመን በኢትዮጵያ ላይ ያደረሱት ግፍ አልበቃ ብሏቸው የኢንዱስትሪ አብዮትን ተከትሎ ጣሊያን የተባለች በቅጡ እንኳን ያልተዋሀደች አገር በእንግሊዝ መንገድ ጠራጊነት ኢትዮጵያን የወረረችውም ለዚህ ነበር።

ለውጭ ጫና አይበገሬዎቹ ኢትዮጵያዊያን ጣሊያን በመጣችበት እግሯ አሳፍረው መልሰዋታል። በዚህም ቂም ያረገዙ ጣሊያውያንን በአንድ በኩል ሌሎች የአውሮፓ አገራት ደግሞ የአገሪቱን አንድነት አደጋ ውስጥ ለመጣልና ለጥቅማቸው ሲሉ በሌላ በኩል እየተጓዙ አጋጣሚዎች ሲጠብቁ ቆይተዋል። የ1906 ዓ.ም የንጉሰ ነገስት ምኒልክ መታመምና ንጉሰ ነገስቱ አልጋ ወራሽ የሚሆን ወንድ ልጅ ያለመኖራቸው የአገሪቱ ክፍተት ነው ብለው እንዲያስቡ አድርጓቸዋል።

ክፍተቱን ለመጠቀምም ሶስቱ የአውሮፓ አገራት ማለትም እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ እና ጣሊያን የሶስትዮሽ ስምምነት (Tripartite treaty) ተፈራረሙ። የስምምነቱ ዓላማም ኢትዮጵያን በማተራመስ ለሶስት መቀራመት ነበር። ነገር ግን የአውሮፓዊያን ሴራ የገባቸው ንጉሰ ነገስቱ ክፋታቸውን የሚያሽር ሁነኛ መድሃኒት አበጁ። አንደኛው አልጋ ወራሼ ልጅ እያሱ ነው ብለው ያስነገሩት ሲሆን፤ ሁለተኛው ዘዴ ደግሞ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ማቋቋማቸው ነበር። በዚህም የአውሮፓዊያን ፍላጎት ድባቅ ተመታ።

ቀን ከሌሊት ለኢትዮጵያ የማይተኙት አውሮፓውያኑ አሁንም ሌላ ሴራ አሴሩ። ይህም በአዲስ አባባ ቆንስላ ጽህፈት ቤታቸውን በመክፈትና በቆንስላዎቻቸው አማካኝነት የኢትዮጵያን ስም በዓለም አቀፍ ማህበረሰቡ ዘንድ ማጠልሸት ነው። በርካታ ቆንስላዎች እና ዲፕሎማቶችም ተግባሩን ፈጽመውታል። ከእነኚህ መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው «ኢትዮጵያ የባሩድ በርሜል» የተሰኘ መጽሐፍ ደራሲው የአስትሪያው ዲፕሎማት ሮማን ፕሮቻዝካ አንዱ ነው። ይህ ሰው ከዲፕሎማሲያዊ ተግባሩ ባፈነገጠ መልኩ ኢትዮጵያን ሊያጠፋ የሚችል ሥራ ሲሰራ በመገኘቱ ከጣሊያን ወረራ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ በ1927 ዓ.ም ከኢትዮጵያ የተባረረ ነው። በመጽሐፉም አውሮፓዊያን ኢትዮጵያን መበታተን/ ማጥፋት እንዳለባቸው አጥብቆ የመከረም ነበር። ይህን ማድረግ ካልቻሉ ደግሞ ኢትዮጵያ አፍሪካን አስተባብራ ለአውሮፓዊያንን ቀጣይ ስጋት ልትሆን እንድምትችልም አስጠንቅቋል።

መጽሐፉ በተጻፈ በዓመቱ በ1928 ዓ.ም ጣሊያን ኢትዮጵያን እንድትወር ሆነ። ኢትዮጵያን ለማጥፋትም የመርዝ ጋዝ እስከመጠቀም ተደረሰ። በዚህ ጊዜ የዓለም ማህበር አባል አገር የሆነችው ኢትዮጵያ የደረሰባትን በደል ለማሰማት ወደጀኔቭ ብትሄድም ነገሮችን ከራሳቸው ጥቅም አንጻር የሚያዩት አውሮፓዊያን ሊሰሟት አልወደዱም። እንደውም ይባስ ብለው በኢትዮጵያዊያን ቁስል ላይ ተሳለቁባት።

ይህን ጊዜ እጅ መስጠት የማያውቁት ኢትዮጵያዊያን በጋራ ተነሱ። ስላቃቸውን አስውጠውም አስጎነበሷቸው። በእብሪት የተወጠረ ልባቸውንም አፈነዱት። ማንም እንደማይደፍራቸው አስመሰከሩም። በአንድነታቸው አገራቸውን ታድገው ቀና ማለትን ለጥቁር ሁሉ አስተማሩም።

እነዚህ ሀይሎች ይህ ሁሉ አልበቃ ሲላቸው ኢትዮጵያንን በመከፋፋል የአገሪቱን አንድነት ፍጽም አደጋው ውስጥ ሊጨምሩ በሚችል መልኩ ወደ ውጭ ለትምህርት አውሮፓ እና አሜሪካ የሚሄዱ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ግማሾቹን በገንዘብ በመደለል ግማሹን ደግሞ በማታለል ኢትዮጵዊያን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ሰላም በመንሳት መከፋፋል የሚያስችላቸውን አውዳሚ የፖለቲካ መርዝ በፖለቲካ ቤተሙከራቸው ውስጥ ፈጥረዋልም። ይህም የብሔር ብሔረሰቦች መብት የሚል ሽፋንን የያዘ ሲሆን፤ በአሸባሪው ሕወሓት አስፈጻሚነት ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል። አሁንም ድረስ ለአገሪቱ ተግዳሮት ሆኖ የቀጠለ የፖለቲካ ነቀርሳ ሆኗል። ተግባሩ ሲፈጸም በፖለቲካ መርዙ የተበከሉት ኢትዮጵያዊያን አገር ውስጥ በመግባት ሌሎችን እንዲከትቡ በማድረግ ነው።

በዘመነ ደርግ ጀምሮ ኢትዮጵያዊያን እርስ በእርስ የተበላሉት በዚህ ተክል ምክንያትም ነው። ለበርካታ ኢትዮጵያዊያን ሕይወት መቀጠፍም ምክንያትም ነበር። ኤርትራን ከእናት አገሯ እንድትገነጠል ያደረገውም ይኸው ምስጢር ነው። ኢትዮጵያንም ያለ ባህር በር እንድትቀርም ያደረጋት ይኸው ጉዳይ እንደሆነ ነጋሪ አያሻውም።

በእርግጥ ከጥንት እስከዛሬ ምዕራባዊያን በኢትዮጵያ ላይ የሚደግሱትን የጥፋት ድግስ በአንክሮ ስንመለከተው ለምን አይተውንም ያስብላል። መቼ ነውስ ከኢትዮጵያ ላይ እጃቸውን የሚያነሱት እንድንል ያደርገናል። ይሁን እንጂ ኃያልነት ሁሉም የሚፈልገው ነውና መነካካቱ አይቀሬ ነው። እናም እንደአገር አይበገሬና አልደፈርም ባይነታችንን ለማስቀጠል ከፈለግን አንድነታችን ከምንም በላይ ማስቀደም ያስፈልገናል። መፈለጋችንንም ልንጠላው አይገባም።

ሌላው ከእኛ የሚፈልገው ትልቅ ማንነት አለን። ያንን ደግሞ አለማስነካት የእያንዳንዳችን ድርሻ ነው። ብርታታችን፤ ሀብታችንና ጀግንነታችን ዘላለማዊ እንጂ የአንድ ዘመን እንዳልሆነም ማመንና መተግበር አለብን። በአባቶቻችን አይበገሬነት እንዲሁም በሕብረ ብሔራዊነት የምዕራባዊንን የጥፋት ድግስ ማክሰምና ወደፊት መጓዝ ይጠበቅብናል። ለዚህ በጎ አሳቢነት ቀዳሚ ነውና እርሱን እንያዝ በማለት ለዛሬ አበቃን። ሰላም !!!

# ነፃ ሃሳብ



**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ጽሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ማመን ኪሳራ

ኡሊሴስ ግራንት ከአሜሪካ መስራች አባቶች እንደ አንዱ ተደርጎ ስሙ በበጎ ይነሳል። የጥምር ሀይሉ አዛዥ፤ የአሜሪካ 18ኛው ፕሬዚዳንት ነበር። ይሁንና በማምሻ ዕድሜው ቤሳቢስቲን የሌለው ድሀና በድብርት የአእምሮ ህመም የሚሰቃይ አግኝቶ ያጣ ሆኖ ነው ህይወቱ ያለፈው። ግራንትን ለዚህ የዳረገው አጭበርባሪ የንግድ ሸሪኩ ነው። በማታለል መኖሪያ ቤቱን ፤ በእርስ በርሱ ጦርነት የተሸለማቸውን የጀግና ሜዳሊያዎችን ሳይቀር እንዲሸጥ አደረገው። ግራንት በአንድ ወቅት ለጠበቃው፤"ሰው ማመን የህይወቴ መርህ ነበር ፤ ከዚህ በኋላ ግን ሌላ የሰው ፍጡር እንዴት ላምን እንደምችል አላውቅም።" ሲል ነግሮታል።

እንዲህ እንደ ግራንት ባመኗቸው የንግድ ሸሪካቸው ወይም አጋራቸው የተከዱትን ቤቱ ይቁጠራቸው ። በዚህ የተነሳ በአንድ ጀምበር ያጣ የነጣ ድሀ በመሆናቸው ትዳራቸውና ቤታቸው የተፈታ፤ ልጆቻቸው ጎዳና የወጡ የትየለሌ ናቸው። በወላጆችና በልጆቻቸው አእምሮ ላይ ትቶት የሚሔደው ጠባሳም ቀላል አይደለም። ታዋቂው የራሽያ ጸሐፊ ተውኔት አንቶን ቼከሆቭ፤" ሰዎችን ማመንና በሰዎች መተማመን አለብህ ። ካለዚህ ህይወት የሚታሰብ አይደለም።" ይላል። በንግድ ሸሪካቸው ወይም አጋራቸው ለተከዱ ፤ ባመኗቸው ሁሉን ነገራቸውን ለተነጠቁ ይህ የቼከሆቭ ምክር ውሃ ያነሳል ለማለት ይቸግራል።

አለመተማመን ወይም ጤናማና ቀጣይ ለሆነ ግንኙነት መሟላት ያለበት ዝቅተኛው ሰው የማመን መስፈርት ሲጎል "የማመን ኪሳራ"("Trust deficit") ይሰኛል ይለናል ስኮት ባራዴል፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ እልፍ አእላፍ መጻህፍት ተጽፈዋል። ፊልሞች ተሰርተዋል። የሀገራችን ፊልሞችና ድርሰቶች አጽመ ታሪክ ገጸ ባህሪያት ባመኗቸው ሰዎች ሲከዱ በዚህ የተነሳ ለተለያዩ ፈተናዎች ሲዳረጉ የሚያሳዩ ናቸው። ከዚህ አልፎ ሰውን ማመን ቀብሮ ነው፤ እገሌ/እገሊት የተልባ ስፍር ነው ማለት የዕለት ተዕለት ንግግራችን አካል መሆኑ ሰዎችን በማመን የከፈልነውን ዋጋ የሚያስታውስ ነው።

ጉግል ኒውስ ላይ ገብተን"የማመን ኪሳራ"በሚል ብንፈልግ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ዜናዎችን እናገኛለን ይለናል ባራዴል፤ ከእነዚህ ዜናዎች አብዛኞዎቹ በሰዎችና በተቋማት መካከል ስላሉ ግንኙነቶች የሚያትቱ ናቸው። ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች በመንግስት፣ በፖሊስ፣ በልሒቃን፣ በሚዲያና በሌሎች ተቋማት ላይ ያላቸው እምነት እየተሸረሸረ መምጣቱን የሚያመለክቱ ናቸው። በሀገራችን የሚስተዋለው የማመን ኪሳራም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በተቋማት ላይ ዕምነት ማጣት ከጀመረ ከረምረም አለ። ይህ ያደረና የባጀ አባዜ ደግሞ ሀገሪቱንም ሆነ ዜጋውን በምንም ሊተመን የማይችል ውድ ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል። ዛሬ ሀገራችንን መቆሚያ መቀመጫ ያሳጣት፤ እረፍት የነሳት፤ እንደ ገበታ ውሃ የሚንጣት ሀሰተኛና የተዛባ መረጃ፣ የተዛባ ትርክት፣ የሴራና የደባ ፖለቲካ፣ ወዘተረፈ የዚህ የማመን ኪሳራ ቅርሻ ነው። በሚዲያዎቻችንና በተቋማት ላይ ዕምነት ማጣታችን ለሚያርተኝነት ዳርጎናል።

ቁጥሩ ቀላል ያልሆነ ዜጋ በቀደሙት 27 አመታት ሆነ ከዚያ በፊት በነበሩ አገዛዞች የተነሳ በመንግስት ማለትም በሕግ አውጭው፣ ተርጓሚውና አስፈጻሚው ዕምነት የለውም። በፓርላማው፣ በፌዴሬሽን ምክር ቤቱ ፣ በፍርድ ቤቶች፣ በፖሊስ፣ በዐቃቢ ሕጉ ፤ በጤና፣ በትምህርት፣ በኢኮኖሚ፣ በሚዲያው፣ ወዘተረፈ ተቋማት (institutions)ላይም እምነት የለውም። በዚህ የተነሳ በሒሳብ መዝገቡ ያልተወራረደ የማመን ኪሳራ ይታያል። ከፈጠረው ሀንጎቨርም ገና በቅጡ አላገገምንም። ሕዝቡ መንግስት በተባለው ተቋም ዕምነት አልነበረውም። እኔን ለማገልገል ሳይሆን የስልጣን ጥሙን ለመቁረጥ፤ ጥቅሙን ለማሳደድ፣ ሀብት ለማካበት፣ የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም፣ የአንድ የተወሰነ ቡድንን ፍላጎት ለማስፈጸም፣ ወዘተረፈ የተመሠረተ ተቋም እንጂ ሕዝብን ለማገልገል የተመሠረተ አይደለም ብሎ ስለሚያምን አልፎ አልፎ እንደ መናጆ ሆነው ከመንግስት የሚወርዱ ለሕዝብ ጥቅም የሚሰጡ ተግባራትን እንኳ በጥርጣሬ ነበር የሚያያቸው።

በተለይ በሕወሓት/ኢህአዴ አገዛዝ ገና ከመነሻው መንግስት የተሰኘው ተቋምም ሆነ ጠቅላላ መዋቅሩ አንድን ቡድን ብቻ እንዲያገለግል ተደርጎ ነው በአምሳሉ ተጠፍጥፎ የተሰራው። ሕግ አውጭው፣ ተርጓሚውና አስፈጻሚው የአገዛዙን ጥቅምና ፍላጎት ለማስከበር በታማኝነት የቆሙ ነበሩ። የሶስቱም የመንግስት አካላት ግብ የሕወሓትን ተልዕኮ እንዲያስፈጽሙ ተደርገው እንጂ ግንኙነታቸውንና አሰራራቸውን መቆጣጠሪያ ወይም ሚዛንና መድለው Check and balance ለማስጠበቅ አልነበረም። የሕወሓትን ሀጢያት የሚያበዛው በመንግስትና በተቋማቱ እንዳናምን ማድረጉ ሳያንስ ለ27 ዓመታት ተቋማዊና መዋቅራዊ አድርጎ በመሐላችን በጎነቆለው ጥላቻና ልዩነት እርስ በርስ እንዳንተማመን ማድረጉ ነው።

ፓርላማው በድርጅታዊ አሰራር የተጠረነፈ ነበር። የሕዝብንና የሀገርን ጥቅም ሳይሆን የሕወሓትን ፍላጎትና ህልም ዳር ለማድረስ ነበር የሚተጋው። ለዚህ ይመቸው ዘንድ የፖለቲካ ፕሮግራሙን አበክሮ ሕገ መንግስት አድርጓልና። አገዛዝ ላይ ለመቆየት እንዲያግዘው በጎሳ ላይ የተመሠረተ ስርዓት አሰፈነ። በአናቱ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሚለውን ሀገራዊ ብሔርተኛ ለማስደንበር የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠል የሚል አንቀጽ በመዶል በአለማችን የመጀመሪያ ሕገ መንግስት ሆነ። በተረፈ ሕወሓት ሕገ መንግስት ያጸደቀው በሕግ ለመግዛት እንጅ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ለማስፈን አልነበረም ። በሕግ መግዛት (Rule by Law) ከሕግ የበላይነት (Rule of Law) በባህርይም በአተገባበርም ይለያያሉ። "በአዲስ ወግ"በተዘጋጀ አንድ መድረክ ላይ "በሕግ መግዛትና የሕግ የበላይነት"በግብርም በባህሪም እንደማይገናኙ በዘርፉ ልሒቃን በደንብ ተደርገው መተንተናቸውን አስታውሳለሁ።

ገዥዎች የራሳቸውን ሥልጣን ለማስከበር ሕግን መጠቀምና ለዜጎች መብቶች፣ ህልውናና ነፃነት እምብዛም ትኩረት አለመስጠት በሕግ የመግዛት ማሳያዎች ናቸው። በአንጻሩ የዜጎችን መብት፣ ነፃነትና ህልውና ማክበር የሕግ የባላይነት መገለጫዎች ናቸው ። የሕግ የበላይነት የዜጎችንና የመንግሥትን ግንኙነት የሚመራ ሥርዓት ነው። የመንግሥት ሥልጣን በሕግ መመራት ፤ ዜጎችም በሕግ መመራት አለባቸው። የሕግ የበላይነት አለ ለማለት ሕግ ግልጽ የሆነ ይዘት ያለው፤ በሕግ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች በሕግ እንደሚፈቱ፤ በሕግ ፊት ሁሉም እኩል መሆኑ፤ የመንግሥት ኃላፊዎች በሕግ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በቅንነት መተግበር፤ ሕግ መሠረታዊ መብቶችንና ነፃነቶችን ማክበር እንደሚጠበቅበት፤ የፍርድ ቤቶችን ነፃነትና ተደራሽነት ማረጋገጠ ፤ ሕጎችን በማስፈጸም ረገድ ወጥነት መኖሩና የፍርድ ቤቶች ሒደት ፍትሐዊ መሆን የሕግ የበላይነት አላባውያን ናቸው።

በሕወሓት የአገዛዝ ዘመን ከእነዚህ የሕግ የበላይነት መሠረታውያን አንዱም ሙሉ በሙሉ ተከብሮ አያውቅም ብል እንደ ድፍረት አይቆጠርብኝ። በዚሁ የአዲስ ወግ መድረክ በተገለጸ መረጃ በዓለም የፍትሕ መድረክ የ2018 ዓ.ም ጥናት መሠረት ኢትዮጵያ ከ186 አገሮች 118ኛ ደረጃን በሕግ ማስከበር የያዘች መሆኗን ፤ በግለሰቦች ነፃነት መመዘኛ ደግሞ ከ162 አገሮች 150ኛ ላይ መሠለፏ ተመልክቷል። ታዲያ ይህ ሕዝብ በእነዚህ ተቋማት ይቅርና በሌሎችስ ዕምነት ቢያጣ ፤ ከፍ ሲልም ሕዝብ ልጁ ቀማኛ አባቱ ዳኛ ብሎ፤ የተቋማቱ አባት በሆነው የሕወሓት አገዛዝ ላይ ዕምነት ቢያጣ ይፈረድበታል ።

በሀገራችንም ዜጎች በኢትዮጵያው ጆሴፍ ጎብልስ(በረከት ስምዖን) ፊታውራሪነት በሚሰለቀው ሀሰተኛ፣ ዘረኛ፣ ከፋፋይ፣ ደረቅ ፕሮፖጋንዳ በመማረር etvን ጨምሮ በሁሉም የመንግስት ብዙኃን መገናኛዎች ላይ እምነት ከማጣት ባሻገር ዕምነቱን እንደ ቪኦኤ ባሉ የውጭ ሚዲያዎችና ማህበራዊ ሚዲያዎች መጣልን መርጦ ነበር። በነገራችን ላይ ዶ/ር ጆሴፍ ጎብልስ የናዚው አዶልፍ ሒትለር የአስገድዶ የማሳመንና የፕሮፖጋንዳ ቀኝ እጅ የነበረ ሲሆን ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል ብሎ የሚያምን ነው። የአሸባሪው ሕወሓት መደበኛና ዲጂታል ወያኔ የፕሮፖጋንዳ አስኳል ይህ የጎብልስ አስተምህሮ ነው። ለ27 አመታት ሲለፈፍ የኖረው ዴሞክራሲና ነጻነት የህልም እንጀራ ሆኖ የቀረው የውሸት ስለነበረ ነው። ሕወሓት/ኢህአዴግ ለብቻው ተወዳድሮ 547 መቀመጫ ሲይዝ ምርጫው ነጻ ፣ ፍትሐዊና ተአማኒ ነበር ብሎ ማህተም በሚመታው በቀድሞው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሕዝበ አዳም ካለማመን አልፎ መሳቂያና መሳለቂያ ቢያደርገው አይደንቅም።

በመግቢያየ ላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ሕገ መንግስቱ ዛሬ የተዋቀረበትን ይዘትና ቅርፅ ይዞ የፀደቀው አንድን ቡድን በስልጣን ላይ ለማስቀመጥ ፣ ለማቆየት፣ የደም ካሳ ለማወራረድ ታስቦበት እንጂ የብሔር ብሔረሰቦችን መብት ለማስከበር አልያም እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለማረጋገጥ ወይም ከቡድን ጥቅም ይልቅ የሀገርን ጥቅም ለማስቀደም አይደለም። የዜጎችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት እኩልነት ለማረጋገጥ እንዳልነበር እነዛ የግፍ 27 አመታት ከየትኛውም ድምፅ በላይ ጮኸ ብለው ይመሰክራሉ።

የአንድን ብሔር መብት ለማስከበር ፣ ነፃ ለማውጣት ጫካ የወረደ ድንገት በለስ ሲቀናው በ180 ዲግሪ የተከረበተ ቤተሰባዊ ወንዜ ቡድን በምን ስሌት ለፌዴራል ስርዓቱ፣ ለብሔር ብሔረሰቦች መብት ተሟጋች እንዲሁም ለሕገ መንግስቱ ጠበቃ፣ ቃፊር ይሆናል ተብሎ ሊታመን ይችላል ! ? ይሄው ቡድን በፊታውራሪነት ራሱ አርቅቆ ያፀደቀውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት መግቢያ PREAMBLE ብቻ በመመልከት እንዴት እንዳሻው ከመጣስ አልፎ ዘወር ብሎ እንኳ ተመልክቶት እንደማያውቅ የአዋጁን በጆሮ ነው። ሆኖም ተቃዋሚዎቹን፣ ተቺዎችን፣ ጦማሪያንን፣ ጋዜጠኞችን፣ ወዘተ . በፈጠራ ክስ በስር ለማማቀቅ ግን አቧራውን አራግፎ ለውንጀላ ይጠቀምበታል። ከዚህ ውጭ የወረቀት ፣ የሕትመት ወጭውን ያህል እንኳ ዋጋ ሰጥቶት አያውቅም ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል።

ከመግቢያው" በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችን ተጠቅመን በነፃ ፍላጎታችን በሕግ የበላይነትና በራሳችን ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመገንባት ቆርጠን በመነሳት። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የግለሰብና የብሔር ብሔረሰብ መሰረታዊ መብቶች መከበራቸው ... "እያለ ይቀጥላል። በእነዚህ አንቀጾች ዋና ዋና ፅንሰ ሀሳቦችን ከተሸከሙ ሀረጋት ሁለቱን ወስደን በቀደሙት 27 አመታት ከተፈፀሙ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር እናመሳክር።

- "ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ":- ሕገ መንግስቱ ከፀደቀ ከ24 አመታት ወዲህ እንኳ በዜጎች ላይ የተፈፀሙ ለመስማት ፣ ለማየት ፣ ለማንበብ ከፍ ሲልም ለማመን እጅግ ስለሚከብዱ ስለሚዘገንኑ ግፎች ፣ ስቃዮች ፣ በደሎች ፣ ወዘተ . ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ባለፉት አራት አመታት ከራሳቸው ከስቃዩ ሰለባዎች፣ ከግፉአን አንደበት ስለሰማን በአይናችን በብረቱ ስለተመለከትን ቁስሉን እንደገና እየነካኩ ፣ እያከኩ ማመርቀዝ አያስፈልግም።

ሆኖም ይህ ሁሉ ግፍ ፣ ስቃይ ፣ ዘግናኝ ወንጀል ሲፈፀም ዛሬ የሕገ መንግስቱ ጠበቃ ሆኖ አይኑን በጥሬ ጨው ታጥቦ ብቅ ያለው እፉኝት ቡድን የዛን ጊዜ የት ነበር !? ይህን አረመኔአዊ ድርጊት በግንባር ቀደምትነት የፈፀሙ ያስፈፀሙ ተጠርጣሪ በላኤ ሰቦችን በመማፀኛ ከተሞቹ በጉያው ደብቆ ስለሕገ መንግስቱ ጥብቅና መቆም አይደለም ትንፍሽ የማለት የቅስም ልዕልና የለውም። ነፃ ዳኝነት፣ ገለልተኛ የደህንነትና የፀጥታ መዋቅር ፣ ነፃ ምርጫ አስፈፃሚ፣ ሕግ አውጭውን፣ ተርጓሚውንና አስፈጻሚውን የሚቆጣጠርበት ሚዛንና መድለው check & balance፣ ወዘተ . እንዳይኖር ሌት ተቀን ሲያሴር ኖሮ "ዋስትና ያለው ዴሞክራሴ "ን እንዴት እውን ሊሆን ይችል ነበር።

"የራስን እድል በራስ የመወሰን..." መብት በአለማችን በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ብቻ ተደንግጎ እንደሚገኝ የሚነገርለት ይህ አወዛጋቢ አንቀፅ ለላንቲካ፣ ከፍ ሲልም ለማስፈራሪያ፣ ለማንገራገሪያ ተቀመጠ እንጂ ፅንሰ ሀሳቡ ከተሸከመው ተዝቆ የማያልቅ "መብት "ዝቅተኛውን ማለትም ሕዝብ በልጆቹ የመተዳደር መብትን እንኳን አላረጋገጠም። ከትግራይ ክልል በስተቀር ሁሉም ክልል በሞግዚት ይተዳደሩ እንደነበር ፀሐይ የሞቀው ሀቅ ነው። በአንዳንድ ክልሎች የፌዴራል መንግስት በቀጥታ የሰየማቸው ባለ አደራዎች ከፌዴራል ትዕዛዝ እየተቀበሉ ይፈልጡ ይቀቆርጡ ነበር። ሌሎቹ በአማካሪ ስም የተመደቡላቸውን ነጭ ለባሾችን ቀጭን ትዕዛዝ ይፈፅሙ ነበር። ይህ አልበቃ ብሎ የየክልሉ ርዕሰ መስተዳድሮች ለዚህ አሻንጉሊታዊ ሹመት ያለ ደህንነቱ እና ያለ ጠቅላዩ ይሁንታ አይታጩም ነበር።

## እንደ መውጫ

ከለውጡ በፊት ሕዝብ በአገዛዙ ላይም ሆነ በተቋማቱ ላይ ምንም አይነት እምነት አልነበረውም። ይህ ማለት እምነቱን ወደ ሌላ አካል አስተላልፎ (Trust displacement)ነበር ማለት ነው። ከኢቲቪ ወደ ቪኦኤና ማህበራዊ ሚዲያው እምነቱን እንዳሸጋሸገው ሁሉ ሌሎች ተቋማትንም እንዲህ አሸጋሽጎ ነበር። በለውጡ ዋዜማ እምነቱን ወደ ፋኖ ፣ ቄሮና ቃሬ ወስዶ እንደነበረው። በአንጻሩ ከለውጡ ወዲህ በመንግስትም ሆነ በተቋማቱ ዕምነት ማሳደር ተጀምሯል። እንደ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ያሉ ተቋማትን በመገንባት የዜጋውን ዕምነት በመመለስ ላይ ነው። ሌሎች ተቋማትም እየተገነቡ ነው ። ያው የተቋማት ግንባታ በአንድ ጀምበር አይጠናቀቅምና ጊዜ ይጠይቃል። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ሰሞኑን በፓርላማው ትኩረት ሰጥተው ካነሷቸው የመንግስት ተግባራት የተቋማት ግንባታ ቀዳሚ መሆኑን አረጋግጠዋል። ይህ የሕዝብ አመኔታን በሒደት ይመልሳል። መተማመን ከሌለ አይደለም ሀገር ቤተሰብ በቅጡ አይመሠረትም ! ።

# ወቅታዊ

# ‹‹ኢትዮጵያ አልፈረሰችም ብቻ ሳይሆን የብልጽግና መሰረቷን እየጣለች ነው ››

*- ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር*



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ከትናንት በስቲያ በተወካዮች ምክር ቤት በመገኘት የምክር ቤት አባላቱ በወቅታዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ላቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል። በዛሬም እትማችን "ለውጡና አገራዊ ሪፎርሙ በሀዲዱ እየሄደ ነው ወይስ ሀዲዱን ስቶ ከመስመር ወጥቷል? ወይም አንዳንዶች እንደሚገልፁት ከሽፏል ወይ?" የሚለውን ጨምሮ በመንገድ ግንባታዎች ዙሪያ ለተነሱ ጥያቄ የሰጡትን ሰፊና ዝርዝር ምላሽ ይዘን ቀርበናል፦

**የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ምላሽ፦**

በመጀመሪያ የተከበረው ምክር ቤት ከግምት ሊያስገባና የእይታ መነጽሩን ሊያስተካክል የሚገባው ባለፉት አራት ዓመታት ቀደም ሲል ከነበረው ጊዜ በተለየ ሁኔታ የገጠሙንን ከበድ ከበድ ያሉ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ፈተናዎች መልሶ ማስታወስ ያስፈልጋል:: እነዚህን ፈተናዎች በደንብ ካልተረዳን አውዱ ይበላሻል:: እንዲህ ብለው ነበር፤ እንዲህ አልሆነም፤ ለማለት እነዚያን ሁኔታዎች በትክክል መገንዘብ ጠቃሚ ይመስለኛል:: ለምሳሌ ከሪፎርም በፊት ኮሮና አልነበረም:: ኮሮና እንደሚመጣ አጋጣሚ ሆኖ ጠንቋይ ስለማንቀልብና እኛም ስለማናውቅ ምን ሊመጣ እንደሚችል መገመት እኛም ዓለምም ልናውቅ አንችልም::

ኮሮና የሚያስከትላቸው ኢኮኖሚክ እና ሌሎች አስጊ ሁኔታዎችን እንዴት እንደምንወጣ ተለምዷዊ በሆነ መንገድ እቅዳችንን እንከልሳለን እንጂ ቀድመን የምናውቀው ጉዳይ አልነበረም:: አንበጣ፣ ጎርፍና ድርቅ ነበር:: እነዚህ የተፈጥሮ ተግዳሮቶች እቅዶቻችንን ለመከለስ፤ የአሰራር ስርዓታችንን ለመፈተሽ እንዲሁም ያቀድናቸውን ነገሮች ለማሳካት የራሳቸው የሆነ እንቅፋት ይሆናሉ:: ከእነዚህ በተጨማሪም ቀደም ሲል ያልነበሩ ሰው ሰራሽ ችግሮች አጋጥመዋል:: አንደኛ ውጊያ ነው:: በአገር ውስጥ የገጠመን ውጊያ እጅግ ከፍተኛ የሰብዓዊ እና የኢኮኖሚ ቀውስ ያስከተለ ነው:: አገር ለማፍረስ ታቅዶ የተሰራ፤ የተጀመረ ውጊያ ነው:: ለማክሸፍ የነበረው ሂደት ቀላል አይደለም::

የአገራችን ውጊያ ረገብ ብሎ አሁን ደግሞ ልማታችንን እንሰራለን ስንል የዩክሬን ውጊያ ደግሞ አጋጠመን። እንደማንኛውም ዓለም የዩክሬንና የራሽያ ግጭትም በእኛ ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው ጫና አለ፤ የአገር ውስጡን ጨርሰን እፎይ ሳንል የውጭው መምጣቱንም በአግባቡ ማየት ጠቃሚ ይሆናል:: መፈናቀል፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ ያልተገባ የውጭ ጫና በዚህ ውስጥ ሊታይ የሚገባው ነው:: የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የገጠሙንን በደንብ ማስተዋል እና ማስታወስ ስንችል ከእቅዶቻችን ምን ያህል አሳካን፤ ምን ያህል አላሳካንም፤ የገጠሙን ፈተናዎች እንዴት አለፍናቸው የሚለውን ለማየት ያግዛል::

እንግዲህ ውጊያ ገጠመን ሲባል ዝም ብሎ ተራ ግጭት አይደለም:: ህዝብ ሊያናክሱ፣ አገር ሊያፈርሱ በይፋ ተናግረው አውጀው የተነሱ ኃይሎች ናቸው የገጠሙን:: ህዝብ አታናክሱ፤ አገር አታፍረሱ የሚለው የመከላከል ውጊያ እንዲሁ አንዳንዶች በቀላሉ እንደሚያነሱት የሚታይ ሳይሆን አገርን ከማፍረስ የታደገ ዘመቻ ነበር:: ኢትዮጵያ አበቃላት የሚለውን በርካቶች በተናገሩት አፋቸው ነገር ተቀልብሷል እንዲሉ ማድረግ ያስቻለ ሁኔታ ነው::

የእነዚህ ሰዎች ዓላማ ኢትዮጵያ የሚባለው የከበረ ስም ታሪክ ማድረግ ነው:: ይህ ስም ከነክብሩ እንዳይዘልቅ የማድረግ ፍላጎት ነበራቸው:: ይህንን ስም ለማጥፋት አስፈላጊውን መስዋዕትነት እንከፍላለን ብለው በግልጽ ያወጁ ኃይሎች ናቸው:: ከእነዚህ ጋር የገጠምነው ጦርነት ኢትዮጵያ አትፈርስም ነው አልፈረሰችም? ኢትዮጵያ አልፈረሰችም ብቻ ሳይሆን የብልጽግና መሰረቷን እየጣለች ነው ያለችው:: ይህን ደግሞ የተከበረው ምክር ቤት በቅርቡ በነበረው ጉብኝት በርካታዎቹን ነገሮች ስላየ እኔም ደጋግሜ አነሳቸዋለሁ::

እነዚህ ሁሉ ፈተናዎችና ችግሮች ያጋጠሙን ደግሞ በወጉ ሳንደራጅ ነው:: ተቋም ሳንፈጥር፣ ከላይ እስከታች እንደመንግስት ሳንቆም የገጠመን ችግር ነው:: ተመሳሳይ ችግር ነገ ቢገጥመን የምንወጣበት መንገድ ከትናትናው ይለያል:: ዛሬ የተሻለ ቁመና ስላለን በተሻለ መንገድ እንወጣዋለን:: ከዚህ ቀደም ግን ችግሩ ሲገጥመን እንደመንግስት ሳንደረጅ፤ እንደፓርቲ ሳንደረጅ የነበረበት ሁኔታ ተግዳሮቱን ለመጋፈጥ የሚጠይቀው ዋጋ በዛው ልክ ከበድ ያለ ያደርገዋል::

ነገር ግን ይህ ችግር የራሱ የሆነ ስጋት ብቻ ሳይሆን እድልም አለው:: እድሉንም ስጋቱንም፤ መከራውንም ልማቱንም፤ ጥፋቱንም በሚዛን ማየት ስንችል የተሟላ ግንዛቤ እንይዛለን:: ኮሮና ስለመጣ ሁሉን ያጠፋ ብቻ ሳይሆን መሬት ጦም አይደር ብለን እንድንዘምት ደግሞ በር ከፍቷል:: ኮሮና መጥቶ መሬት ጦም አይደር ባንል ኖሮ ዛሬ የዩክሬን ውጊያ ላይ አፍሪካ በስንዴ ምክንያት እየደረሰበት ያለው መከራ እኛ ስለኤክስፖርት ቀርቶ ከዚ በመለስ ባለው ጉዳይ ላይ ለመነጋገር እንቸገር ነበር:: እያንዳንዱ መከራ የራሱ የሆነ እድል ይዞ ይመጣል:: ያንን እድል በምን ያህል ልክ እንጠቀምበታለን የሚለው ጉዳይ ከብዙ አገራት ትምህርት መውሰድ ያስፈልጋል::

ተደራራቢ ፈተናዎች የገጠማቸው አገራት፤ የተደራረቡ ችግሮች የገጠሟቸው አገራት፤ እንደ አገር የፈረሱ አገራት በአጠረ ጊዜ ውስጥ ራሳቸውን አደራጅተው እንዴት ቆሙ ነው:: ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ጀርመን ፈርሳ እንዴት ራሷን አደራጅታ በአውሮፓ ትልቁን ኢኮኖሚ መገንባት ቻለች? በኤዥያ ጃፓን በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ፈርሳ በአጠረ ጊዜ ውስጥ ራሷን አደራጅታ እንዴት በኤዥያ ከዓለም ከፍተኛ ኢኮኖሚ ካላቸው አገራት ተርታ መመደብ ቻለች? በሲቪል ጦርነት ኮሪያ ከፈረሰች በኋላ በአጠረ ጊዜ ውስጥ ራሷን ለመቻል እና ለመርዳት የሚያችል የኢኮኖሚ አቅም እንዴት ገነባች? መከራ አገራን የሚያጠፋ ብቻ ከሆነ እነዚህ አገራት ከችግር ውስጥ ወጥተው ራሳቸውን የቻሉበት መንገድ ያንን እሳቤ ይቃረናል::

ሩሲያ እንኳ ብንወስድ የዛሬ 30 ዓመት ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ሩሲያ ተንኮታኮተች የሚባልበት ዘመን ደርሶ ባለፉት 30 ዓመታት ራሷን አደራጅታ አሁን ላለችበት ቁመና ደርሳለች:: የገጠመን ፈተና፤ የገጠመን ችግር /በተፈጥሮም ይሁን በሰው ሰራሽ፤ በውስጡ ያመጣውን እድል መጠቀም ከቻልን፣ በትጋት መስራት ከቻልን ኢትዮጵያን አስተማማኝ መሰረት ላይ ማስቀመጥ የሚችል እድል ሊያመጣ እንደሚችል አይተናል፤ ተምረናል፤ ያለውም እውነታ እሱን ነው የሚያሳየው:: ስለዚህ መከራውንም ችግሩንም በአውዱ ማየትና በዛ መነጽር መገንዘብና መረዳት በእጅጉ ያግዛል::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሪፎርሙን በሚመለከት ሪፎርሙ ተቀልብሷል ወይ? አለ ወይ? የለም ወይ? የሚል ጥያቄ ተነስቷል፤ ሪፎርሙ፣ መነሻ ያደረጋቸው እሳቤዎች እና ሐሳቦች በደንብ ካልተገነዘብንና በዚያው መመዘኛ መሰረት መገምገም ካልቻልን የተዛባ ድምዳሜ ላይ ያደርሰናል:: በኢትዮጵያ ብዙዎች አንድ የሚያግባባቸው ሞቶ አለ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታ ቦታ "It's My Dam" እየተባለ ይነገራል:: It's My Dam> የተባለው ከህዳሴ ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ቢሆንም ለእኛ ሪፎርም ግን አጋዥ በሆነ መንገድ እና ሰዎች በቀላሉ እንዲያስታውሱት እኛ ደግሞ ‹My>ን አጥፍተን ‹Its Dam> በሚል ምህጻረ ቃል ያሰርነውን ሪፎርም ነው የምናካሂደው::

It's Dam> የሚለውን ነገር በቀለለ መንገድ ስንገነዘብ ከዚያ ተነስተን ሪፎርሙ ምን ላይ እንዳለና እንዴት እየተሳካ እንደሆነ ምን ችግሮች እንዳሉበት፤ ምን ሊታረም እንደሚገባው ከውስጡ በቀላሉ ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል::

‹It's Dam> የሚለው የመጀመሪያው ‹I› የሚለው ‹Idea› ሐሳብ ነው:: የሐሳብ ድህነት በጣም አስቸጋሪ ነገር ነው:: ሰዎችን ይንጣል፤ ባለተስተካከለ ጎዳና እንዲጓዙ ያደርጋል:: ምክንያቱም ሐሳብ የመገንባት የማፍረስ አቅም አለው:: አገር የሚገነባውም የሚፈርሰውም ጭንቅላት ውስጥ ነው:: የፈረሰ ጭንቅላት አገር ሊገነባ አይችልም:: የተገነባ ጭንቅላት አገር ሊያፈርስ አይችልም:: ሐሳብ ይገነባል፤ ሐሳብ ያፈርሳል፡ ግልጽነት ያለው እሳቤ ካልያዝን በስተቀር በዚያ ላይ የሚመሰረተው የልማት እንቅስቃሴ ዘላቂ ሊሆን አይችልም::

ሐሳብ ሰው ይገነባል:: ሰው ተቋም ይገነባል:: ተቋም አገር ይገነባል:: ያልተገነባ ሰው ተቋም አይገነባም:: ያልተገነባ ተቋም አገር አይገነባም:: የነገር ሁሉ መሰረት ሐሳብ ነው:: ምክንያቱም ሐሳብ ዘር ነው:: ሐሳብ ዘር ስለሆነ፤ ሰው ዛፍ ነው:: ተቋም ጫካ ነው:: አገር የጫካዎች ድምር ናት:: አገር የሚባለውን ትልቅ የጫካዎች ድምር ስናወራ ዘር የሆነውን ሐሳብ፤ ዛፍ የሆነውን ሰው፤ ጫካ የሆነውን ተቋም በየቦታው በትክክል ማየት ካቻልን አገር ፈርሳ፣ አገር ተገንብታ፣ አገር ወድቃ፣ አገር ተነስታ የሚለው ቋንቋ፣ ቋንቋ ብቻ ነው የሚሆነው::

የነገር ሁሉ ዘርና መሰረት ሐሳብ ነው:: ሐሳብን በዚህ ደረጃ የምናከብርና ዋጋውን የምንገነዘብ ደግሞ ከሆንን እኛ ዘር የማናመክን መሆን አለብን:: ዘር የማያመክነው አርሶ አደር ያንን ዘር ዘርቶ ፍሬያማ ይሆናል:: ዘር የማናመክን፣ ዛፍ የማንቆርጥ፣ ጫካ የማንመነጥር ከሆን፤ ሐሳብ አይመክንም፤ ሰው አይመክንም:: ተቋም እንደ ተቋም ደግሞ የፈረሰና ከፖለቲካ ጋር የሚሄድ የሚመጣ አይሆንም:: ዘር፣ ዛፍና ጫካ በመሰረቱ እየገነባን የምሄድበትን መንገድ ከፈጠርን ግን ፓርቲ ቢሄድ ፓርቲ ቢመጣ እንደ አገር ስጋት አይገባንም::

ከሰሞኑን የጎበኛችሁት ተቋም የሚያሳዩት የሐሳብ ዘር በየተቋማቱ እንደተዘራ፣ ሰው የሚባለው ዛፍ በየተቋሙ እየተፈጠረ መሆኑን፣ ይህ ዛፍ ተደምሮ ደግሞ ጫካ የተሰኘው ተቋም እየገነባን መሆኑን ጅማሮ ነው:: ይህንን አሰናስለን አገር ልናቆም፤ አገር ልናስቀጥል የሚያስችል መሰረታዊ ስራ እየሰራን መሆኑን ያመላክታል::

ይህ ባይሆንስ? ሐሳብ ዋጋ እንዳለው ባንገነዘብስ? ሐሳብ ዘር መሆኑን፤ መሰረት መሆኑን ባንገነዘብስ ያ ደግሞ ወፍ ዘራሽ አረም ይሆናል:: ጫካው ተቋሙ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

አገሩ ወፍ ዘራሽ ይሆናል፤ ወይም በረሃ ይሆናል፤ የተመነጠረ ይሆናል:: በሐሳብ ላይ ስንግባባና ሐሳብ ስናደራጅ ቅድም እንደጠቀስኳቸው ሳንቸገር ወደሚቀጥለው ደረጃ ለመጓዝ እድል እናገኛለን:: እስካሁን የተናገርኩት ሐሳብ የሚለውን ነው::

ቀጥሎ ደግሞ <Time> የሚለውን ‹ጊዜ› ነው:: ጊዜ የሚሰጥ ውድ ሀብት ነው:: ጊዜ ይሰጥሃል እንጂ አትገዛውም:: የተሰጠህን ጊዜ ተገንዝበህ መጠቀም ካልቻልክ ጸጸት ታተርፋለህ፤ ጸጸት ትወልዳለህ:: በተሰጠው ጊዜ የማይጠቀም ሰው ትርፉ ጸጸት ነው:: ጊዜ ሲባል ወደመንግስት፣ ወደ ፓርላማ እንዲሁም ወደሚዲያ እጅ የሚቀሰርበት ሳይሆን እያንዳንዱ ሰው የጊዜን ዋጋንና ምንነት እንዲሁም አጠቃቀም በቀለለ መንገድ መገንዘብ አለበት::

ለምሳሌ እዚህ ያላችሁ የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት በቸርነትና በደግነት ሰጪው ዘጠና ዓመት የተባ ጊዜ ለእያንዳንዳችሁ ቢሰጣችሁ፤ ከዚህ ውስጥ 30 ዓመት በእንቅልፍ ነው የሚያልቀው:: በቀን ውስጥ ስምንት ሰዓት ትተኛላችሁ፤ ስለዚህ 30 ዓመቱ በእንቅልፍ ያልቃል ማለት ነው:: ስለዚህ 60 ዓመት ቀረ:: 30ው ዓመት በእንቅልፍ ስለሄደ ቢሰጥም ባይሰጥም የእንቅልፍ አካል ተደርጎ የሚታይ ነው:: የምንነጋገረው በ60ው ብቻ ይሆናል:: ከ60 ዓመቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ሁኔታ አሁን እንደእናንተ ተምሮ ተመርቆ ፓርላማ የመጣ ሰው ቢያንስ ቢያንስ ኮሌጅ እስኪገባ 20 ዓመት በእናት በአባቱ ጫንቃ ላይ የሚቀመጥ ነው:: 20 ዓመት ስራ አይሰራም:: ሃይስኩል ጨርሶ ኮሌጅ እስኪገባ ድረስ ማለት ነው::

ግን ምናልባት ኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከደረሱ በኋላ ቤተሰቦቻቸውን ያግዛሉ፤ ውሃ ይቀዳሉ፤ በእርሻ ይተባበራሉ:: 20 ከምናደርገው 15 ዓመት እናድርገው:: 15ቱን ዓመት በእናት በአባቱ ጫንቃ ላይ ይቀመጣሉ:: ከዚያ በኋላ ነው ስራ የሚጀምረው ብንል ከ60ው 15ቱን ቀንሱ:: 45 ቀረ:: በኢትዮጵያ ህግ መሰረት ሰው ከ55 እስከ 60 ዓመት ጡረታ ይወጣል:: ነገር ግን በ60 ብንወጣም አንድ አምስት ዓመት ሰው ካለበት የስራ መስክ ከወጣ በኋላ ይፍጨረጨራል፤ ይሠራል ብለን እስከ 65 እንግፋው:: ከታች አምስት ገፍቻለሁ:: ከላይም አምስት ጨምሪያለሁ/ ደግ ለመሆን እንጂ ያን ያህል የሚሠራ አለ ማለት አይደለም/ ::

በ65 ዓመቱ ጡረታ ይወጣል ብለን ብናስብ ከ65 እስከ 90 ለ25 ዓመታት የጡረታ ጊዜ ነው:: 25 ጡረታ፤ 30 እንቅልፍ፤ 15 አልሰራህም ቢባል ያለህ የሥራ ጊዜ 20 ዓመት ነው:: ከ90 ነው:: ከ20 ዓመት ደግሞ ቅዳሜ እና እሁድ፣ የሻይ እረፍት፣ የምሳ ዕረፍት ጨምሩበት፤ ሰው ከተወለደ ጀምሮ እስከሚያርፍበት ቀን ድረስ ለመብላት ሳይታክት፤ ከተወለደ ጀምሮ እስከሚያርፍበት ቀን ድረስ ለመተኛት ሳይታክት 10 እና 15 ዓመት በወጉ ሳይሠራ የተዝናና ሕይወት ሊኖረው አይችልም::

ማንም ሰው የተዝናና ሕይወትን የሚፈልግ ከሆነ መትጋት ግዴታው እንደሆነ ማወቅ አለበት:: ለምን? ውስን ጊዜ ነው:: ለምሳሌ እኔ እና እናንተ ያለን የሥራ ጊዜ ከአሁን በኋላ ቢበዛ 15 ወይም 10 ዓመት ገደማ ነው:: ባንጠቀመው ሰጪው ይወስደዋል:: ብዙ ሰው 20 ዓመት ቤተሰቡ ላይ ተቀምጦ፤ ከዛ ደግሞ በሻይ እረፍት ብዙ ጊዜን አሳልፎ ጡረታው ሲደርስ መብላቱን መቀጠል ይፈልጋል:: ነገር ግን አይቻልም:: መብላት መቀጠል የሚያስብ ሰው ያቺን ጊዜ በአግባቡ መጠቀም አለበት:: ለምን ክረምት በጋ አይሆንም ጨለማም ብርሃን አይሆንም:: ይህ የተፈጥሮ ሕግ ነው::

የተሰጠንን ጊዜ አውቀን ጠዋትና ማታ ክረምት እና በጋ እንደማይቀላቀሉ ሁሉም ነገር በወቅት በጊዜው እንደሚሆን ተረድተን ካልተጠቀምን በስተቀር ጊዜ ባለቤት አለው:: ነገ ይደርሳል ብለህ ብትተወው አታገኘውም:: ጊዜ እንደኪራይ ቤቶች ነው:: የፓርላማ አባል ስትሆኑ ኪራይ ቤቶች ቤት ሠጥቷችኋል:: ልክ አምስት ዓመት አገልግላችሁ የማትቀጥሉ ከሆነ ኪራይ ቤቶች በል ቤቱን ልቀቅ ይላል:: ጊዜ እንደእርሱ ነው:: ይሰጥሃል፤ ትኖርበታለህ:: ሲያልቅ ይወሰድብሃል:: ሌብነቱን፣ ውጤቱን ፣ ፕሮጀክቱን ሁሉንም ከጊዜ አንፃር ማየት ነው:: እያንዳንዱ ሰው የተሰጠችውን ውስን ጊዜ ምን ያህል እየተጠቀምኩበት ነው ብሎ ማየት እና ማሰብ መቻል አለበት::

ከጊዜ ባልተናነሰ ሶስተኛው ሃሳብ ቦታ ነው:: ብዙ ጊዜ ሰዎች ለጊዜ ከበድ ያለ ቦታ ሰጥተው ለቦታ ዝቅ ያለ ቦታ ይሰጣሉ:: ሰው ግን የጊዜ ብቻ ሳይሆን የቦታ እስረኛ ነው:: ሰውን ከቦታ ውጭ ነጥሎ ማየት አይቻልም:: ሁሉ ነገር የሰው እንቅስቃሴ በቦታ ውስጥ ያለ ነው:: ለምሳሌ አልጋ ሰው የሚተኛበት ቦታ ነው:: ቤት ሰው የሚኖርበት ቦታ ነው:: ትምህርት ቤት ሰው የሚማርበት ቦታ ነው:: ቤተክርስቲያን መስጂድ ሰው የሚያመልክበት ቦታ ነው:: መንገድ ሰው የሚጓዝበት ቦታ ነው:: የእርሻ ማሳ ሰው የሚጓዝበት ቦታ ነው:: ሁሉ ቀርቶ ሰው ሲያልፍ ሲቀበር የሚያርፍበትም ቦታ ነው:: ሁሉም ነገር ቦታ ነው::

ቦታን በወጉ የሚረዳ፣ የሚያይ እና የሚጠቀም ሰው ይለማል፤ ይበለጽጋል አይለምንም:: ቦታን በወጉ መጠቀም የማይችል ሰው ግን ይደኸያል:: ለምሳሌ የበጋ ስንዴ ሲባል እያንዳንዱ ዜጋ መገንዘብ ያለበት በበጋ ወቅት የረሳነውን መሬት መጠቀም ማለት ነው:: ክረምት አርሰን በጋ የጣልነው ቦታ፤ አይ በጋም ጥቅም ላይ መዋል አለበት ብሎ መጠቀም መቻል ማለት ነው:: ጊዜውም ቦታውም ያለውን ጉድኝት ማየት ይጠቅማል::

እኛ ስለቦታ <Space> (ስፔስ) ያለን ግንዛቤ እጅግ ያነሰ በመሆኑ በርካታ ነገር መቀየር ስንችል በማይቸግረን ቦታ ራሳችን ተይዘን ታስረን መርዳት የሚችል አገርን ለማኝ አድርገናል:: ይህ ደግሞ የሆነው ሰው ከራሱ ነው የሚጀምረው:: የጊዜ እና የቦታ እይታውን መገንዘብ የሚችለው ከራሱ ነው:: አንድ ሰው ብብቱን የማያፀዳ ፣ ጥርሱን የማያፀዳ ፣ ጫማውን የማያፀዳ ከሆነ ስለቤቱ አታውራ፤ ቤቱን ያፀዳል ብለህ አታስብ:: እላዩ ላይ ያለውን ቦታ ያልጠበቀ፤ የከበረ ማንነት በትክክል ያልጠበቀ ሰው ቤቱን አይጠብቅም፡ መጀመሪያ ጥርስ ማፅዳት፣ ጫማ ማፅዳት፤ ያ ግንዛቤ ያለው ሰው ቤቱን እንደሚያፀዳ መገመት ይቻላል:: ይሔ በግለሰብ ደረጃ ነው:: ቤተሰብስ የምግብ ማብሰያ ክፍሉን (ኩሽናውን) ካላፀዳ፣ መጸዳጃ ቤት ካላፀዳ፣ ጓሮውን ካላፀዳ እና ካልተጠቀመ አንድ ቤተሰብ ከተማውን ያፀዳል የሚባለው በየት በኩል ነው ?

አንድ ሰው ላዩ ላይ ያለውን ሳያፀዳ ቤቱን አያፀዳም:: አምስት አስር ሰው የሚኖርበት አንድ ቤተሰብ በጋራ የሚጠቀምበትን ኩሽና ካላፀዳ፤ ከተማውን አያፀዳም:: አንድ መንደርተኛ፣ አንድ ጎረቤት ደግሞ ሰፈሩን በትክክል ካላፀዳ እና ካልተጠቀመ አገሩን ሊያለማ አይችልም:: አገሩንም አያውቅም:: ከእናንተ መካከል ኢትዮጵያን ከጫፍ ጫፍ የሚያውቅ ስንት ሰው አለ? አምስት ሰው የለም:: አገራችንን በወጉ አናውቅም:: ሰው ሰፈሩን ሳያፀዳ፤ ሰፈሩን ሳያስተካክል አገሩን ያፀዳል ማለት ዘበት ነው:: ቤተሰብ በቤቱ በጋራ የሚጠቀምበትን ሳያፀዳ፤ ከባቢ ሳይጠቀም ከተማውን ያፀዳል ማለት ዘበት ነው::

ቦታ ላይ ያለን ግንዛቤ ልክ እንደጊዜው ግልጥ ያለና ያልታወቀ ከሆነ ልማት ችግር ነው:: ለዚህ ነው፤ በርካታ ኢትዮጵያውያን አዲስ አበባ የጠበበን:: ሶፍ-ዑመር የተረሳው፤ ላልይበላ ያረጀው፤ ኮያሻ የተዘነጋው፤ ስለቦታ ያለን ግምት እጅግ አነስተኛ ስለሆነ ነው:: አይገባንም ስፔስ፤ በቅርቡ እዚሁ አዲስ አበባ አካባቢ ለአንዳንድ ጉዳይ ቦታ ስናፈላልግ፤ የሆነ የሚገርም ቦታ አየን፤ ቦታው መኪና አይገባበትም:: የምንሔደው በእግር ነበር:: እኔም አብረውኝ የነበሩት ሰዎችም ደነገጥን::

እንደዚያ ያለ ከፍታ፤ እንደዛ ያለ የሚያምር ቦታ፤ አዲሰ አበባን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ፤ ልክ እኔ እንደማያችሁ ከተማዋን የሚያሳይ ቦታ በዚህ ከባቢ አለ ብለን አስበን አናውቅም:: ስለእንጦጦ እያወራሁ አይደለም:: ለማንኛውም ይህ ቦታ ብዙዎች ሊዝናኑበት የሚችሉበት በጣም በጣም ምርጥ እይታ (ቪው) ያለው በመሆኑ ኮብልስቶን ሰርተን እያዘጋጀነው ነው:: አረንጓዴ ልማት



የምንጀምረው እዛ ስለሆነ በሚቀጥለው ሳምንት ታዩታላችሁ:: ለምን ይህንን ቦታ አላየንም:: ምናልባት እኛ ትንሽ ራቅ ያልን እንሆናለን ብለን ለከተማው ቀረብ ያሉ ሰዎችን ይዘናቸው ሔድን፤ ያውቁት እንደሆን ብለን ነበር፤ አያውቁትም::

ለቦታ፣ ለጊዜ እና ለሐሳብ ያለን ግምት እጅግ ውስን ስለሆነ እንደተባለው ነው:: ችግር ስንተነትን እንኖራለን:: መፍትሔ የሚባል ነገር የለም:: ኢትስ ‹It's› ያልነው አይዲያ፤ ታይም እና ስፔስ ነው:: ዳም <Dam> ያልነው ዲውቲ እና ሞራል ነው:: ሥራ ሲባል መድከም አይደለም:: ስምንት ሰዓት ቢሮ ቆይቼ መጣሁ ደከመኝ አይደለም:: ከሥራህ ፍሬ ማፍራት አለብህ:: ውጤት ማምጣት አለብህ:: ከጀመርክ መጨረስ አለብህ:: ህዳሴን ጀምሪያለሁ፤ ስኳርን ጀምሪያለሁ ሳይሆን ማለቅ አለበት:: መጀመርና መጨረስ መድከም እና ፍሬ ማፍራት ማለት ነው::

ለምን የሚሠራ ሰው አይለምንም:: ያካፍላል:: በሥራ እንደሚጠቀም እንደሚያገኝ የሚያውቅ ሰው አርሶ አደርም ቢሆን ከማሳው ያካፍላል፤ እንጂ አይለምንም:: የሚሠራ ሰው አያባክንም፤ ዝም ብሎ አይረጭም፤ እንዴት ደክሞ እንዳመጣው ስለሚያውቅ ይቆጥባል:: አያባክንም:: የሚሠራ ሰው የዕጦት ጭንቅላት የለውም:: በሥራ ውስጥ ፈጣሪ ስለሆነ፤ የተትረፈረፈ ሃሳብ ነው ያለው:: የማካፈል ሐሳብ ነው ያለው:: የመስጠት የማጋራት ሐሳብ ነው ያለው:: በዚህ ሐሳብ የተነሳ በሰላም መኖር ይችላል::

ሥራ እንደኛ በድህነት ላሉ እና ልመናን ለተለማመዱ አገራት እጅግ ወሳኝ ነገር ነው:: ከሥራ አንፃር ሁላችንም መገንዘብ ያለብን ምድር ለሚሠራ ሰው ክብርን፣ ለሚያወራ ሰው ችግርን፤ ለሚበላ ሰው መቃብርን አትነፍግም:: ከበላህ የሆነ ጊዜ ስትሞት ትሰጥሃለች፤ ቦታ አትከለክልህም፤ አትነፍግህም:: ምድር ደግ ናት:: ካወራህም ችግርን ታስታቅፍሃለች:: በወሬ ችግር እንጂ ውጤት ስለማይመጣ::

ዓለም ከሠራህ ታከብርሃለች:: የሚሠሩ ሰዎች ጠዋት ቢወቀሱ፤ ጠዋት ቢነቀፉ፤ ማታ ሞገስ እና ክብር ይጠብቃቸዋል:: ስትሠራ አሁን ያለውን ጫጫታ ሳይሆን፤ ነገ የሚመጣውን ክብር እያሰብክ መሆን አለበት:: የጠዋት ወቀሳ የማታ ሞገስ እና ክብር ስለሚያመጣ:: እስኪ እኛ አገር ኢትዮጵያ ውስጥ የማይሠራ አይብላ ቢባል፤ ከ100 ሚሊዮን ስንት ሰው ይበላል ብላችሁ ታስባላችሁ?

የማይሠራ ሰው አይብላ ብላችሁ አዋጅ ብታወጡ፤ ህግ ብታወጡ፤ ይህ ትንሽ ይከብዳል:: እናንተንም ምናልባት ላይምር ስለሚችል፤ የማይሠራ አይብላ የሚለው ይቅርና ተግቶ የማይሠራ ሰው አርባ ጅራፍ ይገረፍ፤ ቢባል ከዚህ ውስጥ ስንት ሰው ሳይገረፍ ይወጣል የሚለው ነው ጥያቄው:: ሕግ አውጥታችሁ በቃ ካልሰራህ አትብላ፤ እርሱም ከባድ ስለሆነ ግዴለም ትንሽ ትንሽ ቅመስ፤ ግን አርባ ጅራፍ ትገረፋለህ ብትሉ፤ ከ100 ሚሊዮን ስንት ሰው እንደሚተርፍ እናንተው አስቡበት::

ወገኖቼ መስራት አለብን:: በሥራ ብቻ ነው ለውጥ የሚመጣው:: እኛ የምንሰራው ሰባት ቀን ነው:: እኛ የምንሰራው ሶስት እና አራት ሰዓት እየተኛን ነው የምንሰራው:: ለምን? ውጤት ፍሬ ስለምንፈልግ ነው:: ቅድም አንድ ወንድሜ በመግቢያ ንግግሩ ያነሱትን ጉዳይ በኋላ እመጣበታለሁ:: በጣም የረሳኋቸውን ቁም ነገሮች ስላስታወሱኝ፤ ለምሳሌ ‹‹የወሰን ጉዳይ ይመለሳል ብለው ነበር::›› አሉ:: እንዴት እንደረሱ አላውቅም:: ሲዳማ እንዴት በሰላማዊ መንገድ የራሱን ክልል እንዳወጀ፤ እንዴት ምዕራብ በሰላማዊ መንገድ የራሱን ክልል እንዳወጀ እንዴት ማስታወስ እንዳልቻሉ አልገባኝም:: እሱ ማለት እኮ ነው:: የወሰን ጉዳይ ሲባል የሕዝቦች ጥያቄ ህጋዊ በሆነና በሰላማዊ መንገድ በሕዝቦች ድምፅ ምላሽ መስጠት መቻል ማለት ነው::

የመጨረሻው ሞራል ነው:: አይዲያ፣ ታይም እና ስፔስ (ኢትስ) ያልኳችሁ ይህንን ነው:: በመጨረሻ ሞራል ነው:: በተለይ ሌብነት፤ የተከበሩ የምክር ቤት አባል ከንብረት ጋር ተያይዞ ጥያቄ አንስተዋል:: ሌብነት ቅድም ያነሳኋቸውን ነገሮች ሁሉ የሚያፈርስ ካንሰር ነው:: ነቀርሳ ነው:: የሚሰርቅ ሰው ስለጊዜ፣ ስለስፔስ እና ስለአይዲያ ቢገባውም ባይገባውም ዋጋ የለውም:: ሰራቂ ማለት አጉዳይ ማለት ነው:: ግን የኛ ሌብነት መንግስት፤ መንግስት፤ እንደሚባለው ነው ወይ? የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት የኛ ልጆች እኮ ናቸው ፈተና እየኮረጁ ያስቸገሩን:: ተማሪ ይኮርጃል፤ ሌብነት እርሱ ነው:: ተማሪን አትኮርጅ ሳንል መንግስት ከሆነ በኋላ አትስረቅ ብንል ዋጋ የለውም:: የሌላ ሰው እኮ አይደለም:: ከኬኒያ መጥቶ አይደለም የሚኮርጀው፤ የኛ ልጆች ናቸው የሚኮርጁት::

ሰራተኛ ብሎ መንግስት ቀጥሮ በሌለው ሃብት፤ የተቀጠረው ሰራተኛ አብዛኛውን ጊዜውን ቅድም ካልኳችሁ ውስን ጊዜ ውስጥ የሚያጠፋው ዩቲዩብ ላይ ነው:: ዩቲዩብ ማለት የአገር እና የሕዝብን ጊዜ ሰርቀህ አልባሌ ወሬ ስትሰማ መዋል ማለት ነው:: ዩቲዩብ ውስጥ አስተማሪ ጉዳዮች አሉ፤ ጠቃሚ ጉዳዮች አሉ:: እነርሱን በፕሮግራም ማድመጥ ጠቃሚ ነገር ነው:: ነገር ግን አብዛኛው ሰው ያለው እዛ አይደለም:: ይህ ሌብነት ነው:: ካሽ መቀባበል ብቻ አይደለም:: ምክንያቱም ጊዜን ስለሚበላ፤ ታናሽ ታላቅን አያከብርም፤ መከባበር የሚባል ነገር የለም::

ወንድ ሴትን አያከብርም፤ ዜጎች ሕግ አያከብሩም:: ሌብነት አደገኛ ካንሰር ነው:: የሞራል ዝቅጠት ነው:: ልማታችንን ይጥላል ስንል በእነዚህ አይቆምም:: የሃይማኖት አባቶች፤ ቅድም እንደተባለው የምዕመኖቻቸውን የተከታዮቻቸውን ሕይወት አስይዘው ቁማር ይጫወታሉ:: በነገራችን

# ወቅታዊ

ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት ተቋማት መሬት ሊዝ የማይከፍሉት፤ ኦዲት የማይደረጉት፤ ታክስ የማይከፍሉት የሃይማኖት ተቋማት እንዳሻቸው ይሁኑ የሚል ህግ ስላለ አይደለም:: እንደዛ ዓይነት ህግ የለም::

አሜሪካ ውስጥ የሃይማት ተቋማት ቤቱን ይገዛል:: ቤተክርስቲያኑንም ሆነ መስጂዱን ይገዛል:: ዝም ብሎ የሃይማኖት ተቋም ነው የሚባል ነገር የለም:: ኢትዮጵያ ውስጥ ያ የሚሆነው ለምንድን ነው? የሃይማኖት ተቋማት እንደአጋጣሚ ሆኖ የውስጥ ማንነት ይሰራሉ፤ ሞራል ላይ ይሰራሉ፤ ሰላም ወዳድነት ላይ ይሰራሉ፤ ግድየለም፤ አንዳንዱ ቢቀርም መንግስት የማይሸፍነውን ነገር ይሸፍናሉ፤ መሬት ቢቀር ፤ ኦዲት ባይደረጉ ችግር የለውም ፤ እኛ የማንሰራቸውና ወሳኝ ስራዎችን ስለሚሰሩ ይካካሳል ነው እሳቤው:: አሁን ያለው የተገላበጠ ነው:: ከፍተኛ ምዝበራ ያለው እዚያ ነው፤ የሞራል ዝቅጠት ያለው እዚያ ነው፤ እንኳን የውስጥ ማንነት ሊሰሩ የውስጥ ማንነት በይፋ እያፈረሱ ይውላሉ:: በዚህ ምክንያት ሌብነት በእያንዳንዱ ሰው ጓዳ ውስጥ በምርጫው የታቀፈው ካንሰር ሆኖ ይታያል:: ይህንን ካላስተካከለ ሪፎርሙ የተከበሩ ወንድሜ እንዳነሱት የትም አይደርስም::

ሃሳብ ላይ የጠራ ሃሳብ አለን፤ የጠራ ግንዛቤ አለን ሁላችሁም እንደምታውቁት:: ጊዜን በሚመለከት እንዳልኩት ነው ፤ ሰባት ቀን ነው የምንሮጠው፤ ውጤት ለማምጣት፤ ስፔስን በሚመለከት የምንዞረው የምናየው ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ሃብቶች ለማውጣት ነው:: በስራ መቼም አንታማም:: በስራ የሚያሙን ሰዎች ካሉ መቼም ስራ የማያውቁ ናቸው:: ከሞራል ጋር ተያይዞ ያለው ውስንነትና ድካም በጣም ስራ ይፈልጋል:: በካሽ ብቻ ካየነው ሁሉም ነገር አያመጣም:: ተቋሞቻችን በዚህ ውስጥ ነው ያሉት፤ የዚህን ሪፎርም ፈተና በአንዲት ቀላል ምሳሌ ማንሳት ይቻላል::

አራት ሽምግል ያሉ ታላላቅ ሰዎች ላልተወሰነ ጊዜ በአርምሞ በፀጥታ ሪፍሌክት እናድርግ፤ በጥሞና እንቆይ፤ እንፀልይ ብለው ይወስናሉ:: ንግግር አይፈቀድም፤ ከፈጣሪያችን ጋር ብቻ ነው የምናወራው ያም ንግግር የሚፈቀደው በአርምሞ በዝምታ ውስጥ ነው ብለው ተስማምተው ፀሎት ይጀምራሉ:: ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ጧፍ ለኩሰው እየፀለዩ እያሉ ንፋስ እየመጣ ጧፉን ለማጥፋት ይረብሻል:: ከአራቱ አንዱ ሰው ንፋሱ እኮ ጧፋችንን ሊያጠፋብን ነው ብሎ ይናገራል:: ሁለተኛው ሰው ዝም እንበል በል ተብሎ አልነበረም ወይ ይላል:: ሶስተኛው ሰው እናንተ ሁለት ሰዎች በጠበጣችሁን፤ ለምን ትናገራላችሁ ይላል:: አራተኛው ሰው ደግሞ ዋው እኔ ብቻ ቃሌን ጠበኩኝ ይላል::

የመጀመሪያው ንፋሱ በአፋ ሊያጠፋብን ነው ያለው ሰው የተፈጥሮን ፈተና መቋቋምና ቃል ለገባለት አላማ መቆም የማይችል ነው:: ምክንያት የሚፈልግ ማለት ነው:: ሁለተኛው ዝም እንበል ብለን አልነበረም ወይ የሚለው ሰው ከዋናው አላማው ከፀሎቱ ፤ ከስምምነቱ በላይ ህግ ያስጨንቀዋል:: ዝም እንበል የተባለበት ዋናው ምክንያት ለፀሎት ነው:: ዝም እንበል የተባለበትን ምክንያት ረስቶት ስምምነት ተጣሰ ይላል:: የሚስጨንቀው ህግ ነው:: ሶስተኛው ዝም አትሉም ወይ ያለው ሰው ትዕግስት የለውም:: መታገስ አይችልም:: መታገስ አይችልም ብቻ ሳይሆን በሰዎች ይሰናከላል::

ለምሳሌ ሪፎርሙ ችግር ያገጠመው የሚመስላቸው ሰዎች የምናቆም ይመስላቸዋል:: እኛ ግን አንቆምም፤ የጀመርንበትንም፤ የምንደርስበትንም እናውቃለን:: በሰዎች ንግግር የሚሰናከል ሰው ነው ሶስተኛው:: አራተኛው በሰራው ስራ ሳይሆን፤ በራሱ ውጤት ሳይሆን፤ በሰዎች ስህተት አንደኛ መሆን የሚፈልግ ማለት ነው:: በአንድ ደቂቃ ውስጥ ጧፉ ሊጠፋ ነው አለ፤ ዝም እንበል ተብሏል አለ፤ ዝም አትሉም ወይ አለ፤ እኔ ጠበኩኝ አለ:: ሁሉም የአምስት ደቂቃ ጉዳይ ነው::

በሰዎች ድካምና ስንፍና እሱ አንደኛ መሆን ይፈልጋል:: እንደዚህ አይነት ተግዳሮቶች ሪፎርሙ አሉበት:: የተፈጥሮ ህግ የማይቋቋሙ አሉ፤ ነገሮች በስምምነትና በህግ ያሉ ብቻ እንጂ ውጤት የማያዩ ሰዎች አሉ:: በሰዎች ድካምና ስህተት በቃኝ የሚሉ ሰዎች አሉ:: ምን አቃጠለኝ የሚሉ ሰዎች አሉ:: በቃን ምን አቃጠለን የሚሉ ሰዎች አሉ ፤ አንዳንዶች ደግሞ ሳይሰሩ በሌላው ድካም የተሻለ መስለው የሚቀርቡ ሰዎች አሉ:: ይህ ስራ ይፈልጋል::

ሪፎርማችን ከዚህ አንፃር ለማመን የሚከብዱ ውጤቶች እያመጣ ነው:: ለእናንተ አይደለም፤ ለእኔ ለራሴ ፤ የፈጣሪን ቸርነት፤ ደግነት የመከናወን የመጨረሻ ውጤት የሚታይባቸው አስደማሚ ነገሮች በሪፎርም እየመጡ ነው:: ዩቲብና ፌስቡክ የሚያወራውን አይደለም የምላችሁ፤ መሬት ላይ ያለውን ነው የምነግራችሁ፤ ለምሳሌ አንደኛው ከመንገድ ጋር ተያይዞ ያነሳችኋቸውን ጥያቄዎች በሚመለከት በጥቅሉ ላንሳ::

በኢትዮጵያ ውስጥ ከሪፎርሙ በፊት የመንገድ አውታር 127 ሺ ኪሎ ሜትር ነበር:: ይህ የገጠር መንገድ፣ ክልሎች የሚሰሩትን፤ የከተማ መስተዳደር የሚሰራውን፤ ፌዴራል መንግስት የሚሰራው ተደምሮ ነው:: ከሪፎርሙ በኋላ 165 ሺ ደርሷል:: ነገር ግን 165 ሺ ደርሷል ሲባል ቀድሞ የሚቆጠር መሬት አስፓልት የሚደገምም አለ:: 30 እና 40 ዓመት የሞላው አስፓልት ፤ አስፓልት የሚባል የነበረ፤ ግን የፈራረሰ አሁን ደግሞ እንደአዲስ የሚሰራ ሊኖር ይችላል:: ለምሳሌ ከጅማ አጋሮ እንደሚሰራው አይነት ማለት ነው:: ድሮም አስፋልት ነው፤ አሁንም የሚጠገን አስፋልት ነው:: በዚያም ይቆጠራል፤ በዚህም ይቆጠራል::

ነገር ግን የሚያስደነግጠው ነገር አጠቃላይ ኔትወርኩ ሳይሆን የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የሰራቸው ኮንክሪት አስፓልቶች ከሪፎርም በፊት 13 ሺ ኪሎ ሜትር ነበሩ:: ባለፉት ሶስት ዓመት ተኩልና አራት ዓመት ገደማ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ብቻ በአገር ደረጃ 4ሺ 700 ኪሎ ሜትር መንገድ አጠናቆ አስገብቷል አንድ፤ 8 ሺ113 ኪሎ ሜትር አሁን እየተገነባ ነው ያለው፤ ግማሹ በሚቀጥለው ዓመት አንዳንዱም ከሁለት ዓመት በኋላ የሚያልቅ ማለት ነው:: ተጨማሪ 9ሺ102 ኪሎ ሜትር እናንተ በጀት አፅድቃችሁ ፤ ኮንትራት ወጥቶለት ግማሹ ጨረታ ከወጣለት በኋላ በፀጥታ ምክንያት በጀት እያለው ያልተጀመረ፤ አንዳንዱ ኮንትራቱ ችግር ኖሮበት ተሰርዞ ድጋሚ የጨረታ ሂደት ላይ ያለ፤ ቢያንስ ግን በጀት የፀደቀለት፤ ያለቀና የተጀመረ ስትደምሩ 22ሺ ኪሎ ሜትር ነው::




**ባለፉት ሶስት ዓመት ተኩልና አራት ዓመት ገደማ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ብቻ በአገር ደረጃ 4ሺ 700 ኪሎ ሜትር መንገድ አጠናቆ አስገብቷል**

ይሄ የተረተረት ቁጥር አይደለም፤ መንገዶች ባለስልጣን ሄዳችሁ መቼ እንደተጀመረ? ከየት እስከየት ከተማ ተሰራ? በምን ያህል ገንዘብ ብላችሁ ማጣራት ትችላላችሁ:: ከ22ሺ ውስጥ 9ሺው በፀጥታና በአንዳንድ ምክንያት ያልተጀመረ ቢሆንም ድሮ የነበረን ያህል ቁጥር የሚያክል ግን ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን እየተገነባ ይገኛል:: ሪፎርሙ ያመጣው ውጤት ይሄ ነው:: ይህንን በአዲስ አበባ ብቻ እንመልከት፤ ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመት አዲስ አበባ ውስጥ 151 ኪሎ ሜትር አስፋልት መንገድ ተጠናቆ ስራ ጀምሯል:: አንዳንዱ እስከ 60 ሜትር ስፋት አለው:: 151 ኪሎ ሜትር ሲባል እንደገጠሮቹ ሰባት አስር ሳይሆን እስከ 60 ሜትር ስፋት አለው:: ከአስፓልት ውጪ 470 ኪሎ ሜትር ኮብልስቶን ተሰርቷል::

በጣም የሚገርመው እዚህ ምክር ቤት ላይ አዲስ አበባ ውስጥ በርካታ ሰዎች መኪና የላቸውም፤ ታስታውሶ እንደሆነ አስፋልት ብቻ ሳይሆን ሰፋ ያለ የእግረኛ መንገድ ያስፈልጋል ብዬ ነበር:: 116ኪሎ ሜትር ሰፋፊ የእግረኛ መንገድ ተገንብቷል:: ልክ በአራት ኪሎና ቸርቸር ጎዳና እንደምታዩት ወደሜክሲኮ እንደምታዩት ሰፋፊ የእግር መንገድ ከዚህ ቀደም በዚህ መጠን ያልነበረ፤ በዚያ ጥራትም ያልነበረ 116 ኪሎ ሜትር ተገንብቷል:: ይሄ ብቻ አይደለም ከተማ ውስጥ ትራፊክ መጨናነቅ ስላለ ማቋረጫዎች ተሰርተዋል:: ለምሳሌ ቦሌ ሚካኤል፤ ኢምፔሪያል፤ መብራት ኃይል አካባቢ እየተፈጠኑ ይገኛል:: ከሳርቤት ጎተራ ያለውና ሁለት ዓመት ተኩል የፈጀው መንገድ አሁን እያለቀ ነው:: ይህ መንገድ እንደምታውቁት በአዲስ አበባ ውስጥ ረጅም ታናል የያዘ ነው:: የመጀመሪያው ታናል የተገነባው አሁን ነው፤ ከፑሽኪን ጎተራ ያለው ማለት ነው::

**(ይቀጥላል)**

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› -ለአምራች ዘርፉ ችግር የመፍትሄ አማራጭ

**አንተነህ ቸሬ**

ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ዘርፍ እምቅ አቅም ያላት አገር ናት። አገሪቱ አምራች ኃይል አቅም፣ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ፣ ሕጋዊ ማዕቀፎችና ለዘርፉ እድገት አወንታዊ አስተዋፅዖ የሚያበረክቱ ሌሎች መልካም አጋጣሚዎችና አስቻይ ሁኔታዎችም አሏት። በኢንዱስትሪ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ ሽግግር እውን ለማድረግ ባለፉት ዓመታት በርካታ ተግባራትን አከናውናለች።

በዓይነትም ሆነ በብዛት በርካታ የሆኑት የዘርፉ ችግሮች፤ የመንግሥትን፣ የግሉን ዘርፍና በአጠቃላይ የሕዝቡን የተቀናጀ ጥረት የሚፈልጉ እንደሆኑ በተደጋጋሚ ሲነገር ቆይቷል። ለችግሮቹ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ብዙ ሙከራዎች ተደርገው የማይናቁ ውጤቶች ቢመዘገቡም፤ ከአገሪቱ አቅምና ከችግሮቹ ስፋት አንፃር ግን መፍትሄዎቹ የሚፈለገውን ያህል ውጤት ሊያስገኙ እንዳልቻሉ በተደጋጋሚ ተገልጿል።

ዘርፉ በግብዓት (ጥሬ ዕቃ)፣ በሰው ኃይል፣ በቦታ፣ በኃይል፣ በፋይናንስና በውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ችግሮች ተተብትቦ የተያዘ ነው። በዚህም ምክንያት ኢንዱስትሪዎች እያመረቱ ያሉት የአቅማቸውን ግማሽ ያህል ብቻ እንደሆነ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃዎች ያሳያሉ። በአሁኑ ወቅት የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአጠቃላይ ጥቅል አገራዊ ምርት የስድስት ነጥብ ስምንት በመቶ ድርሻ ያለው ሲሆን ይህን ድርሻ ወደ 17 ነጥብ ሁለት በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል። ከዚህ በተጨማሪም አሁን ያለውን 50 በመቶ የኢንዱስትሪዎች የምርታማነት አቅም ወደ 85 በመቶ የማድረስ እቅድም ተይዟል።

መንግሥት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ችግሮችን ለማቃለል እየተገበራቸው ከሚገኙ የመፍትሄ እርምጃዎች መካከል በቅርቡ ይፋ የተደረገው የ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ሀገራዊ ንቅናቄ ተጠቃሽ ነው። የሀገራዊ ንቅናቄው ዋና ዋና ዓላማዎች የአምራች ኢንዱስትሪውን ችግሮች በጋራ በመፍታት ለዘርፉ ዘላቂ ልማትና ተወዳዳሪነት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ዘርፉ ለኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግር የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲወጣ ማስቻል እንዲሁም በዘርፉ ያለውን የሥራ ባህል ማሻሻል ብሎም የኢንዱስትሪ ምርቶችን ጥራትና ተወዳዳሪነት በማሻሻል ገቢ ምርቶችን የመተካት ሽፋንን ማሳደግ ናቸው።

ንቅናቄው የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርትና ምርታማነት ለመጨመር ብሎም የዘርፉን ልማት ለመደገፍ እንዲሁም አምራች ኢንዱስትሪዎችን በጥራትና ቁጥር ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት የሚከናወኑበት ሲሆን የኢንዱስትሪ ዘርፉን ከተለመደው አሰራር በማሻገር ምርታማነትን ለመጨመር እንደሚያግዝ ታምኖበታል። በአሁኑ ወቅት ኢንዱስትሪዎች ለሀገር ውስጥ ምርት እድገት እያበረከቱት ያለውን አነስተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያሳድግም ተሥፋ ተጥሎበታል።

በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር የዘርፉን የማምረት አቅም ማሳደግ፣ ለዜጎች ተጨማሪ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ እና ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመተካት የውጭ ምንዛሬን ማዳን ከ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› መርሃ ግብር የሚጠበቁ ውጤቶች ናቸው።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ በንቅናቄው ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ላይ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ለማሳደግ በአገር ውስጥ የማምረት አቅምን ማሳደግ እንደሚገባና የአገር ውስጥ ምርቶችን መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ ተናግረው ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰኔ 7 ቀን 2014 ዓ.ም ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ማብራሪያም፣ በ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ የኢንዱስትሪ ዘርፉን

**የሀገራዊ ንቅናቄው ዋና ዋና ዓላማዎች የአምራች ኢንዱስትሪውን ችግሮች በጋራ በመፍታት ለዘርፉ ዘላቂ ልማትና ተወዳዳሪነት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ዘርፉ ለኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግር የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲወጣ ማስቻል እንዲሁም በዘርፉ ያለውን የሥራ ባህል ማሻሻል ብሎም የኢንዱስትሪ ምርቶችን ጥራትና ተወዳዳሪነት በማሻሻል ገቢ ምርቶችን የመተካት ሽፋንን ማሳደግ ናቸው**

ምርታማነት ለመጨመር እየተሠራ እንደሆነ ገልፀዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል የ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ ኢንዱስትሪዎች የገጠሟቸውን ችግሮች በመፍታትና ለምርታማነታቸው ማደግ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የኢንዱስትሪው ዘርፍ በአገራዊ ኢኮኖሚ የሚኖረውን ድርሻ ለማሻሻል ታቅዶ መተግበር እንደተጀመረ በንቅናቄው ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ላይ መግለፃቸው የሚታወስ ነው።

አቶ መላኩ በቅርቡ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ባዘጋጀው የድሬዳዋው የውይይት መርሃ ግብር ላይ ስለንቅናቄው ምንነትና ፋይዳዎች ገለፃ አቅርበው ነበር። የአምራች ዘርፉ እድሎችንና የመንግሥትን ትኩረት በተመለከተው በዚሁ ገለፃቸው ላይ አገሪቷ ያላትን ትልቅ የዘርፉን እምቅ ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ይቻል ዘንድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ተሞክሮዎችን በመቀመር በቅርቡ የ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ መጀመሩን ጠቁመው፣ የዚህ ንቅናቄ ምሠሦዎችም ባለድርሻ አካላትን ማሣተፍ፣ ዘርፉን በጥናትና ምርምር መደገፍ፣ ለዘርፉ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ማድረግ እና የአገር በቀል ምርቶችንና አመራረትን ማሳደግ መሆናቸውን አብራርተዋል። የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግርን ለመፍታት የመጀመሪያውና መሠረታዊው መፍትሄ የአገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ እንደሆነ ያስረዱት አቶ መላኩ፣ ከዚህ አንፃር ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ተናግረዋል። ‹‹ኢትዮጵያን ከኢንዱስትሪ ውጭ ማሰብ አይቻልም›› ያሉት አቶ መላኩ፣ መንግሥት የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን በመደገፍ ዘርፉን ለማጠናከር በ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ የአቅም ማጠናከር ሥራ እያከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ ንቅናቄው ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ የኢንዱስትሪ ምርቶችን አምርቶ ለመሸጥ እንዲሁም ከውጭ የሚገቡ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በአገር ውስጥ ለመተካትና የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅረፍ የምታደርገውን ጥረት ወደ ወሳኝ ምዕራፍ የሚያሻግር ተግባር እንደሆነም ገልፀዋል።

አገሪቱ ያላትን የኢንዱስትሪ አቅም ገቢራዊ ለማድረግ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍና ተወዳዳሪ ማድረግ ይገባል። የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ዘርፍ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍና ተወዳዳሪ የማድረግ ጉዳይ በምጣኔ ሀብት ትብብርና በእርዳታ ስም የሚደረግን የሀብታም አገራትንና የተቋሞቻቸውን ጣልቃ ገብነት በማስቀረት ሉዓላዊነትን እስከማስከበር ድረስ የዘለቀ ትርጉምና ፋይዳ አለው።

የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጀማል አህመድ በበኩላቸው በድሬዳዋው የውይይት መድረክ ላይ የግሉ ባለሀብት በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ስላለለው ተሳትፎ፣ ስላበረከተው አስተዋፅዖ እና ስላሉበት ችግሮች ባቀረቡት ገለፃቸው፣ መንግሥት የአገር ውስጥ አምራቾች እንዲበረታቱ ለዓመታት ያከናወነው ሥራ በተለያዩ ዘርፎች የግል ባለሀብቱ እንዲጠናከር አቅም መፍጠሩን ተናግረው፣ በሕዝቡም ሆነ በመንግሥት በኩል የአገር ውስጥ ምርት በመጠቀም ረገድ ያሉ ክፍተቶችን ማስተካከል እንደሚገባ ገልጸዋል። ለዚህም ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› የተሰኘው ንቅናቄ ትኩረት ተሰጥቶት በትክክል ከተተገበረ ትልቅ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ጠቁመዋል።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ‹‹ፍሮንቲየርአይ (Frontieri)›› ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ሞላ አለማየሁ ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› የተሰኘው ንቅናቄ አንድ አገር ባላት እምቅ ሀብት ላይ ተመስርታ ማምረት እንደሚገባት የሚጠቁም መርሃ ግብር እንደሆነ ያስረዳሉ።

‹‹በርካታ አገራት ዜጎቻቸው፣ ባለሀብቶቻቸውና የሌሎች ሀገራት ባለሀብቶችም በሀገራቸው እንዲያመርቱ ጥረት ያደርጋሉ። የኢትዮጵያም ጥረት ከዚህ የተለየ አይሆንም። ‹ኢትዮጵያ ታምርት› ሲባል አገራዊ የማምረት አቅሟን በማሳደግ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች የመተካት ተግባሯን ከማጠናከር ጋር ትስስር አለው›› ይላሉ።

እንደርሳቸው ገለፃ፣ ‹ለማምረት ምን ያስፈልጋል?› ለሚለው ጉዳይ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። የግብዓት እጥረት የአገሪቱ ኢንዱስትሪዎች ከግማሽ በታች በሚሆነው አቅማቸው እንዲያመርቱ ስላስገደዳቸው የማምረት አቅምን ለማሳደግ የግብዓት አቅርቦትን ማመቻቸት ይገባል። ንቅናቄው የአገር ውስጥ ባለሀብቶችም ሆኑ የውጭ ኢንቨስተሮች በኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ያስችላቸዋል። በተገቢው የፖሊሲ ማዕቀፍ እና በተቀናጀ ጥረት ከታገዘ ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ እጥረትንም ለማቃለል አማራጭ መፍትሄ መሆን ይችላል።

ንቅናቄው ካስገኛቸው ውጤቶች መካከል አንዱ ማምረት ያቆሙ ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ እንዲመለሱ ማገዙ ነው። በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ማምረት አቁመው ከነበሩ ፋብሪካዎች መካከል በንቅናቄው ትግበራ ከ118 በላይ የሚሆኑት ወደ ሥራ መመለሳቸውን የኢንዱትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ተናግረዋል።

በእርግጥ የንቅናቄው ውጤታማነት በመንግሥት ጥረት ብቻ የሚሳካ አይሆንም። አምራች ኢንዲስትሪው ለዘላቂ ልማት ዋነኛ ሞተር የመሆኑ እውነታ ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር አቶ መላኩ ከመንግሥት ጥረት ባለፈ ባለሃብቱም ተገቢውን የኢንዱስትሪ አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ ምርታማነትን ማሳደግ እንዳለበትም ተናግረዋል። ‹‹የሕግና የፖሊሲ አፈፃፀሞችን መከታተል እንዲሁም ከዚህ ቀደም የተተገበሩ አሰራሮችን መገምገም ያስፈልጋል፤የአመለካከት ችግሮችን የሚፈቱ ሥራዎችን ማከናወንም ያስፈልጋል›› ብለዋል።

ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት ዓመታት በኢንዱስትሪው ዘርፍ ለማሳካት የያዘችውን እቅድ ከግብ ለማድረስ ሚና እንደሚኖረው የታመነበት ይህ ንቅናቄ ዓላማውን እንዲያሳካ የተቀናጀ ተግባር እንደሚያስፈልግ ዶክተር ሞላ ይናገራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፤ ለመርሃ ግብሩ ስኬት የመንግሥት፣ የባለሀብቱና የሕዝቡ ድርሻ በግልፅ ሊታወቅ ይገባል። ንቅናቄው የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግብና ለዘላቂ መፍትሄ አጋዥ እንዲሆን በተገቢ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መደገፍ ይኖርበታል።

መንግሥት ንቅናቄውን እንዲሁም ዘርፉን ውጤታማ የሚያደርጉ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማዘጋጀት ምቹ የኢንዱስትሪ ከባቢን መፍጠር ይጠበቅበታል። የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራትና የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ለመደገፍ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል። መንግሥት ማበረታቻዎችን ሲያደርግም ማበረታቻዎቹ ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ማረጋገጥ አለበት። ከዚህ በተጨማሪም መንግሥት የመርሃ ግብሩን አፈፃፀም እየተከታተለና እየገመገመ ማስተካከያዎችን በማድረግ የአመቻችነት ሚናውን ሊወጣ ይገባል። ባለሀብቶችም አዳዲስ አሰራሮችን በመተግበር አቅማቸውን ማሳደግና ከመንግሥት የሚደረጉላቸውን ማበረታቻዎች በጥንቃቄ መጠቀም እንደሚኖርባቸውም ዶክተር ሞላ ይናገራሉ።

ኅብረተሰቡ ስለሚኖረው ሚና ደግሞ ‹‹ከሀገር ውስጥ ምርቶች ይልቅ ለውጭ ምርቶች የተሻለ ትኩረትና ፍላጎት የመስጠት አመለካከትን መቀየር ይገባል። የሀገር ውስጥ ምርቶችን በተጠቀምን ቁጥር የአምራቾቹን አቅም እያጎለበትን እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል›› ይላሉ።

የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና እድሎች እንዳሉ አይካድም። ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት አገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት በብዙ ርቀት ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ለወቅቱ የሚመጥን ተግባራዊ ምላሽ መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው። ለዚህ ደግሞ አገራዊ የማምረት አቅምን በማጎልበት የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ፣ ተጨማሪ የሥራ እድሎችን ለመፍጠርና ተወዳዳሪ አገራዊ ምጣኔ ሀብት ለመገንባት ያስችላል ተብሎ የታመነበት የ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ አማራጭ የመፍትሄ አቅጣጫ ነው።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# ሻምበል በላይነህ- እድሜውን ለህዝብና ለጥበብ የሰጠ ድምጻዊ

ዳግም ከበደ

### ጥበብን ፍለጋ

ወደ ሙዚቃ ሕይወት የገባው በአጋጣሚ አልነበረም:: አስቦበት በመሆኑ ያሳለፋቸው አስቸጋሪ ጊዜያትና የከፈላቸው ዋጋዎች ሁሉ አምኖበት ያደረጋቸው በመሆናቸው አይከፋባቸውም::እርሱ ከጥበብ ጋር ሲተዋወቅ ገና ነፍሱን ለሙያው አስገዝቶ ለመኖር ለራሱ ቃልኪዳኑን አስሯል:: ቃሉንም ጠብቆ በደስታና በመከራ ውስጥ እንዳከበራት ዛሬ ላይ ደርሷል:: ወደፊትም ፈጣሪ በሰጠው እድሜ ጥበብን በጥበብነቷ ተቀብሎ ነጻ ሊያወጣባት፤ ነጻነትንና እኩልነትን ሊሰብክባት፤ ታግሎ ሊያታግልባት፤ የተቸገሩ ሊያግዝባት፣ ሊደግፍባት ቃሉን አጽንቶላታል:: እድሜውን ለጥበብና ለህዝብ የሰጠው ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ::

ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ ከመሰንቆና ሙዚቃ ጋር የተዋወቀው በልጅነቱ ነው::ገና በለጋ እድሜው ከቦረቀባት የያኔው የጎንደር ክፍለ ሀገር ቃፍታ ሁመራ አካባቢ የለመዳትን ማሲንቆ ብቻ ይዞ ነው ወደ አዲስ አበባ የመጣው:: የማያውቃትን አዲስ አበባን የናፈቀበትና “አዲስ አበባ የሚባል አገር ውሰዱኝ” ብሎ ያለቀሰውን ሲያስታውስ ዛሬም ድረስ ይገርመዋል::አልቅሶም አልቀረ ለመሳፈሪያ የሚሆን ቤሳ ቢስቲን ባይኖረውም አንዱን ተሳፋሪ ለምኖ ነበር ከጭኑ ላይ ተቀምጦ ጥበብን ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ የገባው::

አዲስ አበባ እንደመጣ ያለችው ብቸኛ ወዳጅ ማሲንቆው ብቻ ስለነበረች በየመጠጥ ቤቱ እየዞረ በማሲንቆው እየተጫወተ የዕለት ጉርሱን ይሸፍን ነበር::በአንድ የተባረከች እለት ግን ማሲንቆው የሕይወቱን መስመር የሚቃኝበትን አጋጣሚ ፈጠረችለት::በዛች የተባረከች ዕለት “ኧረ ገዳሙ ገዳሙ ገዳሙ” እያለ ሲዘፍን ነበር አቶ ታደለ ይደንቃቸውና ሼህ ሙሃመድ ሁሴን አሊ አላሙዲን ያገኙት::በእድሜው ትንሽነትና በድምጹ ማማር የተደነቁት እነዚህ ባለሀብቶች ወደወዳጃቸው ወይዘሮ ጽጌ ባዩ ቤት ወስደው “ትንሽ አዝማሪ አምጥተንልሻል” ብለው አስተዋወቁት:: “እስኪ ዝፈን” ተባለና ያችን የሚያውቃትን ብቸኛ ዜማ “ኧረ ገዳሙን” ሲዘፍን ከድምጹ በላይ ልጅነቱ አሳዘናቸውና “ከዛሬ ጀምሮ ከዚህ ቤት አትወጣም! እዚሁ እንደልጄ ትኖራለህ፤ ትምህርት ቤትም ትገባለህ” ተባለ::

ከወይዘሮ ባዩ ውቤ ቤት ትንሽ እንደቆየም በ1972ዓ.ም ላይ አምባሳደር ቴአትር ቤት ሙዚቀኛ ይቀጥራል ተብሎ ሲሄድ ከነድምጻዊ ፀሐዬ ዮሐንስና ድምጻዊት አበበች ደራራ ጋር “እቴ ጥበብ ሸማ ጥበብ ሸማ ያገር ልጅ አይናማ” የምትለውን ዜማ በማዜም በድምጻዊነትና በማሲንቆ ተጫዋችነት ተቀጠረ::

ለድምጻዊ ሻምበል በላይነህ ያ ዘመን ከጎንደሬነት ወደ ኢትዮጵዊነት የተቀየረበት ምርጡ ዘመን ነበር:: ምክንያቱ ደግሞ የብዙ ብሔር ብሔረሰብ ሙዚቃዎችን፣ ባህልና ቋንቋዎችን በማወቁ ኢትዮጵያ የገዘፈችበት ጊዜ እንደነበር ያስታውሳል::

አምባሳደር ቴአትር ቤት እንደተቀጠረ የመጀመሪያዬ የሚላትን ሙዚቃ ከድምጻዊ ንዋይ ደበበ ጋር ቢሰራትም በማስታወቂያ ሚኒስቴር ግምገማ እንዳትደመጥ ተደረገች:: ተስፋ ያልቆረጠው ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ ከነ ጋሽ ሙላቱ አስታጥቄና ድምጻዊ ማህሙድ አህመድ ጋር በኢትዮ ስታር ባንድ አማካኝነት በአረብ አገራት እየዞሩ ይዘፍኑ እንደነበር ያስታውሳል::ከዛም ወደ አሜሪካ ጥሪ መጥቶለት ሰርቶ ተመልሷል:: ከዛም “አንች ባለድሪ... አብረሽኝ አደሪ” የተሰኘችውን ዜማ ከድምጻዊት ራሄል ዮሐንስ ጋር ሲዘፍን በትክክልም ድምጻዊነቱን አረጋግጦ በመላው አገሪቱ ተወዳጅነት እና ተቀባይነትን አገኘ:: በመቀጠልም “አሞራ በሰማይ ሲያሽ ዋለ” የተሰኘውን ካሴት አወጣና በመላው ኢትዮጵያ ተወዳጅነትን ይበልጥ አተረፈ::

### ጥበብን በስደት

በወቅቱ ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ በስራዎቹ



ተወዳጅነትን ቢያተርፍም የወቅቱ የአገሪቱ ሁኔታ ያሳስበው እንደነበር ያስታውሳል::የ1983 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ በነበረው ጦርነት ነገሮች ጥሩ ባለመሆናቸው ባህር ማዶ ተሻግሮ ኑሮውን አሜሪካ ላይ ይመሰርታል::በአሜሪካ ቆይታውም ከይልማ ገብረአብ እና ከተስፋ ብርሃን ጋር በርካታ ስራዎችን ሰርቷል::በተለይም “ዜሮ ለዜሮ”፣ “ታሪክ ይፍረደው” እና “ኢትዮጵያ” የተሰኙ አልበሞቹ የወቅቱን ሁኔታ ያንጸባረቁና የሕወሓትን ስውር አላማ የሚያጋልጡ በመሆናቸው በመንግስት ጥርስ ተነከሰበት::ተቃዋሚ ተብሎ ተፈረጀና ወደ አገር ውስጥ መግባቱ ቀርቶ በአውሮፓና በአሜሪካም ስራዎቹን እንዳያቀርብ ወከባዎችም ጠነከሩበት::

“አሞራ በሰማይ ሲያይሽ ዋለ” የተሰኘውና በተወዳጅነቱ በብዙ ድምጻውያን የሚዜመውን ሙዚቃ አስመራ ውስጥ በኤርትራውያን ባንድ ነበር የሰራው::አሞራ በሰማይ ሲያይሽ ዋለን ብዙ ሰዎች ከመስራታቸው የተነሳም የመጀመሪያው ዘፋኝ ማን እንደ ሆነ መዘንጋቱን የሚናገረው ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ፣ ብዙዎቹ ሙዚቃዎቹ በሌሎች ድምጻውያን በመዜማቸው ቅሬታ ባይኖረውም ስሙን በመጥቀስ አሻሽለው ቢሰሩት መልካም ነበር ይላል::

በመቀጠልም የስደት ፍሬዎቹ የሆኑት “ሳብየ ኧረ ነይ ሳብየ”፣ “አሞግሱት አሉ” እና “የአባይ ዳር እንኮይ ሎሚ” የተሰኙት ሙዚቃዎቹ በመላው ዓለም ይበልጥ ተወዳጅ ሆኑለት::

“ከአባይ ዳር እንኮይ ሎሚ፣
ከወሎ ልጅ ከዳሚ፣
የለም የሚለኝ ማነው፣
አላምነው::
እጥፍ ዘርጋ እያለች የልቤ ሰላይ፣
መጣች የወሎ ልጅ በገራዶ ላይ” በማለት በምናቡ የሳላትን የወሎ ጉብል የገለጸበት ሙዚቃ ዛሬም ድረስ ምስል ከሳችና ለወሎዬዎች ያለውን ፍቅር የገለጸባት እንደሆነ ይሰማዋል::

### አብዮተኛው ድምጻዊ

በሕወሓት አገዛዝ ዘመን ይደርስ የነበረውን አፈና ቀድሞ የተቃወመው ሻምበል በላይነህ፤ ሕወሓት የኢትዮጵያዊነት ጸር መሆኑን በመረዳቱ፤ በፖለቲካዊ ትግል እንደማይወድና፤ የትጥቅ ትግል ብቸኛው አማራጭ እንደሆነ አምኖ ኤርትራ በረሃ ድረስ ገብቶ የትጥቅ ትግሉን ተቀላቅሎ እንደነበርም ይናገራል:: ሰራዊቱን በሙዚቃ ከማነቃቃት ባለፈም ስልጠና ወስዶ ብረት አንስቶ ለመፋለም ቆርጦ የተነሳበት ጊዜም ነበር::ወደ ወልቃይት በመምጣትም “ወልቃይት ጎንደር እንጂ ትግራይ ሆኖ አያውቅም” የሚለውን ሙዚቃ ቦታው ድረስ በመሄድ ታሪክ አጣቅሶና በመረጃ አስደግፎ በሰራው የሙዚቃ ክሊፕ ሙያውን ለእውነቱ አበርክቶታል::

ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ በዚህ ሁሉ ትግሉ፤ በውጭ አገር የሚገኙ አፍቃሪ ወያኔዎች የሙዚቃ ኮንሰርቶችንና በምሽት ቤቶች እንዳይሰራ ያላደረጉት ጥረት አልነበረም:: “የቀረው ይቅር እንጂ አገር አፍራሹን ወያኔን ደግፌ አልቆምም” በማለት የራሱን ጥቅም ጥሎ ለአገሩ ነጻነት ከ30 አመታት በላይ ሲታገል ቆይቷል::

“የወያኔ ደጋፊዎች 30 አመታትን ያለስራ ቢያስቀምጡኝም ጠንካራ ኢትዮጵያውያንም ነበሩና ድጋፋቸው አልተለየኝም” የሚለው ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ፤ በቅርቡ በነበረው የህልውና ዘመቻ እንደሌሎቹ ዲያስፖራ በገንዘቡ ብቻ አልነበረም የዘመተው:: በአካል ግምባር ድረስ ገብቶ በሙያው ለመፋለም በማሰብ ቤተሰቦቹን ሳያሳውቅ ወደ ኢትዮጵያ መጣ::በትክክል ግንባር ድረስ ገብቶ ለመታገል የሚያመቸውን መንገድ ሲፈልግ በራስ ተነሳሽነት ወደ ግንባር የዘመቱ “ዜማዎችን ለኢትዮጵያችን ዘማች ኪነት” የሚባል ስብስብ እንዳለ ሲሰማ እነርሱን አፈላለገ::በግጥምና ዜማ ደራሲው ተስፋ ብርሃን አማካኝነት ቡድኑን ተቀላቅሎ ከአንድ ወር ላላነሰ ጊዜ በግምባር የሚገኘውን ሰራዊት በማነቃቃት አገራዊ ሚናው ተወጥቷል::

በተለይም በጋሸና እና በላሊበላ ከተማ በነበረው ወሳኝ ግንባር ተገኝቶ ከሰራዊቱ ያገኘውን አድናቆት መቼም እንደማይዘነጋው ይናገራል:: በወረታ፣ በመራዊ፣ በመቄት በጋሸናና በላሊበላ መድረኮቹ ሙያዊ አበርክቶው የታዘበውን ሲናገር፤ “ከወታደሩ ወኔ በላይ ከሰራዊቱ ጎን በመሆን ግንባር ድረስ አብረው የዘመቱ ባለሀብቶችን ተግባር የሚደንቅ ነበር:: ብዙ ባለሀብቶች ጠፍተው ወደሌላ አገር መሄድ እየቻሉ ከሰራዊቱ እኩል ቀድመው በመገኘት ሰራዊቱን ሲያበረታቱና ሲመግቡ የነበሩትን በአካል አግኝቼ አድንቄያቸዋለሁ ኮርቸባቸዋለሁም” ይላል::

ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ ዘመቻውን ለታይታ ያደረገው ባለመሆኑ ወታደር ጋር ሂደው ፎቶ እየተነሱ የሚመለሱት አርቲስቶች እውቅና ሲሰጣቸው እርሱ አስታዋሽ በማጣቱ አላኮረፈም::ለአገር የሚደረግ ማንኛውም ተግባር ሽልማቱና እውቅናው የህሊና እርካታ እንደሆነ ይናገራል:: “በዛን አስቸጋሪ ወቅት በሙያዬ ማድረግ የሚገባኝን ባላደርግ ኑሮ የዕድሜ ልክ ጸጸት ይሆንብኝ ነበር፤ ግን ደግሞ በአስቸጋሪው ወቅት ግንባር ድረስ ተገኝቼ ከሰራዊቱ ያገኘሁት ምላሽ ከእውቅናና ሽልማት በላይ ሆኖልኛል” በማለት በኩራት ይናገራል::

ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ ህዝብ ለህዝብ ላይ የነበረው ሚና ጉልህ እንደነበር ብዙዎች ይመሰክሩለታል::በወቅቱ ለህዝብ ለህዝብ ቡድን የሚሆን አልባሳት መግዣ 80ሺ ብር ጠፍቶ ጉዞው ሊሰረዝ ሲል እሱና ክቡር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሰሰ አዋጥተው እንዲገዛ አድርገዋል:: አልባሳቱ ከተገዛ በኋላ ጓድ መንግስቱ ኃይለማሪያም ስራውን እንዳዩ ባስቸኳይ ሁሉም ነገር እንዲደረግና ጉዞው እንዲካሄድ በማዘዛቸው ገንዘባቸው እንደተመለሰላቸውም ያስታውሳል::

ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ በህዝብ ለህዝብ ጉዞ የታየው ኢትዮጵያዊ አንድነት ዛሬም እንዲመለስ ይፈልጋል:: በወቅቱ አሜሪካኖች ጉዞው እንዲሰናከል በገንዘብ ከማማለል ጀምሮ መኖሪያ ፍቃድ በመስጠት ለማስከዳት ያደረጉትን የመበተን ጥረት ሳይሳካ የህዝብ ለህዝብ አንግቦ የተነሳው ዓላማ መሳካቱን ሲያሳብ ይደነቃል::

### ጥበብን ለበጎነት

ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ በበጎነቱም ይታወቃል::በአሜሪካን አገር ቆይታው 30 አመት ሙሉ ለአገሩና ለህዝቡ ነው የኖረው:: ለራሴ የሚለው ጊዜና ገንዘብ አልነበረውም፤ ይህን የሚመሰክሩለት አስተባብሮና ለምኖ ካሳከማቸው በላይ አሜሪካን አገር የሚኖሩ የሙያ አጋሮቹ ናቸው::

የአምባሰሏ ንግስት ድምጻዊት ማሪቱ ለገሰ በታመመችበት ወቅት ማሲንቆውን ይዞ እየዞረ ለምኖ እንድትታከም አድርጓል::ድምጻዊ አክሊሉ ስዩም፣ ድምጻዊት ዘሪቱ ጌታሁን፣ ድምጻዊ ታምራት ሞላ ታመው ህክምና ባስፈለጋቸው ጊዜ ጀርመንና ለንደን ድረስ በመሄድ ገንዘብ አሰባስቦ ህክምና እንዲያገኙ አድርጓል:: ኮቪድ-19 (ኮረና) ወደ ኢትዮጵያ የገባ ጊዜ ስራ ያቆሙ አርቲስቶችን ለመደገፍ የሙያ አጋሮቹን በማስተባበር ገቢ ሰብስቦ በአቻሬ ጫማ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ልኮ ድጋፍ አድርጓል::

አገሩ በችግር ላይ ሆና ገንዘብ ማሰባሰብ እንደሚያስፈልግ ከሰማ እንቅልፍ አይወስደውም:: በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደር በኩል በሚቀርብለት ጥሪ ሁሉ ቀድሞ ከተፍ ይላል፤ ከሙያዊ አስተዋጽኦ ባለፈ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላሮችን አሰባስቧል::

ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ ስሜተ ስሱ ነው::ያለውን ክህሎት በሙሉ ለሰዎች ሲያውለው ይበልጥ ይደሰታል:: ያኔ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) በታሰረበት ወቅት እንደማናችንም ስሜቱን በከንፈር መምጠጥ አልነበረም የገለጸው፤ በዜማው ነበር በግፍ መታሰሩን የተቃወመው:: “ወትሮም የካሳ ልጅ ቴዲ ሞት አይፈራም” በማለት አሞግሶ አዚሞለታል:: ሰዎች ፍትህ ሲጓደልባቸው አይወድም::በቴዲ አፍሮ መታሰር ከማዘን ባለፈ ከአሜሪካ ተነስቶ እንግሊዝ ለንደን ድረስ በመሄድ ሰላማዊ ሰልፍ አስተባብሮ ድርጊቱን ሲቃወም የቀደመው አልነበረም:: የአሁኗ ምርጫ ቦርድ ኃላፊ ብርቱካን ሚዴቅሳ ያኔ ከወያኔ የእስር ቤት ስቃይ በኋላ ወደ አሜሪካ ስትመለስ “የሴቶች አንበሳ ብርቱካን ሚዴቅሳ” በተሰኘው ዜማ ደማቅ አቀባበል አድርጓል::ለታማኝ በየነም ቢሆን ጀግንነቱን፣ አገር ወዳድነቱን እያየ ዝም ለማለት አልደፈረምና፤

“ብን ብሎ ቢጠፋ ሁሉም እየጣለህ፤
ከሺ መንገደኛ ታማኝ ትበልጣለህ” ብሎ አሞግሶ አዚሞለታል::በአሜሪካን ቆይታው ሶስት ልጆችን አፍርቷል::የሱን ሙያ የተከተለ ልጅ የለውም::ምክንያቱ ደግሞ በታዋቂነቱ ሲጠቀም፤ እንደ ሌሎቹ አሜሪካዊ ድምጻውያን ሀብት ባላማካበቱና የተረጋጋ ሕይወት ሲያሳልፍ ባለማየታቸው እንደሆነም ይናገራል::

### “እንቁናት ኢትዮጵያ”

ከ33ዓመት በኋላ ወደአገሩ የመጣው ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ “እንቁናት ኢትዮጵያ” የተሰኘ የሲዲ ምርቃትና የሙዚቃ ኮንሰርትን አካቶ በስካይ ላይት ሆቴል ሰኔ 16/2014 ዓ.ም ከአድናቂዎቹ ጋር ለመገናኘት ቀጠሮ ይዟል:: በዚህ መርሃግብር ከአድናቂዎቹ ጋር ከመገናኘት ባለፈ “የድሮ ዘፈኖቼን ሰብስቤ በአዲስ መልኩ የማሳተሜ ዋናው አላማ ዘፈኖቹ የኔ መሆናቸውን እንዲታወቅልኝ ነው” በማለት የመርሃ ግብሩን አላማ ተናግሯል::

በድምጻዊ ሻምበል በላይነህ የአልበም ምርቃት ላይ ከአንጋፋዎቹ ጀምሮ አዳዲሶቹ ሙዚቀኞችን ጋብዟል::ሁሉም ድምጻውያን በነጻ እንዲታደሙ አድርጓል::ሊደግፉት የሚፈልጉ ባለሀብቶች ብቻ ናቸው የመግቢያ ከፍለው የሚታደሙት ብሏል::

ወደፊትም በርካታ ግጥምና ዜማዎች እጁ ላይ ስላሉት ዘመኑን የሚዋጁ ጥሩ ጥሩ ስራዎችን ከግጥም ደራሲው ተስፋ ብርሃን እና ከዜማ ደራሲው አበበ ብርሃኔ ጋር ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ተናግሯል::አሁን ለአድማጭ በሚደርሰው አልበም ሁለት አዳዲስ ዜማዎች የተካተቱበት ሲሆን ቀሪዎቹ ተወዳጅ የሆኑ የቀድሞ ስራዎቹን አካቶበታል::

### መልዕክት

በመጨረሻም “የአገራችን ችግር እንደ ባህል ሆኖ እየቀጠለ ነው:: 30 ዓመት ሙሉ ብቻዬን ታገልኩ ለውጥም አምጥቻለሁ ብዬ አስባለሁ፤ የተሳሳትኩትም ነገር ይኖራል ብዬ አምናለሁ:: ይሁን እንጂ አሁን የተጠናወተን የዘር ፖለቲካ ለልጅ ልጆቻችን አልፎ ሊያጫርሰን አይገባም:: አንድ ቦታ ላይ ሊቆም ይገባል:: ዓለም በኢኮኖሚ እየጠነከረ ባለበት ዘመን እኛ እርስ በእርስ እንጋጫለን::ጦርነት ለማንም አይጠቅምም፣ ለልጅ ልጅ እያስተላለፈን የምናስጨርስበት መሆን የለበትም” በማለት ይናገራል::

“ጠንካራ መሪ ጠንካራ ህዝብ ይፈጥራል፤ ጠንካራ ህዝብም ጠንካራ መሪ ያወጣልና በ ”ፌስ-ቡክ” የሚመራ ህዝብ የትም አይደርስምና ህዝቡ በእውቀት ይመራ፤ አንድነቱን ያስቀድም” በማለት መልእክቱን አስተላልፏል::

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## አማኝ አሰሪና ታማኝ ሠራተኛ!

**ሰላማዊት ውቤ**

ስለ ቤት ሠራተኛና አሰሪ ብዙም መልካም ነገሮች አይደመጥም። ሁለቱም በየፊናቸው ቻል አድርገውት ቢቀመጡም አንዳንድ ጊዜ ግን ተግባቦታቸው ላይ ችግሮች ያጋጥማሉ። የብዙዎቹን የአሰሪና ሠራተኞች ግንኙነትን የእሳትና ጭድ ማለቱ እንደሚሻል የገለፁልንም አሉ።

የአሰሪና የቤት ሰራተኞችን ግንኙነት እንዲህ የሚያሻክረው ምንድነው? ስንል ላነሳነው ጥያቄ ወይዘሮ ዝማም ጅሮ የቤት ውስጥ ፍጆታ እንደሆነ አጫውተውናል። ወይዘሮዋ በተለይ አሁን ባለው የኑሮ ውድነት እሳትና ጭድ የሚያደርጋቸው እንደ ዘይት ያሉ በውድ ዋጋ እየተገዙ ያሉ የምግብ ግብዓቶች በክነት መሆኑን ይናገራሉ ። ይህንን መሰሉን የቤት ውስጥ ፍጆታ መቋቋም ያልቻሉት አሰሪዎች ግብዓቶቹን ከመቆለፍ ጀምሮ ሰፍረው እስከመስጠት ደርሰዋል።

የሥራ ጫና፤ የዕረፍት ጊዜ በአግባቡ አለመስጠት፣ የትምህርት ጥያቄ አለመመለስ፤ ዝቅተኛ ደመወዝና ሌሎችም አሰሪና ሰራተኞች ከማይግባቡባቸው ሌሎች ምክንያቶች መካከል ይጠቀሳሉ።

ዛሬ ልናነሳ የወደድነው ለብዙዎች አሰሪና የቤት ሠራተኞች አርአያ ስለሆኑ ግለሰብ ነው። አሰሪዋ ወይዘሮ አልማዝ ለማ በቅርቡ በቤት ውስጥ ለስምንት ዓመት ስታገለግላቸው የነበረችውን የቤት ሰራተኛቸውን አስተምረው አስመርቀውና ድረው ለወግ ማዕረግ ያበቁ ናቸው።

ሰራተኛዋ በለጡ ሞገስ ከወይዘሮ አልማዝ ጋር የኖረችባቸው ስምንት ዓመታት ምንም ዓይነት የባዕድነት ስሜት ያልተሰማት ራሷን እንደ ሰራተኛ ሳይሆን እንደቤተሰብ ቆጥራ በፍቅርና በጥሩ መግባባት አብራ መኖሯን ትናገራለች። እንደ ቤተሰብ እንዴውም ልክ እንደ ቤቱ ባለቤት ነው አይታ የኖረችው። ባለቤቶቹም ቢሆኑ ከዚህ በተለየ እንደቤት ሰራተኛ አይተዋት አያውቁም። አንቺ እንዳልሽ ነው የሚሏት።



ፎቶ፡ አዮብ ተፈሪ

ወይዘሮ አልማዝ ለማ



ወይዘሮ በለጡ ሞገስ

በመሆኑም በሁሉም ነገር ወሳኝ ነበረች። በተለይ ወይዘሮ አልማዝ አብዝተውም ይተማመኑባት ስለነበር ‹‹ሌላው ቀርቶ አልሚ መኖሪያ ቤቷን ስታስገነባ ለኮንትራክተሩ የግንባታ ቁሳቁስና የሰራተኛ ወጪ በቅርበትና በፍጥነት እንድሰጠው በብዙ መቶ ሺዎች የሚቆጠር ብር እኔ ጋር ነበር የምታስቀምጠው›› ብላናለች። ሽሮና በርበሬ ወይም ዘይት አለ የለም፤ በመባባል ጭቅጭቅ የለም። መቆለፍ የሚባል ነገር ፍፁም አያውቁም። የሚያስፈልጋት ሁሉ ፍጆታ በእጇዋ ነው። የሚያስፈልገውን በሙሉ አስባ ነው የምትሰራውና ይሄን ሥሪ ብለው አዘዋትም አያውቁም። አንዳንዴ እሷ ሥራ ላይ ሳለች ልጆቹ ድንገት ያልታሰበ ነገር ይሰራልን ብለው ቢሉም አሰሪዋ ይሄን ትተሽ እነሱ ያሉትን አድርጊ ብለው በትዕዛዝ አያጨናንቋትም። እሳቸው ራሳቸው የሚሰሩበት ጊዜም አለ። ‹‹ዘመድ አዝማድም ሆነ ጎረቤት ሲመጣ ቡና አፍይ ወይም እንዲህ አድርጊ የሚለኝ የለም›› ስትልም የሚገባውን ሁሉ አስባ እንደምታደርግም ነግራናለች። በለጡ እንደምትለው አሰሪዋ እንደ ታናሽ እህታቸው ነው የሚያይዋት። ጎረቤት ወይም እንግዳ መጥቶ ሠራተኛሽ ሲሏቸው ደስ አይላቸውም።

‹‹በእርግጥ አስተምሮ፣ ድሮ ኩሎ የሚሸኝ አሰሪ ለእኔ ከእህትም በላይ ነው›› የምትለው በለጡ ቅዳሜና እሁድ አስተምረው ከመደወላቦ ዩኒቨርሲቲ በአካውንቲንግ በዲፕሎማ እንዳስመረቋትም ትናገራለች። 10ኛ ክፍል ፈተና ተፈትና ውጤት ሳይመጣላት በቀረበት ወቅት በዘመድ እነ ወይዘሮ አልማዝ ቤት መቀጠሯን የምታስታውሰው በለጡ ዘንድሮ ድረው ኩለው የሴትነት ክብሯን ለማየት ያበቋት መሆኑንም ትናገራለች።

‹‹እኔ ታማኝ የሆንኩት አሰሪዬ ታማኝና ፈራሂ እግዚአብሔር ያላት ስለሆነች ነው›› አንዳንድ አሰሪዎች ሁሉንም ፍጆታ ቆልፈው መሄዳቸው ሳያንስ ማታ ወደቤት ሲገቡም ለምን ይሄ አልተሰራም ለምን ያ አልሆነም እያሉ ቁም ሰቅል የሚያሳዩም እንዳሉም ትናገራለች። ነገር ግን ኃላፊነት መስጠት፤ ማመንና ማክበርም ከጭቅጭቅ አድኖ አብሮ እንደሚያከርምም ትናገራለች።

አሰሪዋ ወይዘሮ አልማዝ ለማ በበኩላቸው ለኔ መልካም የሆነችልኝ እኔ መልካም ስለሆንኩላት ይሆናል። ሰራተኞቻችንን እንመናቸው፤ ኃላፊነት እንስጣቸው፣ እናክብራቸው። ክፉ የሚሆኑት እኛ ክፉ ስለምንሆንባቸው ነው። እኔ የሚያስፈልጋትን ፍጆታ ደብቄባት ብወጣ ስላልሰጠኋትና ሰርታ ስለማትቆየኝ ከሥራ ስመለስ መነጫነጭ ነው የሚሆነው ይላሉ። ስለሚያምኗትና እንደ ታናሽ እህታቸው ስለሚያይዋት ቆልፈውባት የሚሄዱትም የለም። መኖሪያ ቤታቸውን በሚገነቡበት ወቅት ኮንትራክተሩ ይዛው ብትጠፋስ ብሎ እስከሚገረም ድረስ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ገንዘብ ከባንክ አውጥተው ለሚያስፈልገው ግብዓት መግዣ ሁሉ እየቀነሰች እንድትሰጠው ማድረጋቸውን ይናገራሉ ።

በለጡ እኔ አዝዣት የምትሰረው ነገር የለም የሚሉት አሰሪዋ ከጠዋቱ 11 ሰዓት ከመኝታዋ ተነስታ ለልጆቹም ለቤተሰቡም የሚያስፈልገውን ሰርታ ምሳ ቋጥራ ትሸኛለች። እዚህ ላይ ግን እኔ እንደዚህ አድርጊው የምለው ነገር የለም ሁሉንም የምትሰራው ራሷ አስባ ነውም ይላሉ። ‹‹የራሷ ፕሮግራም አላት። ማታ ስመጣ ቁጭ ብላ ፊልም ስታይ ወይም የምትወደውን ፕሮግራም በቴሌቪዥን ስትከታተል ነው የማገኛት›› በዚህ ምንም ቅር አይለኝም ምክንያቱም ሁሉንም የሚጠበቅባትን አከናውና ስለሆነ የምትቀመጠው በማለትም የልጅቷን ትጉነት ይመሰክራሉ። ልብስ በማሽን እያጠበች ከጎን ሌሎች ሥራዎችን ትሰራለች። እሷን እረፍት ሰደው እሳቸው ኃላፊነቱን በሚወስዱበት ሰዓት ግን እንኳን ሊያርፉና ፊልም ሊያዩ የጣዱትን ይረሱታል። ምሳቸውንም ዘንግተውት ይውላሉ። ‹‹እኔ ቤቴን ብዙም አላውቀውም የጎደለውን ሞልታ አስተካክላ የምትጠብቀኝ በለጡ ነች›› የሚሉት አሰሪዋ ወይዘሮ አልማዝ ሲሰሩም፣ ሲማሩም ሲወልዱም ብዙዎቹን ኃላፊነቶች የምትሸፍንላቸው አጋዣቸው እንደነበረች ያወሳሉ። ሁለት ልጆቻቸውን እንደራሷ ልጆች ተንከባክባ አሳድጋላቸዋለች። አስተምረው ድረው ኩለው የሸኟትም ለዚህ ነው። የሌሎቹም ግንኙነቶች እንዲህ ቢሆኑ ስንመኝ ከሴቶችና ማህበራዊ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ እንደሚያሳየው በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት የተሻለ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን በመግለጽ ነው።

# ዓለም አቀፍ

## “መንግሥት ወደ ትግራይ ክልል ያልተገደበ ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ እያደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ ነው”

- የዓለም የምግብ ፕሮግራም

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ትግራይ ክልል ያልተገደበ ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ እያደረገ ያለውን ጥረት እንደሚያደንቁ የዓለም የምግብ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተር ዳቪድ ቢስሌይ ገለጹ።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን የዓለም ምግብ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተር ዳቪድ ቢስሌይ እና የስዊድን ዓለም አቀፍ ትብብር ሚኒስትር ማቲልዳ ኤርንክራንስን ትናንት በጽህፈት ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋል።

የስዊድን ዓለም አቀፍ ትብብር ሚኒስትር ማቲልዳ ኤርንክራንስም የኢትዮጵያ መንግሥት ለዜጎች ሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረስ እያደረገ ያለውን ጥረት አድንቀዋል።

በውይይቱ በግጭት እና በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች ስለሚደረገው ሰብዓዊ ድጋፍ፣ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ከተካሄደው ጦርነት ጋር ተያይዞ ስለሚነሱ የግልጽነት ጉዳዮች እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግሥት የጋራ መተማመንን በመፍጠር ረገድ እየወሰዳቸው ስላሉ እርምጃዎች ላይ ትኩረት ተደርጓል።

አቶ ደመቀ መኮንን የስዊድን መንግሥት እና የዓለም የምግብ ፕሮግራም በኢትዮጵያ ሰብዓዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ላደረጉት ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል።

በቅርቡ በሰመራ እና ሰርዶ ኬላዎች በመገኘት ወደ ትግራይ ክልል የሚላከውን የሰብዓዊ ድጋፍ ሁኔታ መገምገማቸውን ያስታወሱት አቶ ደመቀ፣ ሰብዓዊ አገልግሎት የሚሰጡ አጋሮች ያለገደብ እንዲንቀሳቀሱ መንግሥት ቁርጠኛ አቋም ያለው መሆኑን ገልጸዋል።

ነዳጅ እና ማዳበሪያን ወደ ትግራይ ክልል በመላክ ረገድ የሰብዓዊ ድጋፍ ተቋማት በጋራ ሊሠሩ እንደሚገባ በውይይቱ ወቅት መገለጹን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

## ፓኪስታን ዜጎቿ የሻይ ፍጆታቸውን እንዲቀንሱ ጠየቀች

የፓኪስታን ዜጎች በአገሪቱ ያለውን የምጣኔ ሃብት ቀውስ ለማረጋጋት የሚጠጡትን የሻይ መጠን እንዲቀንሱ ተጠየቁ። የፓኪስታን ከፍተኛ ሚኒስትር አህሳን ኢቅባል፣ በቀን ጥቂት ብርጭቆ ሻይ መጎንጨት ፓኪስታን የሻይ ቅጠል ምርትን ከውጭ ለማስገባት የምታወጣውን ወጪ ይቀንሳል ብለዋል።

በአገሪቱ ያለው የውጭ ምንዛሬ ክምችት ከውጭ የሚገባ ማንኛውም ምርት ለመግዛት የሚበቃው ከሁለት ወር ላነሰ ጊዜ ብቻ ነው ተብሏል። ይህም አገሪቷን አስቸኳይ የገንዘብ እርዳታ እንድትፈልግ አስገድዷታል። ፓኪስታን ባለፈው ዓመት ከ600 ሚሊየን ዶላር በላይ የሚያወጣ ሻይ ቅጠል ከውጭ በማስገባት ከዓለም ከፍተኛውን ሻይ ቅጠል አስመጪነት ቦታን ይዛለች።

እንደ ፓኪስታን ሚዲያ ከሆነ ሚኒስትር ኢቅባል “የአገሬው ሰው የሻይ ፍጆታውን ወደ አንድ ወይም ሁለት ብርጭቆ እንዲቀንስ እጠይቃለሁ። ምክንያቱም ሻይ ቅጠል የምናስገባው በብድር ነው” ብለዋል። ከዚህም በተጨማሪ የንግድ ተቋማት የሚጠቀሙትን የኤሌክትሪክ ኃይል ለመቆጠብ የንግድ ቦታቸውን ምሽት 2፡30 ላይ እንዲዘጉ ሚኒስትሩ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ተማፅኖው ለፓኪስታን ሕዝብ የቀረበው የአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ክምችት በተከታታይ እና በፍጥነት እየቀነሰ መምጣቱን ተከትሎ ነው። ይህም በአገሪቱ፣ መንግሥት ምርቶችን ከውጭ ለማስገባት የሚያወጣቸውን ወጪዎች በመቀነስ ያለውን የውጭ ምንዛሬ ክምችት ይዞ እንዲያቆይ አስገድዶታል። የአገሪቷ ሕዝቦች የሻይ ፍጆታቸውን እንዲቀንሱ መጠየቃቸው በማኅበራዊ ሚዲያ መነጋገሪያ ሆኗል።

አብዛኛው ሰውም አገሪቷ የገጠማት ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ቀውስ የሻይ ፍጆታን በመቀነስ ይፈታል የሚል እምነት የለውም። የፓኪስታን የውጭ ምንዛሬ ክምችት



የካቲት ወር ላይ ከነበረው 16 ቢሊየን ዶላር በሰኔ ወር የመጀመሪያ ሳምንት ወደ ከ10 ቢሊየን ዶላር በታች አሽቆልቁሏል። ባለፈው ወር የካራቺ ባለሥልጣናት በአገሪቷ ያለውን የውጪ ምንዛሬ ክምችት ለመጠበቅ በርካታ መሠረታዊ ያልሆኑ የቅንጦት እቃዎች እንዳይገቡ ገደብ ጥለው ነበር።

በአገሪቷ ያለው የምጣኔ ሃብት ቀውስ፣ ባለፈው ሚያዝያ ወር በተደረገው የምክር ቤት ምርጫ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢምራን ካህንን ለተኩት ሸህባዝ ሸሪፍ መንግሥት ትልቅ ፈተና ሆኗል።

ሸሪፍ ሥልጣን ተረክበው ቃለ መሃላ ከፈጸሙ በኋላ የአገሪቷ ምጣኔ ሃብት በአግባቡ አልተመራም፤ ወደ ትክክለኛው መንገድ ለመመለስም ከባድ ነው ሲሉ የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር ከሰዋል። ባለፈው ሳምንት ካቢኔው፣ የተቋረጠውን የ6 ቢሊየን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም እንዲጀመር ዓለም አቀፉን የገንዘብ ድርጅት (አይኤምኤፍ)ን ለማሳመን የ47 ቢሊየን ዶላር በጀት አጽድቋል።

አይኤምኤፍ እአአ በ2019 በውጭ ምንዛሬ እጥረት እና ለዓመታት በዘገየ እድገት ምክንያት የሚፈጠር የምጣኔ ሃብት ቀውስን ለማቃለል የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ተስማምቶ የነበረ ቢሆንም፣ አበዳሪዎች አገሪቷ ብድሩን ለመክፈል ያላትን የፋይናንስ አቅም ከጠየቁ በኋላ መቆሙን ቢቢሲ ዘግቧል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን

# ስፖርት

ሐሙስ



ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት
ነው!

## ዋልያዎቹ- በስቴድየምና በበጀት እንቅፋቶች መካከል

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን(ዋልያዎቹ) የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ የምድብ የመጀመሪያ ሁለት ጨዋታዎችን አድርገው በማላዊ ቢሸነፉም ግብፅን አሸንፈው ያልተጠበቀ ውጤት አስመዝግበዋል። ይህም በቀጣይ የአፍሪካ ዋንጫ ለመሳተፍ ያላቸውን ተነሳሽነትና ተስፋ አሳድጎታል። ይሁን እንጂ ዋልያዎቹ ሕዝብን ያስደሰተ ውጤት አስመዝግበው በጥሩ መነቃቃት ላይ ባሉበት በዚህ ወቅት ከመጪው መስከረም ጀምሮ በሚያደርጓቸው የማጣሪያ ጨዋታዎች ሁለት እንቅፋቶች ሊፈትኗቸው እንደሚችሉ ከማላዊው ጉዞ በኋላ ፌዴሬሽኑ ባለፈው ሰኞ ከሰጠው መግለጫ ለመረዳት ተችሏል። አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የፌዴሬሽኑ የጽሕፈት ቤት ሀላፊ አቶ ባህሩ ጥላሁን በመግለጫው በሰጡት ማብራሪያ፣ ዋልያዎቹ በገለልተኛ አገር ጨዋታዎችን ለማካሄድ ከመገደዳቸው ጋር ተያይዞ ፌዴሬሽኑ ከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ የሚያወጣ በመሆኑ ከገንዘብ እጥረት ጋር በተያያዘ ያለው ስጋት አሁንም እንዳልተቀረፈ አስረድተዋል።

ፌዴሬሽኑ በማላዊ ባደረጋቸው ሁለት ጨዋታዎች ለስቴድየም ኪራይና ለሌሎች ወጪዎች ከ50 ሺ ዶላር በላይ ወጪ ማድረጉ ኪሱን በእጅጉ ቢጎዳውም በጨዋታዎቹ ወቅት ከማስታወቂያና ከትኬት ሽያጭ ካወጣው የበለጠ ያላሰበው ገቢ ማግኘቱ ይታወቃል። ያም ሆኖ ያለበት የገንዘብ እጥረት ወደ ፊት ብዙ የሚያራምደው እንዳልሆነ ተጠቁሟል።

‹‹አሁን ላይ በተለያዩ የገበያ አማራጮች አስፍተን ገንዘብ መስራት ችለናል። መንግስትም ደግሞ አሁን የተመዘገበውን ድል በመመልከት የሆነ ነገር ያደርግልናል ብለን እንጠብቃለን። አስቀድመንም ጥያቄያችንን አቅርበናል። ይሄ ነገር ይሆናል የሚል እምነት አለን። ከገንዘብ እጥረት ጋር በተያያዘ የተጋረጠብንን አደጋ ለጊዜውም ቢሆን ቀንሷል፣ ግን አሁንም በዚሁ መልኩ የሚቀጥል ከሆነ ፌዴሬሽኑ አቅሙ እየተሟጠጠ ነው የሚመጣው››በማለት አቶ ባህሩ ያለውን ስጋት ገልጸዋል። በቀጣይ ጨዋታዎች ተመሳሳይ ገቢ ማግኘት ላይቻል እንደሚችል የጠቆሙት አቶ ባህሩ፣ ፌዴሬሽኑ የተረጋጋ የፋይናንስ ጉዞ ላይ ነው ብሎ መናገር እንደሚከብድ አብራርተዋል።

ዋልያዎቹ ቀሪዎቹን ሁለት ጨዋታዎች በሜዳቸው የማካሄድ ጉዳይን በተመለከተ ዋና ጸሐፊው ከጋዜጠኞች ለተነሳላቸው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ “ከስታዲየም ጋር ተያይዞ እኛ ከባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጋር ነው እየተነጋገርን ያለነው። በተጨማሪም በአንድ መድረክ ከጠቅላይ ሚኒስትር ማኅበራዊ ዘርፍ አንድ ተወካይ መጥተው ጥያቄያችንን አቅርበናል። ገና ድልድሉ ሳይታወቅ እንደ ኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አቋማችንን አሳውቀን ነበር። እንግዲህ ለሚመለከተው አካል ጥያቄው ቀርቧል ወይስ አልቀረበም የሚለውን ማጣራት ያስፈልጋል። ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጉዳዩን በደንብ ያውቀዋል። የጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮም እንደዛው፣ ግን ጥያቄው ለሚመለከተው አካል ቀርቧል የሚለው መታየት አለበት። እኛ አሁንም መግፋታችንን እንቀጥላለን” በማለት ተናግረዋል።

“እኛ ስለ አዲስ አበባ ስታዲየም ብቻ አይደለም የምናወራው” ያሉት አቶ ባህሩ፣የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በባለቤትነት ከሚያስተዳድራቸው ስታዲየሞች መካከል የአዲስ አበባ ስታዲየም ላይ የማሻሻያ ስራዎች



የኢትዮጵያ እግር ካስ ፌዴሬሽን የጽሕፈት ቤት ሃላፊ
አቶ ባህሩ ጥላሁን፣

እየተሰሩ መሆኑን ጠቁመዋል። ቶሎ ለማድረስም ሙከራ ላይ መሆናቸውን ገልጸው ፌዴሬሽኑም የተመለከታቸው ነገሮች እንዳሉ አብራርተዋል። የፌዴሬሽኑ ፍላጎት የትኛውም ስታዲየም ቶሎ እንዲደርስና ዋልያዎቹ ጨዋታቸውን በአገራቸው እንዲያደርጉ መሆኑን አያይዘው ገልጸዋል።

“የባህር ዳር ስታዲየም ጥቃቅን ስራ ብቻ አይደለም የሚቀረው። ይሄንን ሁሉም ሰው ሊያውቀው ይገባል። በጣም ብዙ ነገር ነው የሚቀረው። ስታዲየሙ ትልቅ ነው ግን የጎደሉት ነገሮች ጥቃቅን ናቸው ብለን የምንተዋቸው አይደሉም፣መመርመር አለብን። ቢያንስ አንድ ቦታ ላይ የስትራክቸር ችግር እንዳለበት (የሚዲያ እና የቪ አይ ፒ) ተነስቷል። ይሄንን ለማስተካከል ምን ያህል ወጪ ይጠይቃል። ሌሎችን የተዘረዘሩትን ነገሮችንም መመልከት ያስፈልጋል። አሁን እኩል ትኩረት ተሰጥቶ ስታዲየም እንዲደርስልን እንፈልጋለን። ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚደርስ ስታዲየም ካለ እሰይ የሚያሰኝ ስለሆነ እዛ ላይ ትኩረት ይደረግልን ነው እያልን ያለነው” በማለት ዋና ጸሐፊው ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ዋልያዎቹ በመጪው መስከረም የሚያደርጉት ጨዋታ ከመድረሱ በፊት በተቻለ መጠን የአዲስ አበባ ስታዲየምን ለውድድር ለማድረስ እንደሚሰራ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ለፌዴሬሽኑ መናገሩን የጠቆሙት አቶ ባህሩ፣ ጨዋታዎቹን በገለልተኛ አገር መጫወት የፌዴሬሽኑ አስተዳደራዊ የሆኑ ወጪዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጫና እንደፈጠረ ተናግረዋል። እነዚህን አስተዳደራዊ ወጪዎች ፌዴሬሽኑ በተለያዩ መንገዶች ለመሸፈን ሞክሯል።

ዋልያዎቹ ቀጣዮቹን ጨዋታዎች በሜዳቸው ማድረግ ካልቻሉ ፌዴሬሽኑ ምን አይነት አማራጭ እቅድ እንዳስቀመጠ ለተነሳው ጥያቄ “ስለቀጣይ ለማውራት ከባድ ነው ግን ማላዊ ያለው ነገር በጣም ጥሩ ነው። ግን ይሄንን የሚወስነው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ነው። ስለዚህ አንዱ አገር ላይ ውሳኔው ይተላለፋል። እኛ ግን አሁንም ይሄኛው የሚያልቅልን ከሆነ ስቃያችን ይቀንሳል ብለን ነው የምናስበው። ያለበለዚያ ግን ከፍተኛ ችግር ውስጥ ነው እየገባን የምንሄደው” በማለት አቶ ባህሩ ምላሽ ሰጥተዋል።

ኢትዮጵያ በከፍተኛ ወጪ እያስገነባችው የሚገኘውን የአደይ አበባ ብሔራዊ ስቴድየምን በተመለከተ ካፍ ግንባታውን ከአመት በፊት አህመድ ሀራስ በሚባል የክለብ ላይሰንሲንግ ባለሙያ አማካኝነት መመልከቱን ያስታወሱት አቶ ባህሩ፣ ባለሙያው ስታዲየሙ አስፈላጊ መስፈርቶችን ባሟላ መልኩ እየተገነባ እንደሚገኝ አስተያየት መስጠታቸውን ገልጸዋል።

EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

## ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## በማዕከላዊ ቅርንጫፍ የምግብ ደህንነትን የማስጠበቅ ተግባር


**ታምራት ተስፋዬ**

የኢትዮጵያ ምግብና መድህኒት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 1112 /2011 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት አገር ውስጥ የሚመረቱና ከውጭ የሚገቡ ምግብ መድህኒትና የህክምና መሳሪያዎች ጥራት፣ ደህንነት፣ፈዋሽነት ያረጋግጣል። በዚህም ህብረተሰቡን ጥራት ፣ደህንነትን ብቃቱ ካልተጠበቀ ምግብና መድሃኒት ይከላከላል። ይሕን ሃላፊነቱን ለመወጣትም በዋና መስሪያ ቤትም ሆነ በቅርንጫፎች ጣቢያዎቹ የተደራጁ የተለያዩ የቁጥጥር ክፍሎች አሉት። እንደ ባለስልጣን መስሪያ ቤት በአገሪቱ የተለያዩ ክልሎች ሰባት ቅርንጫፎች አሉት። የማእከላዊ ቅርንጫፍ ከእነዚህ አንዱ ነው።

በማዕከላዊ ቅርንጫፍ በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ አምስት መግቢያ መውጫዎች አሉ። በኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎና በመንገደኞች አገልግሎት ሁለት ቅርንጫፍ ቢሮ አለ።ቃሊቲ ወደብና ተርሚናል፣ በአዳማ እንዲሁም በሞጆ ወደብና ተርሚናል ቢሮዎች አሉት።

አቶ አያልሰው መለሰ በኢትዮጵያ ምግብና መድህኒት ባለስልጣን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ሃላፊ ናቸው።በእነዚህ መግቢያ መውጫ ቁጥጥር ጣቢያዎ የምግብ ደህንነትን በማረጋገጥ ረገድ ምን እንደሚከናወን፣ በዘንድሮው በጀት አመት ያለፉት አስራ አንድ ወራት የተከናወኑ ተግባራትን በሚመለከት ቆይታ አድርገናል።

አቶ አያልሰው እንደሚገልፁትም፣ ተቋሙ ቁጥጥር የሚያደርግባቸው ምርቶች መግቢያ መውጫዎች ላይ ሲደርሱ የጥራት፣የደህንነት፣ፈዋሽነት እና ብቃት ደረጃቸው ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል። በመውጫ መግቢያዎች በኩል ምርቶች ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡም ሆነ ከአገር ወደ ውጭ ሲወጡ ማለፍ ያለባቸው ከደህንነት ከጥራት፣ ከብቃት አንጻር የተለያዩ መስፈርቶች አሉ።በተቋሙ በተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት መሰረት የቁጥጥር ስራ ይሰራል።



አቶ አያልሰው መለሰ

በህጋዊ መንገድ ማረጋገጫ አግኝተው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን በሚመለከት የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት አለማሟላታቸውን ይፈትሻል። ያረጋግጣል። መስፈርቱን የሚያሟሉትን ያስገባል፣ የማያሟሉትን ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ክልከላ ያደርጋል።

የምግብን ጥራት ደህንነት ማረጋገጥ የተቋማችን ዋነኛ ተግባር ነው። ይሕን ለማከናወን መግቢያ መውጫ ኬላ ከመድረሱ አስቀድሞ የሚሰሩ ስራዎች አሉ። የምግብ ምዝገባ ስርአት አለ።በዚህ ሂደት ምግቡን የሚያመርተው አካል ማነው? በምን አይነት መልኩ ጥራትና ደህንነቱን ይጠብቃል? የሚለው ይቃኛል። በአስመጪው በኩል ለተቋሙ የሚቀርቡ መረጃዎች ይገመገማል። ይሕ በአግባቡ ማለፍ ሲችል ይመዘገባል። ይሕን የሚያደርገው በተቋሙ የምግብ ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ነው። ይህ ከተደረገ በኋላ ምግቡ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ የገበያ ፈቃድ ያገኛል።

የምግብናን ጥራትና ደህንነት ከምናስጠብቅባቸው መስፈርቶች አንዱም ምግቡ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተመዘገበ ነው ወይ? የሚለው በመቃኘት ነው። የአስተሻሸግና ገላጭ ፅሁፍ ረገድም የተቀመጡ መስፈርቶች አሉ። የመጠቀሚያ ጊዜ፣ ተመጋቢው ማድረግ ያለበት ጥንቃቄ፣ ምግቡ ከምን ከምን እንደተሰራ መግለፅን ጨምሮ የተለያዩ መስፈርቶች ተቀምጠዋል። እነዚህ መስፈርቶች መሟላታቸው መግቢያ መውጫ ላይ ይፈተሻል። ይረጋገጣል።

አንድ ምግብ መግቢያ መውጫው ኬላ የሚደርሰው በተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮች ተጓጉዞ ነው። በጉዞ ወይንም በአቀማመጥ ወቅት ምግቡ ብልሽት ሊያጋጥመው ይችላል። መግቢያ መውጫ ላይም ምግቡ በአግባቡ መጓጓዙን እንዲሁም መቀመጡ ይፈተሻል። ይረጋገጣል።

ናሙና ተወስዶ በላብራቶሪ ፍተሻና ውጤት በኢትዮጵያ ደረጃ መሰረት ማሟላት አላማሟላቱ ውሳኔ ይሠጥበታል። መስፈርቶቹን የማያሟሉ ምግቦች ከሆኑ ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ወይንም አገር ውስጥ እንዲወገድ ይደረጋል። ከመውጫ መግቢያዎች ከወጣ በኋላ እንኳን ምርቱ ችግር ቢገጥመው፣ እራሱን የቻለ ክፍል አለ። ክትትል ይደረግበታል። ድህረ ገበያ ተሰብስቦ ይመረመራል። ምርቱ ችግር ካለበት ከገበያ የሚሰበሰብብበት አሰራር ተዘርግቷል።

በዚህ መልክ ቁጥጥር ሚደረግባቸው በህጋዊ መንገድ ቀረጥ ተከፍሎባቸው መንግስት አውቋቸው የሚገቡ ናቸው።ሌሎች መውጫ መግቢያ አካባቢ በተለያየ በህገ ወጥ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ይኖራሉ።ይሕንም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የመቆጣጠር ስራ ይሰራል።

ከዚህ አልፎ በተለያዩ ምክንያቶች መውጫ መግቢያዎች ላይ ቀሪ የተደረጉ፣መግባት የሌለባቸው ተብለው የተቀመጡ የምግብ አይነቶች አሉ። እነዚህም በምን አግባብ ነው የተቀመጡት፣ ቀሪ የተደረጉት ምግቦች አሉ ወይንስ ተወግደዋል ወይ የሚሉ ስራዎች ይሰራሉ።

በአሁን ወቅት መግቢያ መውጫዎች ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን የማያሟሉ ምርቶች ይመጣሉ።ሰነዶች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ሳይሟሉ ይመጣሉ። ከአጓጓዝ ጋር በተገናኘ እንዲሁም የገላጭ ጽሁፍና አስተሻሸግ ችግር ያለባቸው ምርቶች ይመጣሉ።

እንደ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት በአምስቱ መውጫ መግቢያዎች ባለፉት አስራ አንድ ወራት ውስጥ ጥራትን ደህንነት ፈዋሽነትና ብቃታቸው የተረጋገጡ ምግቦች ወደ አገር ውስጥ ገብተዋል። መስፈርቱን የማያሟሉ ምርቶች እንዳይገቡ ተደርጓል።

ባለፉት አስራ አንድ ወራትም አንድ ሚሊየን አራት መቶ ሰላሳ አምስት ሺ ስምንት መቶ ሜትሪክ ቶን የሚመዝን ምግብ ወደ አገር ውስጥ ገብቷል። ሰባት መቶ አስራ አራት ሜትሪክ ቶን ምግብ ጥራትና ደህንነት መስፈርት ባለማሟላት ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ፣ገብቶም እንዳይሰራጭ መግቢያ መውጫዎች ላይ እንዲያዝ ተደርጓል።በዚህም በበጀት አመቱ የምግብን ደህንነት ከማሥጠበቅ አንስቶ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ምርቶች ወደ አገር በማስገባትና የማያሟሉትን በማስመለስ ረገድ ስኬታማ ተግባራት ተከናውኗል።

ምርቶች አምልጠው ገበያ ላይ ሊገኙ የሚችሉት በአብዛኛው በህገ ወጥ መልኩ ወደ አገር የሚገቡት ናቸው። በህጋዊ መንገድ የሚገቡት የተመዘገበ መረጃ ያላቸው እንደመሆኑ በቀላሉ በቁጥጥር ለመያዝና ችግሮችን ለማስተካከል ያስችላል። ይሕ ማለት ችግሮች የሉም ማለት ሳይሆን መቶ በመቶ የቁጥጥር ስርአት ተዘርግቷል የሚል እምነት የለም።

እንደ ተቋም ብዙ መስራት እንዳለብን እናምናለን። ቁጥጥር ውስብስብ ስራ ነው።አንድ ተቋም ብቻውን የሚሰራው አይደለም። ሌሎች ቁጥጥርን የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት አሉ። ከእነዚህ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት ያስፈልጋል።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/